# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት - አንደኛ

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-2)

I. አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት (1፥3—2፥10)

(ሀ) ድነት በእምነት መሆኑ (1፥3-12)

(ለ) ቅድስና በመታዘዝ የሚገኝ መሆኑ (1፥13—2፥10)

II. አንድ አማኝ ከሌሎች ጋር ያለው ግንኙነት (2፥11—3፥12)

(ሀ) ለማንኛውም ሰው ሊኖር ስለሚገባ ኀላፊነት (2፥11-17)

(ለ) በቤት ውስጥ ሊኖር ስለሚገባ ኀላፊነት (2፥18—3፥7)

1. ባሮች ለጌቶቻቸው ሲሉ መወጣት የሚገባቸው ግዴታ (2፥18-25)
2. ሚስቶች ለባሎቻቸው ሲሉ መወጣት ያለባቸው ግዴታ (3፥1-6)
3. ባሎች ለሚስቶቻቸው ሲሉ መወጣት ያለባቸው ግዴታ (3፥7)

(ሐ) አማኝ ከሌሎች ጋር ማድረግ የሚገባውን ግንኙነት በተመለከተ የመርሖች አጥርታ (3፥8-12)

III. አማኝ ሥቃይን እንዴት መቀበል እንዳለበት (3፥13—5፥11)

(ሀ) በሥቃይ ውስጥ ጸንቶ መገኘት (3፥13—4፥11)

1. ምክንያቱም ከበደል ነጻ ተሁኖ ካለ ሥቃይ ውስጥ ሲገባ በረከት ስለሚገኝ ነው (3፥13-17)
2. ምክንያቱም ክርስቶስ የላቀና ኀያል የሆነ ምሳሌያዊነት በማሳየቱ ነው (3፥18—4፥6)
3. ምክንያቱም የመጨረሻው ጊዜ አጣዳፊ በመሆኑ ነው (4፥7-11)

(ለ) በሥቃይ ውስጥ እያሉ ሐሤት ማድረግ (4፥12-19)

1. ምክንያቱም እምነታችን የቱን ያህል እውነት እንደ ሆነ ስለሚፈተን ነው (4፥12)
2. ምክንያቱም በክርስቶስ ሥቃይ ውስጥ መሳተፍ በመሆኑ ነው (4፥13ሀ፥14-16)
3. ምክንያቱም ክብር ላለው ዳግም ምጽአቱ ስለሚያዘጋጀን ነው (4፥13ለ፥17-19)

(ሐ) ሥቃይ በሚደርስ ጊዜ የተሰጠ ምክር (5፥1-11)

1. ለሽማግሌዎች - በጎችን ጠብቁ (5፥1-4)
2. ለጕልማሶች (5፥5-11)

*መደምደሚያ* (5፥12-14)

**ጸሓፊ፤** *ጴጥሮስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ለክርስቶስ ብሎ መሠቃየት*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *60—63 ዓ.ም*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይህ ሐዋርያው ጴጥሮስ ከጻፋቸው ሁለት መልእክቶች የመጀመሪያው ነው (1፥1፤ 2ጴጥ 1፥1)። የመጀመሪያ መልእክቱ ሲጻፍ ሲላስ (በግሪክ "ሲልባኖስ") ጸሓፊው ሆኖ (5፥12) በእርሱ ረዳትነት የተጻፈ መሆኑን ጴጥሮስ ራሱ ይመሰክራል። የሲላስ ከፍተኛ የግሪክ ቋንቋ ችሎታና የአጻጻፍ ስልት በዚህ መልእክት ላይ ተንጸባርቆአል፤ ይህ እንደ ተጠበቀ ሆኖ የጴጥሮስም የግሪክ ቋንቋ ችሎታ ከከፍተኛ የግሪክ ቋንቋ ችሎታ በታች

መሆኑ በሁለተኛው መልእክቱ ላይ ይታያል። የ1ኛ ጴጥሮስ መልእክት ድምፀትና ይዘት ስለ ስምዖን ጴጥሮስ ከምናውቀው ጒዳይ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከጌታ ኢየሱስ ጋር ያሳለፋቸው ጥብቅ የኅብረት ዓመታት የኢየሱስን ሞትና (1፥11፡19፤ 2፥21-24፤ 3፥18፤ 5፥1)፥ ትንሣኤ (1፥3፡21፤ 3፥21)፣ በግሩም ሁኔታ አስታውሶ ለመጻፍ መሠረቶች ናቸው፤ እንዲያውም በገሊላ ያየውን የኢየሱስን ድኅረ ትንሣኤ መገለጥ ኢርቱዕ በሆነ መልክ የሚያመለክት ይመስላል (2፥25፤ 5፥2ሀ ይመ፤ ከዮሐ 21፥15-23 ጋር ያነጻጽሩ)። በተጨማሪም በዚህ መልእክትና በየሐዋርያት ሥራ ላይ በሰፈረው በጴጥሮስ ስብከት መካከል ኢያሌ ተመሳሳይነት ይታያል። ጴጥሮስ ይህን መልእክት የጻፈው በሮም ግዛት፣ “በእስያና ... ተበትነው በመጻተኞች ለሚኖሩ” ወገኖች ነው (1፥1)። ከእነዚህ አንዳንዶቹ በጰንጠቆስጤ ዕለት ለጴጥሮስ ስብከት ልባቸውን በመስጠት ያገኙትን አዲስ እምነት ይዘው ወደየገራቸው ከተሞች የተመለሱ ናቸው (ከሐሥ 2፥9-11 ጋር ያነጻጽሩ)። እነዚህ አማኞች፥ “እንግዶችና መጻተኞች” ተብለዋል (2፥11)። “እንግዶችና መጻተኞች” የተባሉትም የክርስቶስ ጠላት በሆነው ዓለም ውስጥ ክርስቲያናዊ ጒዞአቸው እንዳለና ከዚሁ ዓለምም ስደት ሊደርስባቸው እንደሚችል መገንዘብ እንዳለባቸው ለማስታወስ ነው። ጴጥሮስ ይህን መልእክት የጻፈበት ምክንያት በእስያ የሚኖሩ አማኞች መንግሥት ሊያባብሰው የሚፈልገው (2፥12-17) ተቃውሞ እያደር እየባሰበት መሄዱን ጽፈውለት ስለ ነበር (4፥12-16)፣ የተከሠተውን ተቃውሞ አስመልክቶ የሰጠው ምላሽ ሳይሆን አይቀርም።

ጴጥሮስ ይህን መልእክት የጻፈው፥ “በባቢሎን” ሆኖ ነው (5፥13)። ይህ እንግዲህ በቀጥታ አመለካከት በመስጴጦምያ የምትገኘው ባቢሎን ልትሆን ትችላለች፤ ወይም ደግሞ በመጀመሪያው ምእተ ዓመት የነበረችው ትልቋና የተደራጀችው ፈሪሀ እግዚአብሔር አልባዋ የሮም ከተማ በዘይቤያዊ አገላለጽ ስትታይ ሊሆን ይችላል። ጴጥሮስ በባቢሎን ውስጥ የሚገኙትን እውነተኛ አይሁድ አንድ ጊዜ የጎበኘ ቢሆንም እንኳ፣ በ60ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ጴጥሮስ፣ ሲላስና (5፥12) ማርቆስ (5፥13) በቀጥታ በተገለጸችው ባቢሎን ነበሩ ከማለት ይልቅ፣ ሁሉም ያን ጊዜ በአንድ ላይ በሮም ከተማ ሳይኖሩ አልቀረም ማለቱ ይቀላል (ቈላ 4፥10 ይመ፤ ጴጥሮስና ማርቆስ አብረው በሮም የነበሩ ስለ መሆናቸው ፓፒያስ የሰጠውን አስተያየት ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ)። ኔሮ በሮም ውስጥ ካደረሰው አሠቃቂ ደም መፋሰስ (64 ዓ.ም.) ቀደም ብሎ ጴጥሮስ በሮም ውስጥ እያለ ከ60—63 ዓ.ም. ይህን መልእክት ሳይጽፍ አልቀረም።

### ዐላማ

ጴጥሮስ ለአማኞች ስለ ምድራዊ ሕይወታቸው መለኮታዊና ዘላለማዊ እይታ ለመስጠትና እንዲሁም በጣዖት አምላኪ ማኅበረ ሰብ ውስጥ ሆነው ከባድ በሆነ የሥቃይ ፈተና ውስጥ በማግባት ላይ ለሚገኙት ክርስቲያኖች በተግባር የተፈተነ ምሪት ለመለገስ፣ በሐሤት የተሞላ ተስፋ ያለበትን ይዞ ይህን መልእክት ጻፈ። ክርስቲያኖች ያላግባብ የመንግሥትን መዋቅር ማወክ እንደሌለባቸው፣ ሥቃይንም በንጹሕ ልብ፣ በጽድቅና በጨዋነት በመቀበል ረገድ የክርስቶስን ምሳሌ እንዲከተሉ ጴጥሮስን አሳስቦት ነበር።

### ቅኝት

አንደኛው የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት ለአማኞች የሚከተሉትን በማሳሰብ ይጀምራል፦ (1) በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባለ ክብር የሆነ ጥሪና ሰማያዊ ርስት እንዳላቸው (1፥2-5)፤ (2) እምነታቸውና ፍቅራቸው በዚህ ዓለም ውስጥ በሚኖሩት ሕይወት በፈተናና በመታነጽ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት፥ ጌታ ሲገለጥም ምስጋናን፥ ክብርንና ሞገስን የሚያስገኝ እንደሚሆን (1፥6-9)፤ (3) ይህ ታላቅ ድኅነት በብሉይ ኪዳን ነቢያት አስቀድሞ ታይቶ እንደ ነበር (1፥10-12)፥ (4) አማኞች በዙሪያቸው ካለው ዳግም ልደትን ካላገኘው ዓለም በተለየ ዐይነት ቅዱስ ሕይወት መኖር እንዳለባቸው (1፥13-21)። የተመረጡትና የተቀደሱት አማኞች (1፥2)፣ ንጹሕ የሆነ የቃሉ ወተት የሚያስፈልጋቸው (2፥1-3) ታዳጊ ሕፃናት መንፈሳዊ ቤት ለመሆን የሚሠሩ (2፥4-10) ሕያዋን ድንጋዮች፣ በባዕድ አገር የሚያልፉ እንግዶች (2፥11-12) ናቸው። በጒዟቸውም ከሰዎች ሁሉ ጋር ባላቸው ግንኙነት በክብርና በትሕትና ማለፍ አለባቸው (2፥13—3፥12)።

የአንደኛ ጴጥሮስ መልእክት ዋና ሐሳብ የሚያተኩረው ለክርስቶስ ሲባልና በእርሱ ምሳሌ መሠረት (2፥18-24፤ 3፥9—5፥11) በጽድቅ መገዛትና መሠቃየት በሚለው ላይ ነው። ጴጥሮስ አማኞችን ለሚቀበሉት ጻድቅ ሥቃይ ከእግዚአብሔር የሆነውን ሞገስና ሽልማት እንደሚያገኙ ያረጋግጥላቸዋል። በዚህ ትምህርት ዐውድ ውስጥ ማለትም ለክርስቶስ ሲባል

አማኞች ሊቀበሉት ስለሚገባ ሥቃይ ጴጥሮስ የእርስ በርስ ትስስር ባላቸው ዐበይት ሐሳቦች ይኸውም በድነት፣ በተስፋ፣ በፍቅር፣ በደስታ፣ በእምነት፡ በቅድስና፣ በትሕትና፣ እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በመታዘዝና በመገዛት ላይ አጽንዖት ያደርጋል።

### ልዩ ገጽታ

አንደኛ የጴጥሮስ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) እንደ ዕብራውያን መልእክትና እንደ ዮሐንስ ራእይ ሁሉ መልእክቱ የሚያተኵረው የኢየሱስ ክርስቶስ ከመሆናቸው የተነሣ በአሠቃቂ ስደት ውስጥ በማለፍ ላይ በሚገኙት አማኞች ላይ ነው። (2) ክርስቲያን በክርስቲያንነቱ ኢፍትሐዊ የሆነ ስደትና ሥቃይ ሲደርስበት እንዴት መቋቋም እንዳለበት ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መልእክት ይልቅ ትምህርት ይሰጣል (3፥9—5፥11)። (3) ክርስቲያኖች በዚህ ምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች በመሆናቸው እውነት ላይ ጴጥሮስ አጽንዖት ያደርጋል (1፥1፡ 2፥11)። (4) በብሉይ ኪዳን ላይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጡ አያሌ መጠሪያዎች የአዲስ ኪዳን አማኞች መጠሪያ ሆነዋል (ለምሳሌ 2፥5፡9-10)። (5) ለትርጓሜ እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑት የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ውስጥ፣ "በወህኒ ቤት ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው — በኖኅ ዘመን" (3፥19-20) የሚለውን ክፍል የያዘ ሲሆን፣ ይኸውም ጌታ ኢየሱስ መቼ? የት? እንዴት? እንደ ሰበከላቸው መረዳት አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ ነው።

### አንደኛ ጴጥሮስን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን ማንበብ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ አንደኛ ጴጥሮስን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአምስት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1-21 ❑ 1፥22—2፥25 ❑ 3 ❑ 4 ❑ 5

*ማስታወሻ*

1 የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ጴጥሮስ፤
በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጰዶቅያ፣
በእስያና በቢታንያ ተበትነው በመጻተኝነት
ለሚኖሩ በእግዚአብሔር ምርጦች፤ 2በእግዚአብሔር
አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፣ ኢየሱስ
ክርስቶስን ለመታዘዝ በደሙ ለተረጨቱና
በመንፈስ አማካይነት ለተቀደሱት፤
ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

## ሕያው ስለ ሆነው ተስፋ ለእግዚአብሔር የቀረበ ምስጋና

3የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና
አምላክ ይባረክ፤ እርሱ ከታላቅ ምሕረቱ
የተነሣ በኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣት
ምክንያት ለሕያው ተስፋ በሚሆን አዲስ
ልደት፣ 4እንዲሁም በሰማይ ለማይጠፋ፣
ለማይበላሽና ለማይለወጥ ርስት እንደገና
ወለደን። 5እናንተም በመጨረሻው ዘመን
ሊገለጥ የተዘጋጀው ድነት እስኪመጣ
ድረስ በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር
ኀይል ተጠብቃችኋል። 6አሁን በብዙ
ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት
ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ በዚህ
እጅግ ደስ ይላችኋል። 7እነዚህ ነገሮች
በእናንተ ላይ የደረሱት፣ በእሳት ተፈትኖ
ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ
እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ
መሆኑ እንደተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ
በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን ክብርንና፣
ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው። 8እርሱንም
ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤ አሁን ባታዩትም
በእርሱ ታምናላችሁ፤ መግለጽ በማይቻልና
ክብር በሞላበት ሐሤት ደስ ብሎአችኋል፤
9የእምነታችሁን ፍጻሜ እርሱም የነፍሳችሁን
ድነት እየተቀበላችሁ ነውና።
10ለእናንተ ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት
የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ ድነት ተግተው
በጥንቃቄ ይመረምሩ ነበር፤ 11በእነርሱ
ውስጥ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ ስለ
ክርስቶስ መከራ እንዲሁም ከመከራው በኋላ

1፥1 ማቴ24፥22፤ ሐሥ2፥9፤ 16፥6-7፤ 18፥2፤ ዕብ11፥13፤ ያዕ1፥1፤ 2ጴጥ1፥1
1፥2 ቈላ14፥22፤ ሮሜ1፥7፤ 8፥29፤ 2ተሰ2፥13፤ ዕብ10፥22፤ 12፥24
1፥3 ቈላ13፥21-23፤ ዮሐ1፥13፤ 1ቆሮ15፥20 2ቆሮ1፥3፤ ቲቶ3፥5፤ ዕብ13፥6፤ 1ጴጥ3፥21
1፥4 ሐሥ20፥32፤ ሮሜ8፥17፤ ፊል1፥5፤ 2ጢሞ4፥8፤ 1ጴጥ5፥4
1፥5 1ሳሙ2፥9፤ ዮሐ10፥28፤ ሮሜ8፥18፤ 11፥14
1፥6 ሮሜ5፥2፤ ያዕ1፥2፤ 1ጴጥ4፥12፤ 5፥10
1፥7 ቈላ13፤ ኢዮ23፥10፤ መዝ66፥10፤ ምሳ17፥3፤ ኢሳ48፥10፤ 2ቆሮ4፥17፤ 1ተሰ2፥19፤ 1ጴጥ4፥13
1፥8 ዮሐ20፥29
1፥9 ሮሜ6፥22
1፥10 ቈላ13፤ ማቴ13፥17፤ 26፥24
1፥11 ማቴ26፥24፤ ሐሥ16፥7፤ 2ጴጥ1፥21

**1፥2 እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፤** የእግዚአብሔር አስቀድሞ ማወቅ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ማለትም ለቤተ ክርስቲያን ባለው ዘላለማዊ ፍቅርና ሐሳብ ላይ ያተኮረ ነው (ሮሜ 8፥29 እና ማብ ይመ)። "የተመረጡት" የተባሉት በመንፈስ ቅዱስ የማንጻት ሥራ አማካይነት እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ለመቤዠት ባለው ውሳኔ መሠረት የተመረጡ የእውነተኛ አማኞች ስራዊት ናቸው (በገጽ 1860 ላይ፣ ***"ምርጫና አስቀድሞ መወሰን"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። አማኞች ሁሉ መጠራታቸውንና መመረጣቸውን በናፍቆት እርግጠኛ ለማድረግ በዚሁ ጉዳይ ላይ መሳተፍ አለባቸው (2ጴጥ 1፥5፡10 እና ማብ ይመ)።

**1፥2 በመንፈስ አማካይነት ለተቀደሱት፤** የክርስቲያንን ሕይወት መቀደስ በተመለከተ የተሰጠውን ሐተታ ለመገንዘብ በገጽ 2000 ላይ፥ ***"መቀደስ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥3-4 አዲስ ልደት ... ወለደን፤** በገጽ 1606 ላይ፣ ***"ዳግም ልደት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥5 በእምነት አማካይነት በእግዚአብሔር ኀይል ተጠብቃችኋል፤** ይህ ጥቅስ የአማኞችን ደኅንነት በተመለከተ ሦስት እውነትን ያቀርባል፤ ይህም በተለይ ያን ጊዜ ለነበሩት ሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክቱን ለጻፈላቸው ምእመናን ጠቀሜታ አለው፤ ብዙዎቹ በከባድ ስደት ውስጥ በማለፍ ላይ ነበሩና፡ (1) አማኞች ሕይወታቸውንና በክርስቶስ ያገኙትን ድነት ከሚያጠፋ ከማንኛውም የክፋት ኀይል ሁሉ፣ "በእግዚአብሔር ኀይል" ተጠብቀዋል (2ጢሞ 4፥18፤ ይሁ 1፡24 ከሮሜ 8፥31-39 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) የእግዚአብሔርን ጥበቃ ለማግኘት ከአማኝ የሚጠበቀው፣ "እምነት" ብቻ ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ ***"እምነትና ጸጋ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የእግዚአብሔር ጥበቃ ለእኛ በዘፈቀደ የሚከናወን አይደለም፤ አማኞች፣ "በእምነት" ብቻ እንደ ዳኑ ሁሉ (ኤፌ 2፥8)፣ በእግዚአብሔር ኀይል የሚጠበቁትም በእምነት ብቻ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን የማያቋርጥ ጥበቃ እናገኝ ዘንድ ምንጊዜም ሕያው በሆነ እምነት ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርጎ ማመን ከእኛ የሚጠበቅ ኀላፊነት ነው (ቍ 9፤ ዮሐ 15፥4፡6፤ ቈላ 1፥23፤ 2ጢሞ 3፥14-15፤ 4፥7፤ ራእ 3፥8፡10)።

(3) በክርስቲያኑ እምነት አማካይነት የእግዚአብሔር ጥበቃ የመጨረሻ ግብ "ድነት" ነው። ከዚህ ላይ ድነት የሚያመለክተው የድነት የወደፊት ልኬታ የቱን ያህል ከፍ ያለና የጠለቀ መሆኑን ነው (ከሮሜ 1፥16 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይኸውም በመንግሥተ ሰማይ ርስትንና፣ "የነፍሳችሁን ድነት" (ቍ 9) የተባለውን ማግኘት ነው።

**1፥7 እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ፤** ሥቃይን የመቀበሉ ጉዳይ ዋና ሐሳብ በመሆን በዚህ መልእክት ውስጥ ከዳር እስከ ዳር አጽንዖት ተሰጥቶታል (2፥19-23፤ 3፥14-17፤ 4፥1-4፡12-19፤ 5፥10)። ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስብን ሐሤት ማድረግ አለብን (ቍ 6)፤ ምክንያቱም በፈተና ውስጥ ሆነን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በታማኝነት መጽናታችን፣ እምነታችንን ያጠራዋል፤ በውጤቱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ ውዳሴን፥ ክብርንና ሞገስን ለእርሱና ለእኛ ያስገኛል። ጌታ በፈተና ውስጥ ጸንተን መገኘታችንንና በክርስቶስ ላይ ያለንን እምነት ለዘላለም ውድ ነገር አድርጎ ይቈጥረዋል።

**1፥8 እርሱንም ሳታዩት ትወዱታላችሁ፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከትንሣኤው በኋላ ካዩትና ከሰሙት ክርስቲያኖች እምነት ይልቅ፥ ዛሬ ያሉትን ክርስቲያኖች እምነት እግዚአብሔር የላቀ አድርጎ ያየዋል። ዛሬ አማኞች ጌታ ኢየሱስን በዐይነ ሥጋ ከቶ ያላዩት ቢሆኑም እንኳ፣ ይወዱታል፤ በእርሱ ያምናሉ፤ ጌታ ኢየሱስ እንደ ተናገረውም፣ "ሳያዩ የሚያምኑ" (ዮሐ 20፥29) ልዩ በረከትን ያገኛሉ። በእምነት ስንኖር የእግዚአብሔር ስጦታ ሆኖ ደስታ ተሰጥቶናል (መዝ 16፥11፥ ዮሐ 16፥24፤ ሮሜ 15፥13፤ ገላ 5፥22)።

**1፥11 በእነርሱ ውስጥ የነበረው የክርስቶስ መንፈስ፤** እምነታችን የተመሠረተው በአዲስ ኪዳን ላይ ባለው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሳይሆን፣ በብሉይ ኪዳን ላይ ባለውም የእግዚአብሔር ቃል ጭምር ነው። መንፈስ ቅዱስ በነቢያት በኩል ስለ ክርስቶስ ሥቃይና

ስለሚሆነው ክብር አስቀድሞ በመናገር
ያመለከታቸው ጊዜ መቼና እንዴት
እንደሚፈጸም ይመረምሩ ነበር። 12አሁን
ከሰማይ በተላከ መንፈስ ቅዱስ ወንጌልን
ባበሠሩላችሁ ሰዎች የነገሯችሁን ነገር
ባወሩላችሁ ጊዜ እናንተን እንጂ ራሳቸውን
እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው። መላእክትም
እንኳ ሳይቀሩ እነዚህን ነገሮች ይመኛሉ።

## በቅድስና መኖር

13ስለዚህ ልባችሁን አዘጋጁ፤ ራሳችሁንም
ግዙ፤ ተስፋችሁን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ
ለእናንተ በሚሰጠው ጸጋ ላይ ሙሉ በሙሉ
አድርጉ። 14ታዛዦች ልጆች እንደ መሆናችሁ
መጠን ቀድሞ ባለማወቅ ትኖሩበት
የነበረውን ክፉ ምኞት አትከተሉ። 15ነገር
ግን የጠራችሁ እርሱ ቅዱስ እንደ ሆነ
እናንተም በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ 2ጴጥ
16ምክንያቱም "እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም 1፥3-
ቅዱሳን ሁኑ" ተብሎ ተጽፎአል። 11
17ለሰው ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ
የሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ
የምትጠሩት ከሆነ፣ በዚህ ምድር በእንግድነት
ስትኖሩ በፍርሀት ኑሩ። 18ከቀድሞ
አባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከንቱ ከሆነ
ሕይወት የተዋጀችሁት በሚጠፋ ነገር፣ በብር
ወይም በወርቅ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ፤
19ነገር ግን እናንተ የተዋጃችሁት ነውርና
እንከን እንደ ሌለበት በግ ደም፣ በክርስቶስ
ክቡር ደም ነው። 20እርሱ አስቀድሞ
የታወቀው ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሲሆን
አሁን ግን በመጨረሻው ዘመን ስለ እናንተ
ተገለጠ። 21በእርሱም አማካይነት፣ ከሞት
ባስነሣውና ክብርን በሰጠው በእግዚአብሔር
ታምናላችሁ፤ ስለዚህ እምነታችሁና
ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ላይ ነው።
22እንግዲህ ለእውነት በመታዘዝ
ነፍሳችሁን ስላነጻችሁ፣ ለወንድሞቻችሁ
ቅን ፍቅር ይኑራችሁ፤ እርስ በርሳችሁም
አጥብቃችሁ ከልብ ተዋደዱ። 23ዳግመኛ
የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር ሳይሆን
ሕያው በሆነና ጸንቶ በሚኖር፣ በእግዚአብሔር
ቃል አማካይነት ከማይጠፋ ዘር ነው።
24ምክንያቱም መጽሐፍ እንደሚል፣
"ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደ ሣር ነው፤
ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው።
ሣሩ ይጠወልጋል፤ አበባውም
ይረግፋል፤
25የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ
ይኖራል።"

1፥12 ቍ25፤ ሉቃ24፥49፤ ሮሜ4፥24
1፥13 ቍ3፡7፡10፡21፤ ሐሥ24፥25፤ 1ቆሮ1፥7፤ ዕብ3፥6
1፥14 ቍ2፡22፤ ሮሜ12፥2፤ ኤፌ4፥18
1፥15 ኢሳ35፥8፤ 1ተሰ4፥7፤ 1ዮሐ3፥3
1፥16 ዘሌ11፥44፡45፤ 19፥2፤ 20፥7
1፥17 ማቴ6፥9፤ 16፥27፤ ሐሥ10፥34፤ ዕብ11፥13፤ 12፥28
1፥18 ማቴ20፥28፤ 1ቆሮ6፥20፤ ገላ4፥3
1፥19 ዘጸ12፥5፤ 1ዮሐ1፥29፤ ሮሜ3፥25
1፥20 ማቴ25፥34፤ ኤፌ1፥4፤ ዕብ9፥26
1፥21 ቍ3፡13፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ4፥24፤ ፊል2፥7-9፤ ዕብ2፥9፤ ዕብ3፥6
1፥22 ቍ2፥14፤ ዮሐ13፥34፤ ሮሜ12፥10፤ ያዕ4፥8
1፥23 ቍ3፤ ዮሐ1፥13፤ ዕብ4፥12
1፥25 ኢሳ40፥6-8፤ ያዕ1፥10፡11

*1፥22 አንዳንድ የጥናት ቅጆች ከንጹሕ ልብ ይላሉ።*

ከሥቃዩ በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ ተናገረ (ዘፍ 49፥10፤ መዝ 22፤ ኢሳ 52፥13—53፥12፤ ዳን 2፥44፤ ዘካ 9፥9-10፤ 13፥7 ይመ፤ ከሉቃ 24፥26-27 ጋር ያነጻጽሩ፤ 2ጴጥ 1፥21 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 552 ላይ፣ "ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። መንፈስ ቅዱስ፣ "የክርስቶስ መንፈስ" ተብሎአል፤ ምክንያቱም በነቢያት በኩል ስለ ክርስቶስ ተናግሮአል፤ የተላከውም ከክርስቶስ ነው (ቍ 11-12 ይመ፤ ከዮሐ 16፥7፤ 20፥22፤ ከሐሥ 2፥33 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፥12 መንፈስ ቅዱስ ወንጌልን ባበሠሩላችሁ፤** ለብሉይ ኪዳን ነቢያት እስትንፋሰ እግዚአብሔርን የሰጠ መንፈስ ቅዱስ (ቍ 11)፣ ለወንጌል እውነትም ይኸው መንፈስ እስትንፋሰ እግዚአብሔርን ሰጥቶአል፤ ስለዚህ መልእክቱ የመነጨው ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። በጰንጠቆስጤ ቀን ለወንጌል እውነት እስትንፋሰ እግዚአብሔርን የሰጠ መንፈስ፣ ለሁሉም አማኞች ወንጌልን ያውጁ ዘንድ ኀይልን ይሰጥ ጀመር (ሐሥ 1፥8፤ 2፥4)።

**1፥14 አትከተሉ፤** ሮሜ 12፥2 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥16 ቅዱሳን ሁኑ፤** እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፤ ቅድስና የእግዚአብሔር ባሕርይ እንደ ሆነ ሁሉ የሕዝቡ ባሕርይ እንዲሆንም ያስፈልጋል። ቅድስና ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለው ከዓለም መንገድ መለየትንና ለፍቅር፣ ለአገልግሎትና ለእግዚአብሔር አምልኮ ሲባል ተለይቶ መኖርን አካትቶ ይገኛል (ዘሌ 11፥44 እና ማብ ይመ)። በክርስቶስ ሆነን የምመረጣችን ዐላማና ዕቅድ ቅድስና ነው (1፥4)፤ ይህም እርሱን እያስደሰቱ በመኖር (ሮሜ 12፥1፤ ኤፌ 1፥4፤ 2፥10፤ 1ዮሐ 3፥2-3 ይመ፤ ዕብ 12፥14 እና ማብ ይመ)፤ እግዚአብሔርን መምሰልና ሕይወትን ለእርሱ ክብር አሳልፎ መስጠት ማለት ነው። የሚፈጸመውም ነፍሳችንን ከኀጢአት በማያነጻው፣ በክርስቶስ አምሳል በሚያድሰን፣ በቃሉ መሠረት እግዚአብሔርን እንድንታዘዘው ጸጋውን በሚሰጠን በእግዚአብሔር መንፈስ ነው (ገላ 5፥16፡22-23፡25፤ ቈላ 3፥10፤ ቲቶ 3፥5፤ 2ጴጥ 1፥9)። ቅድስና በማንኛውም አማኝ ሕይወት ውስጥ መታየት ያለበት መሆኑን በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1962 ላይ፣ "መቀደስ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥17 የሚፈርደውን፤** በገጽ 1822 ላይ፣ "*በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥17 በፍርሀት ኑሩ፤** ሐሥ 5፥11 እና ማብራሪያውን፤ 9፥31 እና ማብራሪያውን፤ ሮሜ 3፥18 እና ማብራሪያውን፤ ፊል 2፥12 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥18 የተዋጃችሁት፤** በገጽ 1735 ላይ፣ "*ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥19 በክርስቶስ ክቡር ደም፤** መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን መሥዋዕታዊ ሞት የአማኙን መዋጀት የሚያስገኝ መሆኑን ግልጽ አድርጎ ያሳያል፤ ይኸውም ከኀጢአት ባርነት ነጻ መውጣት ማለት ነው (ከኤፌ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ፤ ዕብ 9፥14 እና ማብ ይመ)።

**1፥22 እርስ በርሳችሁም አጥብቃችሁ ከልብ ተዋደዱ፤** ዮሐ 13፥34-35 እና ማብራሪያውን፤ ሮሜ 12፥10 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥25 የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤** ጴጥሮስ ኢሳይያስ 40፥6-8ን ሲጠቅስ የሚያመለክተው እንደ ሬሳ እንደ ምድር የሰው ክብርና የተገኘው ቅርስ ሁሉ (እንደ ባህል፣ ሳይንስና ፍልስፍና ያለው) እንደሚገኝና እንደሚጠፋም ነው (ከመዝ 90፥5-10፤ ከያዕ 4፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ የእግዚአብሔር

# መቀደስ

*1ጴጥ 1፥2 "እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ ካወቃቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመታዘዝ በደሙ ለተረጩትና በመንፈስ ለአማካይነት ለተቀደሱት፤ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።"*

መቀደስ (በግሪክ፣ ዩ.ሀጂ.ያስምስጶ) ማለት ብፁዕ ማድረግ፣ ንጹሕ በማድረግ ለይቶ ማስቀመጥ፣ ከዓለም መለየት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዲኖረንና በደስታ እንድናገለግለው ከኀጢአት መለየት ማለት ነው (በገጽ 1826 ላይ፣ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(1) "ይቀድስ" (ከ1ተሰ 5፥23 ጋር ያነጻጽሩ) ከሚለው ቃል በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የመቀደስ መለኪያ በሚከተሉት አገላለጾች ተመልክቶአል፦ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤" (ማቴ 22፥37)፣ "ነቀፋ የሌለባችሁና ቅዱሳን ሆናችሁ" (1ተሰ 3፥13)፣ "ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው" (2ቆሮ 7፥1)፣ "ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው" (1ጢሞ 1፥5)፣ "ንጹሓንና ነቀፋ የሌለባችሁ" (ፊል 1፥10)፣ "ከኀጢአት ነጻ ወጥታችሁ" (ሮሜ 6፥18)፣ "ለኀጢአት ሞተናል" (ሮሜ 6፥2)፤ "ወደ ቅድስና ለሚወስደው ጽድቅ ባሪያ አድርጋችሁ" (ሮሜ 6፥19)፣ "ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና" (1ዮሐ 3፥22) እንዲሁም "ዓለምን ያሸንፋል" (1ዮሐ 5፥4)። እንደነዚህ ያሉት አገላለጾች በክርስቶስ እውን በሆነው ድነት አካማይነት የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ያመለክታሉ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እውን ካደረገው ድነት የተነሣ መንፈስ ቅዱስ ከኀጢአት እስራትና ኀይል ነጻ ያወጣናል (ሮሜ 6፥1-11)፤ አሁን ካለው ከዚህ ዓለም ኀጢአተኛ ተግባር ይለየናል፤ በክርስቶስ አምሳል ተፈጥሯችንን ያድሳል፤ በእኛ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ እውን ያደርጋል፤ ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን በመስጠት ቅዱስና አሸናፊ የሆነ ሕይወት እንድንኖር ያደርገናል (ዮሐ 17፥15-19፡23፤ ሮሜ 6፥5፡13፡16፡19፤ 12፥1፤ ገላ 5፥16፡22-23 ይመ፤ 2ቆሮ 5፥17 እና ማብ ይመ)።

(2) እነዚህ አባባሎች የሚያመለክቱት ሙሉውን ፍጽምና ሳይሆን፣ በንጽሕና በመታዘዝና በነውር አልባነት የሚገለጸውን ነቀፋ የማይገኝበትን ባሕርይ ማለትም ሥነ ምግባራዊውን ጽድቅ ነው (ፊል 2፥14-15፤ ቈላ 1፥22፤ 1ተሰ 2፥10 ይመ፤ ከሉቃ 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ጸጋ አማካይነት ከክርስቶስ ጋር ሞተዋል፤ ከኀጢአት ኀይልና ባርነትም ነጻ ወጥተዋል (ሮሜ 6፥18)፤ ስለዚህ ኀጢአት ይሠሩ ዘንድ አይገባም፤ መሥራትም የለባቸውም፤ ይልቁንስ በአዳኛቸው በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወሳኝ ድልን ማግኘት ይችላሉ። ከኀጢአት ፈተናና ኀጢአትን ከመሥራት ዝንባሌ ሙሉ በሙሉ ነጻ የምንሆንበት ስፍራ በዚህ ምድር ላይ ፈጽሞ ባይገኝም እንኳ፣ በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ኀጢአትን ከመሥራት መታቀብ እንችላለን (1ዮሐ 2፥1፤ 3፥6)።

(3) በብሉይ ኪዳን መቀደስ ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር፤ በዙሪያቸው ከነበሩት አሕዛብ የአኗኗር ዘይቤ ተለይተው ቅዱስ ሆነው ወይም የተቀደሰ ሕይወትን ገንዘብ አድርገው መኖር ነበረባቸው (ዘፀ 19፥6 እና ማብ፤ ዘሌ 11፥44 እና ማብ፤ 19፥2 እና ማብ፤ 2ዜና 29፥5 እና ማብ ይመ)። እንደዚሁም በክርስቶስ ያሉ አማኞች ቅድስና ይታይባቸው ዘንድ ግድ ነው። "ያለ ቅድስና ማንም ጌታን ማየት" እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዕብ 12፥14)።

(4) የእግዚአብሔር ልጆች መቀደስን የሚያገኙት በእምነት ነው (ሐሥ 26፥18)፤ ይኸውም ከክርስቶስ ጋር በሞቱና በትንሣኤው በመተባበር (ዮሐ 15፥4-10፤ ሮሜ 6፥1-11፤ 1ቆሮ 1፥30)፣ በክርስቶስ ደም (1ዮሐ 1፥7-9)፣ በቃሉ (ዮሐ 17፥17)፣ በራሱ በመንፈስ ቅዱስ በሚከናወነው አዲስ ፍጥረት በመሆንና በመቀደስ ሥራ ነው (ኤር 31፥31-34፤ ሮሜ 8፥13፤ 1ቆሮ 6፥11፤ ፊል 2፥12-13፤ 2ተሰ 2፥2፥13)።

(5) መቀደስ የእግዚአብሔርና የሕዝቡ የሁለቱም ሥራ ነው (ፊል 2፥12-13)። አማኞች በመቀደስ ረገድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይፈጽሙ ዘንድ፣ ክፋትን ከመሥራት በመታቀብ (ሮሜ 6፥1-2)፤ "ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ" ራሳቸውን በማንጻት (2ቆሮ 7፥1 ይመ፤ ከሮሜ 6፥12፤ ከገላ 5፥16-25 ጋር ያነጻጽሩ) እንደዚሁም በዓለም ከመበከል ራሳቸውን በመጠበቅ (ያዕ 1፥27 ይመ፤ ከሮሜ 6፥13፡19፤ 8፥13፤ 12፥1-2፤ 13፥14፤ ከኤፌ 4፥31፤ 5፥18፤ ከቈላ 3፥5፡10፤ ከዕብ 6፥1፤ ከያዕ 4፥8 ጋር ያነጻጽሩ) በመንፈስ ቅዱስ የማንጻት ሥራ መተባበር አለባቸው።

(6) እውነተኛ መቀደስ አማኞች የሚከተሉትን እንዲፈጽሙ ይፈልጋል፤ ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዲኖራቸው (ዮሐ 15፥4 እና ማብ)፣ ከክርስቲያኖች ጋር ኅብረት እንዲኖራቸው (ኤፌ 4፥15-16)፣ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለጸሎት እንዲሰጡ (ማቴ 6፥5-13፤ ቈላ 4፥2) የእግዚአብሔርን ቃል እንዲታዘዙ (ዮሐ 17፥17)፣ የእግዚአብሔርን ሀልዎትና እንክብካቤ ልብ እንዲሉ (ማቴ 6፥25-34)፣ ጽድቅን እንዲወዱና ክፋትን እንዲጠሉ (ዕብ 1፥9)፣ ኃጢአትን እንዲገድሉ (ሮሜ 6)፣ ለእግዚአብሔር ቅጣት ራሳቸውን እንዲያስገዙ (ዕብ 12፥5-11)፣ እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንዲቀጥሉና በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ (ሮሜ 8፥1፤ ኤፌ 5፥18)።

(7) በአዲስ ኪዳን ላይ መቀደስ ከኃጢአት ቀስ በቀስ ነጻ የሚወጣበት አዝጋሚ ሂደት ሆኖ አልታየም። ይልቁንስ አማኙ ከሰይጣን እስራት በጸጋ ነጻ በመውጣት ለእግዚአብሔር ይኖር ዘንድ ከኃጢአት ግልጽ የሆነ መለየትን የሚያሳይበት ቊርጥ ያለ ክንውን ተደርጎ ቀርቦአል (ሮሜ 6፥18፤ 2ቆሮ 5፥17፤ ኤፌ 2፥4-6፤ ቈላ 3፥1-3)። ይሁን እንጂ ቀደም ሲል የተነገረው እንደ ተጠበቀ ሆኖ መቀደስ የዕድሜ ልክ ሂደት ሆኖ ተገልጾአል፤ በመቀደስ የሥጋን ክፉ ሥራ እየገደልን እንኳዛለን (ሮሜ 8፥17)፤ በዚህም ክርስቶስን ወደ መምሰል እያደር እናድጋለን (2ቆሮ 3፥18)፤ በጸጋም ረገድ እናድጋለን (2ጴጥ 3፥18)። ለእግዚአብሔርና ለሰዎች የላቀ ፍቅር እናሳያለን (ማቴ 22፥37-39፤ 1ዮሐ 4፥7-8፡11፡20-21)።

(8) የመጀመሪያ ድነት እውን ከሆነ በኋላ መቀደስ ተለይቶ የሚታወቅ የገጠመኝ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል፤ አማኞች የእግዚአብሔርን ቅድስና በተመለከተ ጉልሕ የሆነ መገለጥ ሊቀበሉ ይችላሉ፤ ከኃጢአትና ከዓለምም ራሳቸውን በላቀ መንገድ ይለዩ ዘንድ እግዚአብሔር የሚጠራቸው መሆኑንና ወደ እርሱም ቀርበው ይመላለሱ ዘንድ እንደሚገባቸው ግንዛቤን ሊያገኙ ይችላሉ (2ቆሮ 6፥16-18)። ከዚህ ግንዛቤ የተነሣም አማኞች ራሳቸውን ሕያው መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር ያቀርባሉ፤ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ ሕይወት ይኖሩ ዘንድም ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋን፣ ንጽሕናን፣ ኀይልንና ድልን ያገኛሉ (ሮሜ 6፥19-22፤ 12፥1-2)።

የተሰበከላችሁም የምሥራች ቃል ይህ
ነው።

2 [2]እንግዲህ ክፋትን ሁሉ፣ ማታለልን
ሁሉ፣ ግብዝነትን፣ ቅናትንና ሐሜትን
ሁሉ አስወግዱ፤ [2]በድነታችሁ እንድታድጉ፣
አዲስ እንደ ተወለዱ ሕፃናት ንጹሑን
መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤ [3]ጌታ መልካም
መሆኑን ቀምሳችኋልና። ሕያው ድንጋይና
የተመረጠ ሕዝብ

## ሕያው ድንጋይና የተመረጠ ሕዝብ

[4]በሰው ዘንድ ወደ ተናቀው፣ በእግዚአብሔር
ዘንድ ግን ወደ ተመረጠውና ክቡር ወደ
ሆነው ወደዚህ ሕያው ድንጋይ እየቀረባችሁ፣
[5]እናንተ ደግሞ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካ
ይነት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ
መሥዋዕት ታቀርቡ ዘንድ፣ ቅዱሳን ካህናት
ለመሆን እንደ ሕያዋን ድንጋዮች መንፈሳዊ
ቤት ለመሆን ትሠራላችሁ። [6]ምክንያቱም
በመጽሐፍ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፤
"እነሆ፤ የተመረጠና ክቡር የማእዘን
ድንጋይ፣ በጽዮን አኖራለሁ፤
በእርሱም የሚያምን፣ ከቶ አያፍርም።"

[7]እንግዲህ ለእናንተ ለምታምኑት ይህ
ድንጋይ ክቡር ነው፤ ለማያምኑት ግን፣
"ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ[a] ሆነ።"
[8]ደግሞም፣ "ሰዎችን የሚያሰናክል፣
የሚጥላቸውም ዐለት ሆነ።"
የሚሰናከሉት ቃሉን ባለመታዘዛቸው
ነው፤ የተመደቡት ለዚህ ነውና።
[9]እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ
ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ
ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣
የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ራእ
ለራሱ የለየችሁ ሕዝብ ናችሁ። [10]ቀድሞ 5፡9
የእርሱ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን 14
የእግዚአብሔር ሕዝብ ሆናችኋል፤ ቀድሞ
ምሕረትን አላገኛችሁም ነበር፤ አሁን ግን
ምሕረትን አግኝታችኋል።
[11]ወዳጆች ሆይ፤ በዚህ ዓለም እንግዶችና

2፥1 ኤፌ4፥22፤ ያዕ4፥11 2፥2 1ቆሮ3፥2፤ ኤፌ4፥15፡16፤ ዕብ5፥12፡13 2፥3 መዝ34፥8፤ ዕብ6፥5 2፥4 ቍ7፤ ኢሳ42፥1 2፥5 ቍ9፤ ዘፀ19፥6፤ ምሳ9፥1፤ ኢሳ61፥6፤ 1ቆሮ3፥9፤ ኤፌ2፥20-22፤ ፊል4፥18፤ 1ጢሞ3፥15፤ ዕብ13፥15፤ ራእ1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6 2፥6 ኢሳ28፥16፤ ሮሜ9፥32፡33፤ 10፥11፤ ኤፌ2፥20 2፥7 ቍ4፤ መዝ118፥22፤ ሐሥ4፥11፤ 2ቆሮ2፥16 2፥8 ኢሳ8፥14፤ ሉቃ2፥34፤ ሮሜ9፥22 2፥9 ቍ5፤ ዘፀ19፥6፤ ዘዳ7፥6፤ 10፥15፤ 1ሳሙ12፥22፤ ኢሳ62፥12፤ ሐሥ26፥18፤ ቲቶ2፥14 2፥10 ሆሴ1፥9፡10፤ 2፥23፤ ሮሜ9፥25፡26 2፥11 ሮሜ13፥14፤ 1ቆሮ10፥14፤ ገላ5፥16፤ ዕብ11፥13፤ ያዕ4፥1

[a]2፥7 ወይም የማእዘን ድንጋይ

ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል። ከሰው ጥረት ሁሉና ግንኙ ከሚታየው የዓለም መንፈስ አንጻር መጽሐፍ ቅዱስ ከሚመዘን ይልቅ፣ እነዚህ ሁለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ አኳያ መመዘን አለባቸው። ከምሁራዊ አስተሳሰብ ጋር ለማስማማት ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል እቃልለው የሚያቀርቡና የትውልዳቸውን ሚዛን የሚበርዙ ሁሉ፣ "ሕያው" የሆነውንና "ጸንቶ" የሚኖረውን የእግዚአብሔር ቃል ይክዳሉ (ቍ 23)።

**2፥2 ንጹሑን መንፈሳዊ ወተት ተመኙ፤** ዳግም የተወለድን የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን (1ቆሮ 6፥19፤ ገላ 4፥6)፣ ንጹሑን የእግዚአብሔርን ቃል ወተት መመኘት አለብን (1፥23-25)። በመንፈስ የምናደርግ ለመሆናችን አስተማማኝ ምልክቱ ሕያውና ዘላለማዊ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ለመመገብ ጥልቅ ናፍቆት ያለን መሆኑ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ራብና ጥማት ሲጠፋ መንቃት አለብን፤ ይህ ናፍቆት በተሳሳተ ሁኔታ (ቍ 1) እንዲሁም፣ "በምድራዊ ሕይወት ጭንቀት፣ በባለጠግነትና ተድላ ደስታ" (ሉቃ 8፥14 ይመ፡ ማቴ 5፥6 እና ማብ ይመ፡ 1ቆሮ 15፥2 እና ማብ ይመ) ሊጠፋ ይችላል።

**2፥5 ቅዱሳን ካህናት፤** በብሉይ ኪዳን ክህነት የብቃት መለኪያውን ለሚያሟሉ ጥቂት ሰዎች ብቻ የተሰጠ ነበር። ጉልሕ የሆነው ተግባራቸው ሕዝቡን በመወከል መሥዋዕት ማቅረብና ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መነጋገር ነበር (ዘፀ 28፥1፤ 2ዜና 29፥11)። አሁን ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በእግዚአብሔር ፊት ካህን ሆኖአል (ራእ 1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6)። አማኞች ሁሉ ካህናት ናቸው ማለት ቀጥሎ ያሉትን መናገር ነው፡ (1) አማኞች ሁሉ በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በቀጥታ መቅረብ ይችላሉ (3፥18፡ ዮሐ 14፥6፤ ኤፌ 2፥18)።

(2) አማኞች ሁሉ ቅዱስ ሕይወት ይኖሩ ዘንድ ግዴታ አለባቸው (ቍ 5፡9፤ 1፥14-17)።

(3) አማኞች ሁሉ ለእግዚአብሔር፡ "መንፈሳዊ መሥዋዕት" ማቅረብ አለባቸው፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡ (ሀ) እግዚአብሔር በመታዘዝ፣ ከዓለም ጋር ግን ባለመስማማት መኖርን (ሮሜ 12፥1-2)፤ (ለ) ወደ እግዚአብሔር መጸለይንና ለእግዚአብሔር ውዳሴ ማቅረብን (መዝ 50፥14፤ ዕብ 13፥15 ይመ፤ በገጽ 802 ላይ፣ "*ምስጋና*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡ (ሐ) በሙሉ ልብና ፈቃደኛ በሆነ አእምሮ ማገልገልን (1ዜና 28፥9፤ ኤፌ 5፥1-2፤ ፊል 2፥17)፡ (መ) መልካም ሥራን መፈጸምን (ዕብ 13፥16)፤ (ሠ) ከሀብታችን መስጠትን (ሮሜ 12፥13፤ ፊል 4፥18) እና (ረ) ሰውነታችንን የጽድቅ መሣሪያ በማድረግ ለእግዚአብሔር ማቅረብን (ሮሜ 6፥13፡19)።

(4) አማኞች ሁሉ ለእርስ በእርስና ለሰዎች ሁሉ ማማለድና መጸለይ አለባቸው (ቈላ 4፥12፤ 1ጢሞ 2፥1፤ ራእ 8፥3 ይመ፤ በገጽ 1280 ላይ፡ "*የምልጃ ጸሎት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(5) አማኞች ሁሉ ቃሉን መስበክ ለስኬታማነቱም መጸለይ አለባቸው (ቍ 9፡ 3፥15፤ ሐሥ 4፥31፤ 1ቆሮ 14፥26፤ 2ተሰ 3፥1)።

(6) አማኞች ሁሉ የጥምቀትንና የጌታ ራትን ሥርዐት ሊፈጽሙ ይችላሉ (ማቴ 28፥19፤ ሉቃ 22፥19)።

**2፥9 ቅዱስ ሕዝብ፤** አማኞች ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ለመሆንና (ከሐሥ 20፥28፡ ከቲቶ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ) የድነትን ወንጌል ለእግዚአብሔር ክብርና ውዳሴ ለማወጅ (ዘፀ 19፥6 እና ማብ ይመ፤ ኢሳ 42፥1 እና ማብ ይመ) ከዓለም ተለይተዋል።

**2፥11 እንግዶችና መጻተኞች፤** የእግዚአብሔር የራሱ ርስት የመሆናችን አዲሱ ስፍራችን በዚህ ዓለም ላይ መጻተኞች እንሆን ዘንድ ከዚህ ዓለም ሰዎች ይለየናል። አሁን እየኖርን ያለነው የራሳችን ባልሆነ አገር ነው፤ እውነተኛው ዜግነታችን ግን ከክርስቶስ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ውስጥ ነው (ከፊል 3፥20፡ ከዕብ 11፥9-16 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ምድር ላይ ባዕዳን ነንና ነፍሳችንን ለማጥፋት በሚሻ በዚህ ዓለም ክፉ ደስታ ውስጥ ከመሳተፍ መታቀብ አለብን (በገጽ 1853 ላይ፣ "*የኃጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣
ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ
እለምናችኋለሁ። 12ምንም እንኳ ክፉ እንደ
ምትሠሩ አድርገው ቢያሟችሁም ለፍርድ
በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን ሥራችሁን
1ዮሐ 2፥15-17 ዐይተው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ በአሕዛብ
መካከል በመልካም ሕይወት ኑሩ።

## ለአለቆችና ለጌቶች መታዘዝ

13ስለ ጌታ ብላችሁ ለምድራዊ ባለ
ሥልጣን ሁሉ ተገዙ፤ የበላይ ባለ ሥልጣን
ስለ ሆነ ለንጉሥ ቢሆን፣ 14ወይም ክፉ
አድራጊዎችን ለመቅጣት፣ በጎ አድራጊዎችን
ለማመስገን እርሱ ለሾማቸው ገዦች ታዘዙ፤
15ምክንያቱም፣ መልካም በማድረግ የአላ
ዋቂዎችን ከንቱ ንግግር ዝም እንድታሰኙ
የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። 16እንደ እግዚአብሔር
አገልጋዮች ሆናችሁ በነጻነት ኑሩ እንጂ
ነጻነታችሁን የክፋት መሸፈኛ አታድርጉት።
17ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት ስጡ፤
ወንድሞችን ውደዱ፤ እግዚአብሔርን ፍሩ፤
ንጉሥን አክብሩ።

18እናንተ አገልጋዮች ሆይ፤ ለደጎችና ለገ
ሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም
በፍጹም አክብሮት ታዘዙ። 19ስለ እግዚአብሔር
ሲል የግፍ መከራን የሚቀበል ሰው ምስጋናን
ያገኛል። 20ክፉ ሥራ ሠርታችሁ ብትቀጡና
ብትታገሡ ምን ምስጋና ይኖራችኋል?

2፥12 ማቴ9፥8፡ ፊል2፥15፡ ቲቶ2፥8፡14፡ 1ጴጥ3፥16
2፥13 ሮሜ13፥1፡ ቲቶ3፥1
2፥14 ሮሜ13፥3፡4
2፥15 ቍ12፡ 1ጴጥ3፥17፡ 4፥19
2፥16 ዮሐ8፥32፡ ሮሜ6፥22፡ ገላ5፥13
2፥17 ምሳ24፥21፡ ሮሜ12፥10፡ 13፥7
2፥18 ኤፌ6፥5፡ ያዕ3፥17
2፥19 1ጴጥ3፥14፡17
2፥20 1ጴጥ3፥17
2፥21 ማቴ11፥29፡ 16፥24፡ ሐሥ14፥22፡ ሮሜ8፥28፡ ፊል1፥29፡ 1ጴጥ3፥9፡18፡ 4፥1፡13
2፥22 ኢሳ53፥9፡ 2ቆሮ5፥21
2፥23 መዝ9፥4፡ ኢሳ53፥7፡ ሉቃ23፥46፡ ዕብ12፥3፡ 1ጴጥ3፥9
2፥24 ዘዳ32፥29፡

ነገር ግን መልካም ሥራ ሠርታችሁ
መከራ ብትቀበሉና ብትታገሡ ይህ
በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ያስገኝላችኋል።
21የተጠራችሁትም ለዚሁ ነው፤ ምክንያቱም
ክርስቶስ ስለ እናንተ መከራን የተቀበለው
የእርሱን ፈለግ እንድትከተሉ ምሳሌን
ሊተውላችሁ ነው።
22"እርሱ ኀጢአት አላደረገም፤
በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም።"
23ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤
መከራ ሲደርስበት አልዛተም፤ ነገር ግን
በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ።
24ለኀጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ
ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በእንጨት
መስቀል ላይ ተሸከመ፤ በእርሱ ቍስል
እናንተ ተፈውሳችኋል። 25ቀድሞ እንደ ጠፉ
በጎች ትቅበዘበዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ
ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።

## በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት

3 ሚስቶች ሆይ፤ እናንተም እንደዚሁ
ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ አንዳንድ ለቃሉ
የማይታዘዙ ቢኖሩ፣ ያለ ቃል በሚስቶቻቸው

2፥24 መዝ103፥3፡ ኢሳ53፥4፡5፡11፡ ዕብ9፥28፡ 12፥13፡ ያዕ5፥16 2፥25 ኢዩ10፥12፡ ኢሳ53፥6፡ ዮሐ10፥11
3፥1 1ቆሮ7፥16፡ 9፥19፡ ኤፌ5፥22፡ 1ጴጥ2፥18

**2፥13 ባለሥልጣን ሁሉ ተገዙ፤** ሮሜ 13፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥21 ክርስቶስ ... መከራን የተቀበለው ... ምሳሌን ሊተውላችሁ ነው፤** የማንኛውም አማኝ ከፍተኛ ክብርና መብት ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ሥቃይ መቀበል ነው (ማቴ 5፥10 እና ማብ ይመ)። ሥቃይ በመቀበል አማኞች የክርስቶስንና የሐዋርያትን ምሳሌነት ይከተላሉ (ኢሳ 53፡ ማቴ 16፥21፤ 20፥28፤ ሐሥ 9፥16 እና ማብ ፤ ዕብ 5፥8 ይመ)። (1) ክርስቲያኖች ሥቃይን ለመቀበል ፈቃደኞች መሆን አለባቸው (4፥1፤ 2ቆሮ 11፥23-29)፤ ይኸውም በክርስቶስ ሥቃይ ተካፋዮች እንዲሆኑ ነው (4፥13፤ 2ቆሮ 1፥5፤ ፊል 3፥10)፡ ሥቃይ የአገልግሎታቸው አንድ አካል ሊሆን እንደሚችልም ማስብ አለባቸው (2ቆሮ 4፥10-12 ይመ፤ ከ1ቆሮ 11፥1 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል ሲባል "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ" (4፥19)፤ ስለ ስሙ (ሐሥ 9፥16)፣ "ስለ ወንጌል" (2ጢሞ 1፥8)፣ "ስለ ጽድቅ" (3፥14)፣ ስለ " ... እግዚአብሔር መንግሥት" (2ተሰ 1፥5) ሥቃይን መቀበል ማለት ነው።

(3) ለክርስቶስ ሲሉ መከራን መቀበል ከመንፈሳዊ እድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ (ዕብ 2፥10)፤ የእግዚአብሔርን በረከት ለማግኘት (4፥14) እና ሕይወትን ለሌሎች አገልግሎት ለማዋል (2ቆሮ 4፥10-12) የሚያበቃ መንገድ ነው። በክርስቶስ ሥቃይ ተካፋይ መሆን የክርስቶስ የክብሩ ተካፋይ ለመሆን (ሮሜ 8፥17)፣ ዘላለማዊ የሆነውን ክብር ለማግኘት (ሮሜ 8፥18) በአማኙ ሕይወት አስቀድሞ ይገኝ ዘንድ አስፈላጊ ነው። ይህ ከሆነ ዘንድ መከራን መቀበል ከእግዚአብሔር የመጣ ውድ ስጦታ ነው (ቍ 19፤ ፊል 1፥29)።

(4) ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለወንጌል ለመኖር ሲባል ሥቃይ ውስጥ መግባት እንዲሁ መፈለግ የለበትም፤ ይሁን እንጂ አማኞች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው ከመስጠታቸው የተነሣ፣ በሥቃይ ውስጥ ለማለፍ ፈቃደኞች መሆን አለባቸው።

**2፥24 ኀጢአታችንን ... ተሸከመ፤** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ምትክ ሆኖ ለኀጢአታችን የሚገባውን ቅጣት በመቀበል (ዮሐ 1፥29፤ ዕብ 9፥28፤ 10፥10 ይመ፤ በገጽ 202 ላይ፤ *"የስርየት ቀን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፣ በመስቀል ላይ ኀጢአታችንን ተሸከመ (ከኢሳ 53፥4፡11-12 ጋር ያነጻጽሩ)። የዚህ የምትክነት ሞት ዐላማ ከኀጢአት በደል፣ ኀይልና ተጽዕኖ ፈጽሞ እንድንለይ ነው። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ሆነን ወደ እግዚአብሔር የምንመለስበትንና (ሮሜ 3፥24-26) በፊቱ በጽድቅ ለመኖር ጸጋን የምንቀበልበትን መንገድ በመክፈት በደላችንና የበደላችንን ቅጣት በሞቱ አስወገደ (ሮሜ 6፥2-3፤ 2ቆሮ 5፥15፤ ገላ 2፥20)። ጴጥሮስ ከድነት እንዲሁም ድነት ከሚያስገኘው ጥቅም ሁሉ አኳያ ጕዳዩን በማየት፣ "ተፈውሳችኋል" (ከኢሳ 53፥5፤ ከማቴ 8፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ) የሚለውን ቃል ተጠቅሞበታል።

**3፥1 ለባሎቻችሁ ... ተማርከው ይመለሳሉ፤** ጴጥሮስ አንዲት አማኝ ሴት ያልዳነውን ባሏን እንዴት ማሸነፍ እንዳለባት ለሚስት ትምህርትን ይሰጣል፤ (1) ይህችው ሴት ለባሏ መገዛት አለባት፤ በቤተ ሰብ ውስጥ ባሏ የተሰጠውን የበላይነትም አምና መቀበል አለባት (ኤፌ 5፥22 እና ማብ ይመ)። (2) ገርና ጭምት በሆነ መንፈስ በንጹሕና በክብር ጠባይ ራሷን ማስተዳደር አለባት (ቍ 2-4፤ 1ጢሞ 2፥13፡15 እና ማብ ይመ)። (3) ባሏን በአንደበቷ ለመለወጥ ከመሞከር ይልቅ፣ በጠባይዋ ለመማረክ መጣር ይኖርባታል።

አኗኗር ተማርከው ይመለሳሉ፤ 2ይህም
የሚሆነው ንጹሕና ፍጹም አክብሮት
የተሞላውን ኑሮአችሁን ሲመለከቱ ነው።
3ውበታችሁ በውጫዊ ነገሮች በመሸሞንሞን
ይኸውም ሹሩባ በመሠራት፣ በወርቅ
በማጌጥና በልብስ አይሁን፤ 4ነገር ግን
ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ
የከበረ፣ ገርና ጭምት መንፈስ ያለበት፣
ምንጊዜም የማይጠፋ የውስጥ ሰውነት ውበት
ይሁን። 5ተስፋቸውን በእግዚአብሔር ላይ የጣሉ
የቀድሞ ቅዱሳት ሴቶች ራሳቸውን ያስዋቡት
በዚህ ዐይነት ለባሎቻቸው በመገዛት ነበርና።
6ሣራም አብርሃምን "ጌታዬ" እያለች ትታዘ
ዘው ነበር፣ እናንተም ምንም ሳትፈሩ መል
ካም ብታደርጉ የእርሷ ልጆች ናችሁ።

7ባሎች ሆይ፤ እናንተም ደግሞ
ጸሎታችሁ እንዳይደናቀፍ በኑሮአችሁ
ሁሉ ለሚስቶቻችሁ አስቡላቸው፣ ደካሞች
ስለሆኑና የሕይወትንም በረከት አብረዋችሁ
ስለሚወርሱ አክብሯቸው።

## መልካም በማድረግ መከራን መቀበል

8በመጨረሻም ሁላችሁ በአንድ ሐሳብ
ተስማሙ፤ እርስ በርሳችሁ ተሳሰቡ፤
እንደ ወንድማማቾች ተዋደዱ፤ ርኅሩኆችና
ትሑታን ሁኑ። 9ክፉን በክፉ ወይም ስድብን
በስድብ ፈንታ አትመልሱ፤ በዚህ ፈንታ

3፥3 ኢሳ3፥18-23፤ 1ጢሞ2፥9
3፥4 ሮሜ2፥29፤ 7፥22፤ ኤፌ3፥16
3፥5 እስ2፥15፤ 1ጢሞ5፥5
3፥6 ዘፍ18፥12
3፥7 ኤፌ5፥25-33፤ ቈላ3፥19
3፥8 ሮሜ12፥10፤ 15፥5፤ ኤፌ4፥2፤ 1ጴጥ5፥5
3፥9 ማቴ5፥44፤ ሮሜ8፥28፤ ሮሜ12፥17፤ 1ተሰ5፥15፤ ዕብ6፥14፤ 1ጴጥ2፥21፡23
3፥12 መዝ34፥12-16
3፥13 ቲቶ2፥14
3፥14 ቍ17፤ ኢሳ8፥12፡13፤ 1ጴጥ2፥19፡20፤ 4፥15፡16
3፥15 ፋሳ4፥6፤ ዕብ3፥6

ባርኩ፤ ምክንያቱም እናንተ የተጠራችሁት
እንደነዚህ ያሉትን ነገሮች እያደረጋችሁ
በረከትን ለመውረስ ነው። 10ስለዚህ፣
"ሕይወትን የሚወድ፣
መልካም ቀኖችን ሊያይ የሚፈልግ፣
ምላሱን ከክፉ፣
ከንፈሮቹንም ተንኰል ከመናገር
ይከልክል።
11ከክፉ ይራቅ፤ መልካምንም ያድርግ፤
ሰላምን ይፈልግ፤ ይከተላትም፤
12ምክንያቱም የጌታ ዐይኖች ጻድቃንን
ይመለከታሉና፤
ጆሮቹም ጸሎታቸውን ለመስማት
የተከፈቱ ናቸው፤
የጌታ ፊት ግን በክፉ አድራጊዎች
ላይ ነው።"
13መልካም ነገር ለማድረግ ብትቀኑ
የሚጐዳችሁ ማን ነው? 14ነገር ግን ስለ ጽድቅ
እንኳ መከራ ቢደርስባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤
"ዛቻቸውን አትፍሩ*፤ አትታወኩም።"
15ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ
ቀድሱት።እናንተ ስላላችሁ ተስፋ ምክንያትን
ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁል
ጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን
ሁሉ በትሕትናና በአክብሮት አድርጉት፤ 1ዮሐ 1፥2

*3፥14 ወይም የሚፈሩትን አትፍሩ

**3፥3-4 ውበታችሁ ... የውስጥ ሰውነት ውበት ይሁን፤** የሚያብረቀርቅ ወይም ውድ የሆነ ጌጣጌጥ እግዚአብሔር በክርስቲያን ሚስት ላይ እንዲታይ ከሚፈልገው የጭምትነት ጠባይ ጋር ተቃራኒ ነው (1ጢሞ 2፥9 እና ማብ ይመ)። (1) እግዚአብሔር በክርስቲያን ሚስት ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ አለው ብሎ የሚቈጥረው ገርና ጭምት የሆነውን ጠባይዋን ነው (ከማቴ 11፥29፤ 21፥5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይህም ባለቤቷና ቤተሰቧ እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ያለውን ዐላማ ፍጻሜ ላይ ያደርሱ ዘንድ፣ እነርሱን በማገዝ ጌታን ለማክበር በምታደርገው ጥረት ይገለጣል። (ሀ) «ገር» የሚለው ቅጽል የሚያመለክተው ቸርነት የሚታይበትን መገዛትና ለሌሎችም መጨነቅን አክሎ የያዘውን ታይታ አልባ ጠባይን ነው (ከማቴ 5፥5፤ ከ2ቆሮ 10፥1፤ ከገላ 5፥23 ጋር ያነጻጸሩ)። (ለ) «ጭምት» የሚለው ቅጽል ደግሞ የሚያመለክተው ልፍለፋ የሌለበትንና ሁከት የማይፈጥረውን ጠባይ ነው። በሌላ አገላለጽ እግዚአብሔር እውነተኛ ውበት የሚለው ጌጥ ያለበትን ውበት ሳይሆን መልካም ጠባይ የሚገኝበትን ነው።

(2) ክርስቲያን ሚስቶች በዓለማዊነት፣ በዘመን አመጣሽና ስሜት ቀስቃሽ አለባበስና አጊያጊያጥ፣ በእኔነት መንፈስና በሴሰኝነት በተያዘ፣ የቤትንና የቤተሰብን ፋይዳ እየናቀ በሚገዛ ዓለም ውስጥ ሲኖሩ፣ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ ታማኝ መሆን አለባቸው።

**3፥7 ባሎች ሆይ፤** ባሎች ሚስቶቻቸውን በተመለከተ መፈጸም ስላለባቸው ጕዳይ ጴጥሮስ ሦስት ነገሮችን ያነሣል፤ (1) ባሎች በፍቅርና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ስምም ሆነው ከሚስቶቻቸው ጋር በመኖር ሚዛናዊና አስተዋይ ሰዎች መሆን አለባቸው (ኤፌ 5፥25-33፤ ቈላ 3፥19)።

(2) ሚስቶች የእግዚአብሔር ጸጋና ድነት እኩል ተካፋዮች መሆናቸውን ባሎች በመገንዘብ በአክብሮት ይይዟቸው ዘንድ ተገቢ ነው። ሚስቶች በፍላጎታቸው መሠረት ከበሬታንና አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ማግኘት አለባቸው። «ደካሞች» የሚለው ቃል ሴቶች የአካል ጥንካሬ የቱን ያህል እንደማያኩራ ሳያመለክት አይቀርም። ባል ሚስቱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ፍቅርን ልትገልጽለትና ልትረዳው ጥረት ስታደርግ ሊያመሰግናትና ሊያከብራት ይገባል (ቍ 1-6፤ ኤፌ 5፥23 እና ማብ ይመ)።

(3) ባሎች ሚስቶቻቸውን ለጕስቍልና መዳረግ የለባቸውም። አንድ ባል ከሚስቱ ጋር ተግባብቶ መኖር ካልቻለና ሚስቱም እንደ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኗን በመገንዘብ ሳያከብራት ከቀረ፣ በጸሎቱና በአምላኩ መካከል ዕንቅፋት በመፍጠር ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት እንደሚያበላሽ ጴጥሮስ ያመለክታል (ከቈላ 3፥19 ጋር ያነጻጽሩ)።

**3፥10 ሕይወትን የሚወድ፣ መልካም ቀኖችን ሊያይ፤** በቃልና በተግባር ከክፋት ርቀው ሰላምን የሚፈልጉት የሚከተሉትን ያገኛሉ በማለት ጴጥሮስ መዝ 34፥12-16ን ይጠቅሳል፤ እነርሱም ከዚህ በታች ያሉት ናቸው፤ (1) የእግዚአብሔር በረከትና ሞገስ የሞላበት ሕይወት፣ (2) ከርኅራኄውና ከጸጋ ጋር የእግዚአብሔርን ሀልዎት (ቍ 12)፤ እና (3) ጸሎታቸውን እግዚአብሔር መመለሱ (ከያዕ 5፥16፤ ከ1ዮሐ 3፥21-22 ጋር ያነጻጽሩ)።

**3፥15 ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት፤** ስለ ጌታ ኢየሱስ ለመመስከር ምንጊዜም ዝግጁ ሆኖ እንዲሆን ወንጌልን መግለጥ እንዲችል በውስጥ ሰውነት ክርስቶስ ጌታ ሆኖ ይከበር ዘንድ፣ የውስጥ ሕይወትም ለእርሱ ዐልፎ ይሰጥ ዘንድ ጴጥሮስ ጥሪ ያቀርባል (ከኢሳ 8፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ በትክክል ስለ ክርስቶስ ለመመስከርና ሌሎችንም ወደ እርሱ ለማምራት (ከዮሐ 4፥4-26 ጋር ያነጻጽሩ) የእግዚአብሔርን ቃልና እውነት ማወቅ አለብን።

[16]በክርስቶስ ያላችሁን መልካም ጠባይ
እክፉፍተው የሚናገሩ ሰዎች በሐሜታቸው
እንዲያፍሩ በጎ ኅሊና ይኑራችሁ።
[17]የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ከሆነ፣ ክፉ ሠርቶ
መከራ ከመቀበል ይልቅ መልካም አድርጎ
መከራ መቀበል ይሻላል፤ [18]እንዲሁም ክርስ
ቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ኀጢአት
ሞቶአልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ
ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ ስለ ዐመፀኞች
ሞተ፤ እርሱ በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን
ሕያው ሆነ፤ [19]በመንፈስም ሄዶ በወህኒ
ቤት ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው፤ [20]እነዚህ
በወህኒ የነበሩት ነፍሳት ቀድሞ በኖኅ ዘመን
መርከብ ሲሠራ እግዚአብሔር በትዕግሥት
ይጠብቃቸው የነበሩ እምቢተኞች ናቸው፤
በውሃ የዳኑት ጥቂት፣ ይኸውም ስምንት
ሰዎች ብቻ ነበሩ። [21]ይህም ውሃ አሁን
የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል፤ ይህም
የሰውነትን እድፍ በማስወገድ ሳይሆን
በንጹሕ ኅሊና በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ
መማፀኛ* ነው፤ የሚያድናችሁም በኢየሱስ
ክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት ነው፤
[22]እርሱም ወደ ሰማይ ወጥቶ በእግዚአብሔር ቀኝ
አለ፤ መላእክትና ሥልጣናት፣ ኀይላትም
ተገዝተውለታል።

## ለእግዚአብሔር መኖር

4 እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን
ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዐሳብ
ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው
መከራን የሚቀበል ሰው ኀጢአትን ትቶአል።
[2]ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ በሚቀረው
ምድራዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ
እንጂ እንደ ሥጋ ምኞት አይኖርም።
[3]አሕዛብ ፈቅደው እንደሚያደርጉት
በመዳራት፣ በሥጋዊ ምኞት፣ በስካር፣
በጭፈራ፣ ያለ ልክ በመጠጣት፣ በአስጸያፊ
የጣዖት አምልኮ የተመላለሳችሁበት ያለፈው
ዘመን ይበቃል። [4]ይህን በመሰለ ብኩን
ሕይወት ከእነርሱ ጋር ስለማትሮጡ እንግዳ
ሆኖባቸው በመደነቅ ይሰድቧችኋል። [5]ነገር
ግን በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ
ለተዘጋጀው መልስ ይሰጣሉ። [6]ወንጌል
ለሙታን እንኳ ሳይቀር የተሰበከው በዚህ
ምክንያት ነው፤ ስለዚህ እንደ ማንኛውም
ሰው በሥጋ ይፈረድባቸዋል፤ በመንፈስ ግን
እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይኖራሉ።
[7]የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቦአል፤
ስለዚህ መጸለይ እንድትችሉ ንቁ አእምሮ
ይኑራችሁ፤ ራሳችሁንም የምትገዙ ሁኑ።

3፥16 ቶ2፤ ሐሥ23፥1፤ 1ጴጥ2፥12፡15
3፥17 1ጴጥ2፥15፤ 20፤ 4፥15፡16፡19
3፥18 ሮሜ5፥2፤ ቆላ1፥22፤ ዕብ7፥27፤ 1ጴጥ2፥21፤ 4፥1፡6፡13
3፥19 1ጴጥ4፥6
3፥20 ዘፍ6፥3፡5፡13፡14፤ 8፥18፤ ሮሜ2፥4፤ ዕብ11፥7
3፥21 ቶ16፤ ሐሥ22፥16፤ 23፥1፤ 1ጴጥ1፥3
3፥22 ማቴ28፥18፤ ማር16፥19፤ ሮሜ8፥38፤ ዕብ4፥14
4፥1 ሮሜ6፥18፤ 1ጴጥ2፥21
4፥2 ሮሜ6፥2፤ 1ጴጥ1፥14
4፥3 ሮሜ13፥13፤ ኤፌ2፥2
4፥4 1ጴጥ3፥16
4፥5 ሐሥ10፥42
4፥6 1ጴጥ3፥19
4፥7 ሐሥ24፥25፤ ሮሜ13፥11

*3፥21 ወይም ምላሽ

---

3፥19 … **ነፍሳት ሰበከላቸው፤** ከቍ 18-20 ያለው ክፍል ከረጅም ዘመን አንሥቶ እስከሁን ድረስ ለተርጓሚዎች አስቸጋሪ እንደ ሆነ ነው፤ (1) ከአመለካከቶቹ አንዱ ክርስቶስ ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ (ቍ 18)፥ በኖኅ ዘመን ኀጢአት ሠርተው ታስረው ወደ ነበሩት መላእክት ሄደ (ቍ 20 ይመ፤ ከ2ጴጥ 2፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በሞትና በሰይጣን ላይ ያገኘውን ድልም ሰበከላቸው የሚል ነው (ቍ 22)። ሌላው ትርጕም ደግሞ ክርስቶስ በኖኅ አንደበት በመንፈስ ቅዱስ (ከ2ጴጥ 2፥5 ጋር ያነጻጽሩ) ሆኖ የመጨረሻ ፍርዳቸውን በሲዖል ውስጥ ሆነው በመጠባበቅ ላይ ለሚገኙት፣ ለማይታዘዙ የኖኅ ዘመን ሰዎች የማስጠንቀቂያ መልእክት ተናገረ የሚለው ነው። የማይታዘዙ ስለ ነበሩትና ስላልዳኑት፣ በኖኅ ዘመን ስለ ነበሩት ሰዎች የሚናገረው ይህኛው ትርጕም ከጽሑፉ ዐውድ ጋር ይስማማል። ይህም የክርስቶስ መንፈስ ባለፉት ዘመናት በነቢያት በኩል ተናገረ ከሚለው ከጴጥሮስ ሐሳብ ጋር ስምምነት አለው (2ጴጥ 1፥20-21)። (2) ይህም ሆኖ በ4፥6 ላይ ያለው ሐሳብ ዳግም ልደትን ያላገኙት ኀጢአተኞች፣ ከሞት በኋላ ድነትን ያገኙ ዘንድ ሌላ ዕድል ይኖራቸዋል አይሉም። ከሞት በኋላ ፍርድና (ዕብ 9፥27) በዘላለማዊ ጊዜ ውስጥ ተወስኖ ያለው የአንድ ሰው ዕጣ ፈንታ ይመጣሉ (ሉቃ 16፥26)።

3፥21 **ይህም ውሃ አሁን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ ያድናችኋል፤** የውሃ ጥምቀት ያድነናል የተባለው ንስሓ ለመግባታችን፣ በክርስቶስ ለማመናችንና ከዓለም ውስጥ ተለይተን ለመቆማችን የመታዘዝ መግለጫ ከመሆኑ የተነሣ ነው። ይህ ጥምቀት የክርስቶስ ለመሆናችንንና ከእርሱ ጋር ሞተን ለመነሣታችን መግለጫችንና ቃል ኪዳናችን ነው (ሮሜ 6፥3-5፤ ገላ 3፥27፤ ቈላ 2፥12 ይመ፤ ከሐሥ 2፥38-39 ጋር ያነጻጽሩ)። በኖኅ ዘመን ከነበረው የጥፋት ውሃ ጋር የቀረበውን ንጽጽር ልብ ማለት ያስፈልጋል (ቍ 20)፤ የጥፋት ውሃ ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ስለ ጥፋት ውሃ ለሰጠው ትምህርት የኖኅ ታዛዥ መሆን የእምነቱ መግለጫ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በውሃ መጠመቅም ከመጠመቃችን በፊት በክርስቶስ መሥዋዕትነት ድነትን ላመጣልን እምነታችን መግለጫ ነው።

4፥1 **መከራን የሚቀበል ሰው፤** ለክርስቶስ ዐላማ ሲሉ በፈቃደኝነት መከራን የሚቀበሉት፥ ኀጢአትን ለመቋቋምና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመከተል ቀና ይሆንላቸዋል። ራሳቸውን ከክርስቶስ ጋር አንድ አድርገዋል፤ በመስቀሉ ሥቃይም ተካፋዮች ሆነዋል። ከዚህም የተነሣ የኀጢአት ኀይል ተዳክሞአል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በአማኙ ሕይወት የላቀውን ስፍራ ይዟል (ቍ 2)። ይህ መንፈሳዊ መርሕ በአማኞች ሁሉ ሕይወት የሚሠራ ነው። ሥቃይ፣ ልግጫ ወይም መናቅ ቢደርስብንም እንኳ፣ እግዚአብሔርን በመታዘዝ መጽናት፣ በግብረ ገብና በመንፈሳዊ ረገድ ያጠነክረናል፤ ከእግዚአብሔርም የላቀ ጸጋን ያስገኝብታል (ቍ 14)።

4፥6 **ለሙታን፤** "አሁን በሕይወት ለሌሉት ወገኖች ገና በምድር ላይ እያሉ ወንጌል ተሰበከ" በሚለው አኳያ ሐረጉ ያዘለውን ጽንሰ ሐሳብ ማየት የሳቀ ማንዛቤ ይገኝበታል። ወንጌልን ሰሙ፤ አመኑም፤ በዚህ ምድር በሕይወት ባይኖሩም እንኳ (ይኸውም፡ "እንደ ማንኛውም ሰው በሥጋ ይፈረድባቸዋል")፣ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራሉ። ይህንን ጥቅስ ለግንዛቤ አመች ለማድረግ እንዲህ ሊባልም ይችላል፤ «ወንጌል ላመኑት ተሰበከ፤ እነዚህ ወገኖች ወንጌል ከተሰበከላቸው በኋላ ሞተዋል፤ ወንጌል የተሰበከላቸውም ከእግዚአብሔር ጋር የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው ነው።»

4፥7 **የሁሉ ነገር መጨረሻ ተቃርቦአል፤** ሕይወታችን ምን እንደሚመስል ከማይቀረው የክርስቶስ ዳግም ምጽአትና የዓለም ፍጻሜ አንጻር ማየት ይኖርብናል

8ፍቅር ብዙ ኀጢአትን ይሸፍናልና ከሁሉ
በላይ እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ፤ 9እርስ
በር ሳችሁ ያለ ማጒረምረም እንግድነት
ተቀባ በሉ። 10እንደ ታማኝ የእግዚአብሔ ልዩ
ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው
የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል፤ 11ከእናንተ
ማንም የሚናገር ቢኖር እንደ እግዚአብሔ ቃል
ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢኖር እግዚአብሔ
በሚሰጠው ብርታት ያገልግል፤ ይኸውም
እግዚአብሔ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት
እንዲ ክብር ነው፤ ክብርና ኀይል ለእርሱ
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።

## ክርስቲያን በመሆን የሚደርስ መከራ

12ወዳጆች ሆይ፤ እንደ እሳት የሚፈትን
ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር
እንደ ደረሰባችሁ በመቍጠር አትደነቁ፤
13ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ
ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች
በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ። 14ስለ ክርስቶስ
ስም ብትሰደቡ፣ የክብር መንፈስ የሆነው
የእግዚአብሔ መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ
ብፁዓን ናችሁ። 15ከእናንተ ማንም መከራን
የሚቀበል ቢኖር፣ ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ
ወይም ወንጀለኛ ወይም በሰው ነገር ጣልቃ
ገቢ ሆኖ መከራን አይቀበል፤ 16ክርስቲያን
በመሆኑ መከራ ቢደርስበት ግን ስለዚህ
ስም እግዚአብሔርን ያመስግን እንጂ አይፈር፤
17ፍርድ ከእግዚአብሔ ቤት የሚጀምርበት ጊዜ
ደርሶአልና። እንግዲህ ፍርድ የሚጀምረው
በእኛ ከሆነ የእግዚአብሔ ወንጌል የማይታዘዙ
ሰዎች መጨረሻቸው ምን ይሆን?
18እንግዲህ፣

"ጻድቅ የሚድነው በጭንቅ ከሆነ፣
ዐመፀኛውና ኀጢአተኛው እንዴት
ሊሆን ይሆን?"

19ስለዚህ እንደ እግዚአብሔ ፈቃድ መከራ
የሚቀበሉ ሁሉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ
ዐደራ ሰጥተው መልካም ማድረጋቸውን
ይቀጥሉ።

## ለሽማግሌዎችና ለጎልማሶች የተሰጠ ምክር

5 እንግዲህ ከእነርሱ ጋር እኔም ሽማግሌና
የክርስቶስ መከራ ምስክር የሆንሁ
እንዲሁም ወደ ፊት የሚገለጠው ክብር
ተካፋይ የምሆን በመካከላችሁ ያሉትን

4፥8 ምሳ10፥12፤ ያዕ5፥20፤ 1ጴጥ1፥22
4፥9 ሮሜ12፥13፤ ፊል2፥14
4፥10 ሮሜ12፥6:7፤ 1ቆሮ4፥2
4፥11 ሮሜ11፥36፤ 1ቆሮ10፥31፤ ኤፌ6፥10፤ 1ጢሞ2፥4
4፥12 1ጴጥ1፥6:7
4፥13 ማቴ5፥12፤ ሮሜ8፥17፤ 2ቆሮ1፥5፤ 1ጴጥ1፥7፤ 5፥1
4፥14 ማቴ5፥11፤ ዮሐ15፥21
4፥16 ሐሥ5፥41
4፥17 ኤር25፥29፤ ሕዝ9፥6፤ አሞ3፥2፤ 2ተሰ1፥8፤ 1ጢሞ3፥15
4፥18 ምሳ11፥31፤ ሉቃ23፥31
4፥19 1ጴጥ2፥15፤ 3፥17
5፥1 ሉቃ24፥48፤ ሐሥ11፥30፤ 1ጴጥ1፥5:7፤ 4፥13፤ ራእ1፥9

(ከዕብ 10፥25፤ ከያዕ 5፥8-9፤ ከ1ዮሐ 2፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። ጴጥሮስ ይህን የሕይወት መመሪያ ያስተዋለው የሚከተሉትን ግዴታዎች እንደሚያስከትል በመረዳት ነው፦ (1) በሙሉ ልብና በየዕለቱ ወደ እግዚአብሔር መጸለይን (ሐሥ 10፥9 እና ማብ፤ 12፥5 እና ማብ፤ ቈላ 4፥2:12 እና ማብ ይመ)፤ (2) ከልብ በመነጨ ፍቅር እርስ በርስ መዋደድን (ቍ 8 ይመ፤ ከ1፥22፤ ከማቴ 22፥37-39፤ ከ1ተሰ 4፥9-10፤ ከ2ጴጥ 1፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (3) የተቸገሩትን ማስተናገድንና ለእነዚሁም ቸርነት ማሳየትን (ቍ 9)፤ (4) ከመንፈስ ቅዱስ በተሰጡ ስጦታዎች ሌሎች አማኞችን ማገልገልን (ቍ 10 ይመ፤ በገጽ 1800 ላይ፣ *"ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ (5) ስለ ክርስቶስ መመስከርንና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል እግዚአብሔርን ማገልገልን (ቍ 11፤ ሐሥ 1፥5-8)፤ (6) እግዚአብሔርን ማመስገንን (ቍ 11)፤ (7) በፈተና ጊዜ ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ መጽናትን (ቍ 12-19)።

**4፥12 ብርቱ መከራ፤** ታማኝ አማኞች በሰይጣን ቍጥጥር ሥር በሚገኝ ወንጌልን በሚቃወምና ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌለው ዓለም ውስጥ የማይቀርላቸው መከራ እንደሚያጋጥማቸው አዲስ ኪዳን አጽንዖት ያደርጋል (በገጽ 744 ላይ፣ *"የጻድቃን መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ከልብ በመነጨና ታማኝ በሆነ እምነት ሕይወታቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው በሰጡት፣ በመንፈስ በሚመሩትና፣ የወንጌልንም እውነት በሚወዱት ላይ መከራና ሐዘን ይደርሳል። በርግጥ ከጽድቅ የተነሣ የሚመጣ ሥቃይ ክርስቶስን ከልብ ለመከተል ዋልሕ ማስረጃ ነው (ከማቴ 5፥10-12፤ ከሐሥ 14፥22፤ ከሮሜ 8፥17-18፤ ከ2ጢሞ 2፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህ የተነሣ በአንተ ሕይወት ላይ ችግር መድረሱ አንተ እግዚአብሔርን ለማስደሰትህ፣ ለእግዚአብሔርም ታማኝ ለመሆንህ ምልክት ሊሆን ይችላል። አንተ ከኀጢአት፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለው ዓለምና ከሰይጣን ጋር ጦርነት ስታደርግ ብዙ ጊዜ አብረው የሚከሠቱ ናቸው (1፥6-9፤ ኤፌ 6፥12)። እግዚአብሔር በብርቱ መከራ እንድታልፍ በማድረግ፣ አንተ የክርስቶስ ሥቃይ ተካፋይ እንድትሆን በመፍቀድ እርሱ የሚፈልገው ባሕርይ በሕይወትህ እንዲቀረጽ ያደርጋል (ሮሜ 5፥3-5፤ 2ቆሮ 1፥3-7፤ ያዕ 1፥2-4)። ይህም ሆኖ ስትሠቃይና ክርስቶስ ባለህ ታማኝ ሆነህ ስትጸና፣ «የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ላይ ስለሚያርፍ» (ቍ 14 እና ማብ፤ 2፥21 እና ማብ) በተባለው መሠረት በአንተ ላይ ስለሚያርፍ የተባረክህ ትባላለህ።

**4፥13 ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ፤** አንድ አማኝ ለክርስቶስ ሥራ ሲል መከራ በሚቀበልበት ጊዜ በጌታ ያለው ደስታ በስፋትና በጥልቀት የሚጨመርለት መሆኑ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ አንድ መርሕ ነው (ማቴ 5፥10-12፤ ሐሥ 5፥41፤ 16፥25፤ ሮሜ 5፥3፤ ቈላ 1፥24፤ ዕብ 10፥34 ይመ፤ የሚቀጥለውን ማብራሪያ ይመ)። ስለዚህ ለጌታ ሲሉ መለስተኛ ሥቃይ የሚደርስባቸው ወይም ምንም ዐይነት ሥቃይ የማይደርስባቸው ሰዎች ሊቀናባቸው አይገባም።

**4፥14 የክብር መንፈስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ፤** ለክርስቶስ ታማኞች ከመሆናቸው የተነሣ ሥቃይ የሚደርስባቸው ተባርከዋል (ከቍ 13፤ 3፥14፤ ከማቴ 5፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ መንፈስ ቅዱስ በተለየ ሁኔታ ያርፍባቸዋልና። ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ ሀልዎት የተሞላ ነው፤ ይህም የሚሆነው መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ሕይወት ስለሚሠራ፣ ስለሚባርካቸው፣ ስለሚረዳቸውና የመንግሥተ ሰማይን ክብር ከወዲሁ ስለሚሰጣቸው ነው (ከኢሳ 11፥1-2፤ ከዮሐ 1፥29-34፤ ከሐሥ 6፥9-15 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥17 ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት የሚጀምርበት፤** በገጽ 1822 ላይ፣ *"በአማኞች ላይ የሚሰጥ የተለየ ፍርድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ 2በእናንተ
ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ
ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር
እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን
በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ
ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት
ይሁን፤ 3እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ
መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ
2ጴጥ 3፥8-14 በላያቸው በመሠልጠን አይሁን። 4የእረኞች
አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን
አክሊል ትቀበላላችሁ።
5ጐልማሶች ሆይ፤ እናንተም እንዲሁ
ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርስ
በመከባበር ትሕትናን ልበሱ፤ ምክንያቱም፣
"እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤
ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።"
6ስለዚህ እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ
እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ
በታች ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ፤ 7እርሱ ስለ
እናንተ ስለሚያስብ የሚያስጨንቃችሁን
ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።
8ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤
ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን
በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ
ወዲህ ይዞራል። 9በዓለም ዙሪያ ያሉት
ወንድሞቻችሁ ተመሳሳይ መከራ
እንደሚቀበሉ ዐውቃችሁ በእምነት 1ዮሐ 3፥8
ጸንታችሁ ተቃወሙት።

5፥2 ዮሐ21፥16፤ 2ቆሮ9፥7፤ 1ጢሞ3፥3፤ ፊሞ1፥14
5፥3 ሕዝ34፥4፤ ማቴ20፥25-28፤ 1ጢሞ4፥12
5፥4 ዮሐ10፥11፤ 1ቆሮ9፥25፤ 1ጴጥ1፥4
5፥5 ምሳ3፥34፤ ማቴ23፥12፤ ኤፌ5፥21፤ 1ጴጥ3፥8
5፥6 ኢዮ5፥11፤ ያዕ4፥10
5፥7 መዝ37፥5፤ 55፥22፤ ማቴ6፥25፤ ዕብ13፥5
5፥8 ኢዮ1፥7፤ ሐዋ24፥25፤ 2ጢሞ4፥17
5፥9 ሐዋ14፥22፤ ሩላ2፥5፤ ያዕ4፥7

**5፥2 ጠብቁ፤** ሽማግሌዎች (መጋቢዎች ወይም ፓስተሮች) አማኞችን ደቀ መዝሙር በማድረግ፣ ቃሉን በመመገብና እነርሱ በመጠበቅ ረገድ ኀላፊነት አለባቸው (በገጽ 1866 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍና በገጽ 1716 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥2 ለጥቅም በመስገብገብ፤** መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከሁለት አደገኛ ኀጢአት መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል፤ (1) ከገንዘብ ፍቅር (1ጢሞ 3፥3፡8፤ ቲቶ 1፥7 ይመ)፡ የእግዚአብሔርን ሥራ የበላይ ሆነው ለሚያሠሩት መሪዎች ከቤተ ክርስቲያን በቂ ድጋፍ ማግኘት እንዳለባቸውና (ሉቃ 10፥7፡ 1ቆሮ 9፥14፤ 1ጢሞ 5፥17)፡ እነርሱም ለራሳቸውና ለቤተ ሰባቸው በሚቀርብላቸው መተዳደሪያ መርካት እንደሚኖርባቸው የአዲስ ኪዳን ቋሚ መመሪያ ነው። ማንም አገልጋይ በእግዚአብሔር ሥራ አማካይነት ራሱን ማበልጸግ የለበትም። ለዚህ ዐይነቱ ፈተና ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡት ለስግብግብነት፣ ተመሳስሎ ለማደርና ለሌብነት ኀጢአት ራሳቸውን ያጋልጣሉ። ለገንዘብ ጥቅም ሲሉ የእግዚአብሔርን ቃል የጽድቅ መንገድና የመንግሥቱን መርሖች ይሸቃቅጣሉና።

(2) **ከሥልጣን ጥማት፤** የሥልጣን ጥማት ያለባቸው መሪዎች ሥልጣናቸውን መከታ በማድረግ ሊያገለግሏቸው በሚገባ ወገኖች ላይ ፈላጭ ቈራጭ ይሆኑባቸዋል። ከዚህ ይልቅ አንድ መጋቢ (ስተር) ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ አሳልፎ በመስጠት፣ በትሕትና አገልግሎት፣ በጽድቅ ረገድ በመጽናት፣ በጸሎት በመትጋት፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመውደድ አርአያ ሆኖ ቤተ ክርስቲያንን መምራት አለበት።

**5፥5 ትሕትናን ልበሱ፤** ትሕትና የእግዚአብሔር ሰዎች መለያ መታወቂያ መሆን አለበት፤ ይኸውም ከትዕቢት ነጻ መሆን፣ የራስን ድካም መገንዘብ፣ እግዚአብሔር ወይም ሰዎች የሠሩትን ወይም ያከናወኑትን ተግባር የማስተዋል ልዩ ችሎታን ገንዘብ ማድረግ ማለት ነው (ከማቴ 11፥29፤ ከፊል 2፥3-4፥ ከቈላ 3፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። "ልበሱ" የሚለው ቃል (በግሪክ፣ ዪኤግኮምቡማይጹ) ትርጒሙ አንድን ሽርጥ ከዘወትር ልብስ ጋር አያይዞ መልበስ ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ዘመን ባሪያዎች በልብሳቸው ላይ ነጭ እራፊ ጨርቅ ወይም የሚጠለቅ ሽርጥ አድርገው ይታዩ ነበር፤ በዚህ መልክ ይታዩ የነበሩትም ሌሎች ሰዎች እነርሱ ባሪያዎች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ነው። ጴጥሮስ የሚከተሉት በእኛ ላይ እንዲታዩ ወይም ተፈጽመው እንዲገኙ በማሰብ ስለ ትሕትና ይመክረናል፡ (1) ከሌሎች ጋር በትሕትና ሥራችንን ስናከናውን የክርስቶስ ተከታዮች ለመሆናችን መታወቂያ እንዲሆንልን፡ (2) የእግዚአብሔርን ጸጋና ርዳታ እንድንቀበል (ቊ 5-7)። ጴጥሮስ ይህን ሲጽፍ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፎጣ ታጥቆ የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ ትዝ ሳይለው አይቀርም (ዮሐ 13፥4-5)።

**5፥7 እርሱ ስለ እናንተ ስለሚያስብ፤** እግዚአብሔር ስለ ልጆቹ ሁሉ ችግር የሚያስብ መሆኑ በቃሉ ላይ ከዳር እስከ ዳር አጽንዖት የተሰጠው እውነት ነው (መዝ 27፥10፤ 37፥5፡ 40፥17፤ 55፥22፤ ማቴ 6፥25-34፤ 10፥29-31፡ 11፥28-30 ይመ፤ ፊል 4፥6 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ ፍርሀትን፣ ጭንቀትንና ሐሳብን ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ መጣል አስፈላጊ ነው (ከመዝ 55፥22፤ ከሉቃ 12፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 100 ላይ፣ *"መግቦተ እግዚአብሔር"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥8 ጠላታችሁ ዲያብሎስ፤** የሰው ዘር ኀጢአት በሠራ ጊዜ ሰይጣን የዓለም ገዥ ሆነ (ዮሐ 12፥31፤ 14፥30፡ 16፥11)፡ መላው ዓለም በእርሱ ሥር ነው (1ዮሐ 5፥19)፡ ይህን ምድር ለመቈጣጠር ይንከራተታል፤ በክርስቶስ ያልሆኑትን ምርኮ አድርጎ የያዘበት የክፉ መናፍስት ሰራዊት አዛዥ ነው (ኤፌ 2፥2 ይመ፡ በገጽ 1499 ላይ፣ *"በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ከእርሱ ኀይል ነጻ የወጡት አማኞች ብቻ ናቸው (በገጽ 1443 ላይ፡ *"የእግዚአብሔር መንግሥት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይሁን እንጂ እንደሚያገሣ አንበሳ አማኞችን እንዳስፈራራ ይኖራል (ከመዝ 22፥13፤ ከሕዝ 22፥25 ጋር ያነጻጽሩ)፡ በተለይም በሥቃይ ውስጥ እንዲያልፉ በማስገደድ ሊያጠፋቸው ይፈልጋል (ቊ 8-10)። የእግዚአብሔርን ጥበቃ ችላ ያለውን ሁሉ በመንፈሳዊ ረገድ ያጠፋዋል። በክርስቶስ ደም ባለን እምነት (ራእ 12፥11)፤ በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በምናካሄደው መንፈሳዊ ጦርነት (ኤፌ 6፥11-18)፣ ወደ እግዚአብሔር በምናቀርበው ጸሎት (ማቴ 6፥13)፣ የሰይጣንን ተንኰል ለማፍረስ ሙሉ ትጥቅ አለን (ኤፌ 6፥11)፤ እርሱን ለመቋቋምና በእምነት ለመጽናትም እንዲሁ ታጥቀን እንገኛለን (ቊ 9)፤ ቃሉ፣ "በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም ካለው ይበልጣል ... " (ዮሐ 4፥4) ይላልና።

[10]በክርስቶስ ወደ ዘላለም ክብሩ
የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ
መከራ ከተቀበላችሁ በኋላ እርሱ ራሱ መልሶ
ያበረታችኋል፤ አጽንቶም ያቆማችኋል።
[11]ኀይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ለእርሱ
ይሁን፤ አሜን።

## የስንብት ሰላምታ

[12]እንደ ታማኝ ወንድም በምቈጥረው
በስ ልዋኖስ አማካይነት ይህንን አጭር
መልእክት ጽፌላችኋለሁ፤ የጻፍሁላችሁም
ልመክራችሁና ይህ እውነተኛ የእግዚአብሔር
ጸጋ መሆኑን ልመሰክርላችሁ ብዬ ነው።
በዚህ ጸጋ ጽኑ፤ቁሙ።

5፥10
መዝ18፥32፤
ሮሜ8፥28፤
2ቆሮ4፥17፤
2ተሰ2፥17፤
2ጢሞ2፥10፤
1ጴጥ1፥6
5፥11 ሮሜ11፥36
5፥12
ሐሥ15፥22፤
1ቆሮ16፥13፤
ዕብ13፥22
5፥13 ሐሥ12፥12
5፥14
ሮሜ16፥16፤
ኤፌ6፥23

[13]ከእናንተ ጋር የተመረጠችው፣
በባቢሎን የምትገኘው[ሠ] ሰላምታ
ታቀርብላችኋለች፤ እንዲሁም ልጄ ማርቆስ
ሰላምታ ያቀርብላችኋል። [14]በፍቅር አሳሳም
እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።
በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም
ይሁን።

*ሠ5፥13 በአንዳንድ ጥንታዊ ቅጆች ላይ በባቢሎን የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ይላል።*

# የሐዋርያው ጴጥሮስ መልእክት - ሁለተኛ

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲናዊ ሰላምታ (1፥1-2)

I. ትክክለኛ ዕውቀት የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ (1፥2ለ-21)
   (ሀ) እግዚአብሔርን በእውነት ማወቅ የቱን ያህል የመለወጥ ኀይል እንዳለው (1፥2ለ-4)
   (ለ) ክርስቲያናዊ እድገት እያደረ እየላቀ መሄዱ (1፥5-11)
   (ሐ) ስለ እውነት ቃል ሐዋርያው ያቀረበው ማረጋገጫ (1፥12-21)
      1. የተነሣሣበት ምክንያት (1፥12-15)
      2. እውነትን የገለጠበት መንገድ (1፥16-21)
         ሀ. ስለ ትንቢታዊ ቃል የዐይን ምስክርነት (1፥16-19)
         ለ. ትንቢት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያላቸው መሆናቸው (1፥20-21)

II. የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች መወገዛቸው (2፥1-22)
   (ሀ) ከሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ምን እንደሚጠበቅ (2፥1-3)
   (ለ) አማኞች ከእግዚአብሔር የሚጠብቁት (2፥4-10ሀ)
   (ሐ) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች አንዳንድ ጠባያት (2፥10ለ-19)
   (መ) ከእውነት ማፈግፈግ የሚያስከትለው አደጋ (2፥20-22)

III. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ርግጠኛ መሆኑ (3፥1-8ሀ)
   (ሀ) ዳግም ምጽአቱን መካድ (3፥1-7)
   (ለ) የዳግም ምጽአቱ እውነትነት ማረጋገጫ (3፥8-10)
   (ሐ) ዳግም ምጽአቱን እያሰቡ መኖር (3፥11-18ሀ)

ጸሎተ ቡራኬ (3፥18ለ)

**ጸሓፊ፤** *ጴጥሮስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የሚታመን እውነት የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ተግሣጽ ነው*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *ከ66—68 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

*ታሪካዊ ዳራ*

ስምዖን ጴጥሮስ ሰላምታ ባቀረበበት ክፍል የመልእክቱ ጸሓፊ እርሱ ራሱ መሆኑን ይገልጻል፤ በኋላም ይህኛው መልእክት ለተደራስያኑ አስቀድሞ ከጻፈው ሌላ ሁለተኛ መልእክት መሆኑን ያመለክታል፤ አሁን የሚጽፈው መልእክትም በታናሽ እስያ ለነበሩት፥ የመጀመሪያውን መልእክት ለጻፈላቸው አማኞች የተላከ መሆኑን ያሳስባል (1ጴጥ 1፥1)። ጨካኝ ሰው የነበረው ኔሮ በሰጠው ትእዛዝ ጴጥሮስም እንደ ጳውሎስ የተሠዋ ስለ ሆነ (ኔሮ ራሱ በሰኔ 68 ዓ.ም. ሞተ)፣ ሐዋርያው ይህን መልእክት የጻፈው በሮም ከተማ የሰማዕትነት ሞት ከመሞቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ከ66—68 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ ሳይሆን አይቀርም (1፥13-15)።

ጥንትም ሆነ ዛሬ የሚገኙ አንዳንድ ሊቃውንት በጴጥሮስ መልእክት አንደኛና ሁለተኛ መካከል ያለውን አስደናቂ ተመሳሳይነት ችላ ብለው፣ በልዩነታቸው ብቻ በማትኰር፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ የዚህ መልእክት ጸሓፊ አይደለም እስከ ማለት ደረሱ። ይሁን እንጂ በይዘት፣ በቃላት አመራረጥና አገባብ፣ በትኵረትና በአጻጻፍ ስልት ረገድ የተከሠተው ልዩነት፣ ጴጥሮስና ሁለቱ መልእክቶች የተጻፈላቸው ምእመናን ይገኙ ከነበሩበት የተለያየ ሁኔታና ከራሳቸው ከምእመናኑ የማንነት ልዩነት የተነሣ ነው ልዩነቱ እውን የሆነው የሚለው

አጥጋቢ መልስ ነው። (1) የመልእክቱ ተቀባዮች ይገኙበት የነበረው የመጀመሪያ ሁናቴ በዙሪያቸው የነበረው ኅብረተሰብ ያደርስባቸው ከነበረው ስደትና ጥቃት የተለየ ሲሆን፣ ይህም የቤተ ክርስቲያንን የእውነትና የጽድቅ መሠረቶች ሊቃናጉ ወደ ተንሣሡት ወደ ሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ማለትም ወደ ውስጥ ጠላቶች ተሸጋግሮአል። (2) ይህ ሁለተኛው መልእክት ሲጻፍ የራሱ የጴጥሮስ ሁናቴም የተለየ ነበር። የመጀመሪያውን መልእክት ሲጽፍ ብቁ የጽሕፈት ችሎታ የነበረው ሲላስ የቅርብ ረዳቱ ነበር (1ጴጥ 5፥12)፤ ሁለተኛውን መልእክት በጻፈበት ጊዜ ግን ሲላስ አጠገቡ ሊገኝ አልቻለም፤ ከዚህ የተነሣ ይህኛውን መልእክት ጴጥሮስ ሲጽፍ የተጠቀመው፥ በእናት ቋንቋው ተጽፎ የተቀየደውን የግሪክ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፥ ወይም ከሲላስ ያነሰ የጽሕፈት ችሎታ የነበረውን ጸሐፊ ጴጥሮስ የቅርብ ረዳቱ አድርጎ ሊሆን ይችላል።

### ዐላማ

ጴጥሮስ ይህን መልእክት የጻፈው በሚከተለው ምክንያት ነው፥ (1) አማኞች በትጋት እውነተኛ መንፈሳዊነትን፣ ስለ ክርስቶስም ምንጊዜም እውነት የሆነውን ዕውቀት እንዲከታተሉ፤ (2) በታናሽ እስያ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሐዋርያዊ እውነትን በማጣመም ላይ የነበሩትን የሐሰት ነቢያትና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን መሠሪ ተግባር ለማጋለጥና በዐጭሩ ለመቃወም ጴጥሮስ እውነተኛ አማኞችን የሚከተለውን በመምከር በ3፥17-18 ላይ የተነሣበትን ዐላማ ያጠቃልላል፤ (1) "በዐመፀኞች ስሕተት" ተስበው እንዳይወድቁ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ (3፥17)፤ (2) "በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት" እንዲያድጉ (3፥18)።

### ቅኝት

ይህ ዐጭር መልእክት አማኞች ሕይወትንና እውነተኛ መንፈሳዊነትን በተመለከተ ስለ ክርስቶስ ምንጊዜም እውነተኛ የሆነውን ዕውቀት ይዘው እንዲኖሩ በሚገባ ያስተምራል። የመጀመሪያው ምዕራፍ በክርስቲያናዊ እድገት ላይ ያተኩራል። አንድ ክርስቲያን በእምነት በመጀመር ግብረ ገባዊ ብቃትን፣ ዕውቀትን፣ ራስን መግዛትን፣ መጽናትን፣ እውነተኛ መንፈሳዊነትን፣ ወንድማዊ መተሳሰብንና ፍቅርን በትጋት መከታተል አለበት፤ እነዚህም ጥልቅ እምነትንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በትክክል ማወቅን ያስገኛሉ (1፥3-11)።

የሚቀጥለው ምዕራፍ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንደ እንጉዳይ በመፍላት ላይ ስላሉት ሐሰተኛ ነቢያትና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በጥብቅ ያስጠነቅቃል። ጴጥሮስ እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች፣ "በርኩስ ምኞት" ተነሣሥተው የሥጋ ፍላጎታቸውን እንዳሻቸው የሚያሳድዱ (2፥2፡7፡10፡13-14፡18-19)፣ ስግብግቦች (2፥3፡14-15)፣ ትዕቢተኞች (2፥18)፥ በራሳቸው ፈቃድ የሚነዱ (2፥10)፣ ባለ ሥልጣንን የሚንቁ (2፥10-12)፣ ሕግ ወጥ ሰዎች በማለት ያወግዛቸዋል (2፥1፡3፤ 3፥17)። ጴጥሮስ የእነዚህን አጥፊ መናፍቃን ክፉ ምኞትና ጠባይ ይፋ በማውጣት እውነተኛ አማኞችን ከአደጋ ለመጠበቅ ይፈልጋል (2፥1)።

በምዕራፍ 3 ላይ ጴጥሮስ እነዚህ የሐሰት ትምህርት መምህራን ስለ ጌታችን ዳግም ምጽአት ያላቸውን ጥርጥር ከንቱ ያደርጋል (3፥3-4)። በኖኅ ዘመን የነበረው ትውልድ በመታወር ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ ሆኖ በመጣው ታላቅ ማዕበል ላይ እንዳላገጠ ሁሉ፣ እነዚህ አላጋጮችም ጌታችን ዳግም እንደሚመጣ ስለ ተሰጠው ተስፋ ማስተዋል ተስኗቸው ነበር። ይሁን እንጂ ቀኍርጠኛ በሆነ ውሳኔ የማዕበል ፍርድ እውን እንደ ሆነ ሁሉ (3፥5-6)፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣል፤ ይህን ምድርም በእሳት ያጠፋል (3፥7-12)፤ ከዚያም ጻድቅ የሆነ አዲስ ሥርዐት ይመሠርታል (3፥13)። ከዚህ አኳያም አማኞች በአሁኑ ዘመን ቅዱስና ፈሪሀ እግዚአብሔር የሚታይበት ሕይወት መኖር ይገባቸዋል (3፥11፡14)።

### ልዩ ገጽታ

ሁለተኛ የጴጥሮስ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ስለ መጻፉ፣ ስለ አስተማማኝነቱና ሥልጣን ያለው ቃል ስለ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት ብርቱ አገላለጾች አንዱን ይዞ ይገኛል (1፥19-21)። (2) ምዕራፍ 2 እና የይሁዳ መልእክት የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን በማውገዝ ረገድ በሚያስደንቅ ሁኔታ ተመሳሳይነት አላቸው። የሐ ዋርያው ጴጥሮስ መልእክት ሁለተኛ ከተጻፈ በኋላ፣ ሐዋርያው ይሁዳ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ተመሳሳይ ችግር ፈጥረውበት ስለ ነበር፣ ተመሳሳይ የሆነውን ጕዳይ አጉልቶ ለማሳየት ሲል፣ በእግዚአብሔር

መንፈስ ምሪት ከተጻፈው ከጴጥሮስ መልእክት ውስጥ ከፊሉን የሐሳብ ማጉያ አድርጎ ሳይጠቀምበት አልቀረም (የይሁዳን መልእክት መግቢያ ይመልከቱ)። (3) ስለ ጌታችን ስለ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገልጹት ዋና ዋና ምዕራፎች ውስጥ ምዕራፍ 3 አንዱ ነው። (4) ጴጥሮስ ስለ ጳውሎስ መልእክቶች ሲያወሳ፣ "ሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት" (3፥15-16) ሲል ኢርቱዕ በሆነ መልክ የጳውሎስን መልእክቶች በማመልከት ከቅዱሳት መጻሕፍት ወገን መድቦአቸዋል።

## ሁለተኛ ጴጥሮስን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሁለተኛ ጴጥሮስ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሦስት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤ ❑ 1 ❑ 2 ❑ 3

*ማስታወሻ*

1 የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ
ስምዖን ጴጥሮስ፤ በአምላካችንና
በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ በኩል
እንደ ተቀበልነው ዐይነት ክቡር እምነት
ለተቀበሉት፤
2እግዚአብሔርንና ጌታችን ኢየሱስን በማወቅ
ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

## መጠራትንና መመረጥን ማረጋገጥ

3በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን
እርሱን በማወቅ ለሕይወትና ለእውነተኛ
መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ
የመለኮቱ ኀይል ሰጥቶናል። 4ከክፉ ምኞት
የተነሣ በዓለም ካለው ምግባረ ብልሹ ሕይወት
አምልጣችሁ ከመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች
እንድትሆኑ በእነዚህ ነገሮች አማካይነት እጅግ
ታላቅና ክቡር የሆነውን ተስፋ ሰጥቶናል።
5በዚህም ምክንያት በሙሉ ትጋት
በእምነ ታችሁ ላይ በጎነትን ለመጨመር
ጣሩ፤ በበጎነት ላይ ዕውቀትን፣ 6በዕውቀት
ላይ ራስን መግዛት፣ ራስን በመግዛት ላይ
መጽናትን፣ በመጽናት ላይ እውነተኛ
መንፈሳዊነትን፤ 7በእውነተኛ መንፈሳዊነት
ላይ ወንድማዊ መተሳሰብን፣ በወንድማዊ
መተሳሰብ ላይ ፍቅርን ጨምሩ። 8እነዚህ
ባሕርያት ተትረፍርፈው ቢኖሯችሁ ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ዳተኞችና ፍሬ
ቢሶች ከመሆን ይጠብቋችኋል። 9እነዚህ
ባሕርያት የሌሉት ግን የሩቁን የማያይ
ወይም ዕውር ነው፤ ከቀድሞው ኀጢአቱ
መንጻቱንም ረስቶአል።
10ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤
መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ለማጽናት
ከፊት ይልቅ ትጉ፤ ምክንያቱም እነዚህን
ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም፤ 11በዚህም
ወደ ጌታችንና አዳኛችን ወደ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት መግባት
በሙላት ይሰጣችኋል። 1ዮሐ 2:3-6

## የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት

12ስለዚህ ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች
ብታውቋቸውና በያዛችሁት እውነት
ብትጸኑም፣ ስለ እነዚህ ነገሮች እናንተን
ዘወትር ከማሳሰብ ቸል አልልም። 13በዚህ
ምድራዊ ድንኳን ውስጥ እስካለሁ ድረስ
እናንተን መኰትኰት ትክክል ሆኖ
ይታየኛል፤ 14ምክንያቱም ጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ እንደ ገለጠልኝ ይህን ምድራዊ
ድንኳን ቶሎ ጥዬ እንደምሄድ ዐውቃለሁ፤
15እነዚህን ነገሮች ከተለየኋችሁም በኋላ
ዘወትር ታስቡ ዘንድ እተጋለሁ።

1፥1 ሮሜ1፥1፤ 3፥21-26፤ ቲቶ2፥13፤ 1ጴጥ1፥1 1፥2 ቆላ3፥8፤ ሮሜ1፥7፤ ፊል3፥8፤ 2ጴጥ2፥20፤ 3፥18 1፥3 ቆላ2፤ ሮሜ8፥28፤ 1ጴጥ1፥5 1፥4 2ቆሮ7፥1፤ ኤፌ4፥24፤ ዕብ12፥10፤ ያዕ1፥27፤ 2ጴጥ2፥18-20፤ 1ዮሐ3፥2 1፥5 ቆላ2፤ ሩላ2፥3 1፥6 ቆላ3፤ ሐዋ24፥25፤ ዕብ10፥36 1፥7 ሮሜ12፥10፤ 1ተሰ3፥12 1፥8 ቆላ2፤ ዮሐ15፥2፤ ሩላ1፥10፤ ቲቶ3፥14 1፥9 ማቴ1፥21፤ ኤፌ5፥26፤ 1ዮሐ2፥11 1፥10 መዝ 15፥5፤ ሮሜ 8፥28፤ 2ጴጥ 3፥17፤

1፥10 ይሁ1፥24 1፥11 መዝ145፥13፤ 2ጢሞ4፥18፤ 2ጴጥ2፥20፤ 3፥18 1፥12 ፊል3፥1፤ 1ዮሐ2፥21፤ 2ዮሐ1፥2፤ ይሁ1፥5 1፥13 ኢሳ38፥12፤ 2ቆሮ5፥1፡4፤ 2ጴጥ3፥1 1፥14 ዮሐ13፥36፤ 21፥18፡19፤ 2ጢሞ4፥6 1፥15 ሉቃ9፥31

**1፥3 ለሕይወትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚያስፈልገንን ሁሉ፤** የሰማይ አባታችን ፍቅር፣ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነው ድነት፣ ክርስቶስ በመንግሥተ ሰማይ ለእኛ ሲል መማለዱ፣ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ ማደሩና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቃችን፣ የቅዱሳን አንድነትና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል፣ የአማኞችን መሠረታዊ ፍላጎት ሁሉ ለማሟላትና ለእውነተኛ መንፈሳዊነት በቂ ናቸው (ማቴ 11፥28-30፤ ዕብ 4፥16፤ 7፥25፤ 9፥14)።

(1) በክርስቶስ ያገኘነውን ፍጹም ድነት የሚያሳየውን የእግዚአብሔር ቃል ብቃት ሙሉ ለማድረግ ተጨማሪ የሰው ጥበብ፣ ስልት ወይም ትወራ ከቶ አያስፈልግም። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን የጠፉ ሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት የኢየሱስ ቃል፣ በአዲስ ኪዳን ላይ የተገለጠው ሐዋርያዊ እምነትና የእግዚአብሔር ጸጋ በቂ ነበሩ፤ ከዚህ ላይ የተጠቀሱት ዛሬም ቢሆን እንደ ያኔው ብቃት አላቸው። ጌታ ኢየሱስ ከተናገረውና ከሰጠው ትምህርት እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሐዋርያት ከመሰከሩት ቃል ሌላ ልቀት፣ ጥልቀት፣ ብርታትና ርዳታ ከቶ የለም። “መንገድ፣ እውነትና ሕይወት” የሆነው ጌታ ኢየሱስ ብቻ ነው (ዮሐ 14፥6)።

(2) የምናምነው ወንጌል በዚህ ዘመን ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፣ ወንጌላችን ከክርስቶስና ከሐዋርያት ወንጌል ያነሰ መሆኑን ያሳያል።

**1፥4 ከመለኮታዊ ባሕርዩ ተካፋዮች እንድትሆኑ፤** የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች መሆናችን የእግዚአብሔርን ሕይወት የምንቀበልበት የአዲስ ልደት ሌላው መገለጫ ነው (በገጽ 1606 ላይ፤ *“ዳግም ልደት”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች የምንሆነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንድንሆንና በቅድስናው እንድንመስለው ነው (ከ1ቆሮ 6፥19-20፤ ከኤፌ 4፥24 ጋር ያነጻጽሩ)።

**1፥5 በእምነታችሁ ላይ … ለመጨመር፤** በመንፈሳዊ ረገድ አሸናፊዎችና በእግዚአብሔርም ፊት ፍሬያማ ለመሆን (ቍ. 8)፣ አንድ ክርስቲያን ማዳበር ያለበትን በጎ ባሕርያት ጴጥሮስ ይዘረዝራል። “በሙሉ ትጋት” የሚለው ሐረግ አማኞች በክርስቲያናዊ እድገታቸው ንቁ ተሳታፊዎች መሆን እንዳለባቸው ያሳያል (ከፊል 2፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)። ክርስቲያን የሆኑ ሁሉ ሳይውሉ ሳያድሩ እነዚህን ሰባት በጎ ምግባሮች በእምነታቸው ላይ ለመጨመር መጣር አለባቸው (ቍ. 5-8)። የእውነተኛ መንፈሳዊነት ባሕርያት መገለጫዎችን ሆን ብለን በሕይወታችን ካላዳበርናቸው በቀር፣ በዘፈቀደ ወዲያውኑ አያድጉም (በገጽ 1853 ላይ፣ *“የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**1፥10 መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ለማጽናት … ትጉ፤** እምነታችንና ድነታችን በአንድ ጊዜ ተከናውኖ ተፈጽሞአል ተብሎ መታየት የለበትም፤ እስከ መጨረሻው አማኞች ሆነን የምንዘልቀው፣ በቍ 5-9 ላይ የተዘረዘሩትን በጎ ምግባሮች በእግዚአብሔር ጸጋ በእምነታችን ላይ ለመጨመር ማንኛውንም ጥረት ስናደርግ ነው (በገጽ 1860 ላይ፣ *“ምርጫና አስቀድሞ መወሰን”* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**1፥11 ዘላለማዊ መንግሥት መግባት በሙላት፤** አንዳንድ አማኞች ከእንዝህላልነታቸው የተነሣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚገቡት በጭንቅ ነው (1ቆሮ 3፥15)፤ በቅድስና ሕይወት እስከዘለቂታው የጸኑት ሌሎች ግን በክብርና በሙላት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ (ማቴ 25፥21፤ ሐዋ 7፥55-56፤ 2ጢሞ 4፥7-8፡18)፡

16ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይልና
ስለ መምጣቱ የነገርናችሁ እኛ የእርሱን
ግርማ በዐይናችን አይተን እንጂ፣ በሰዎች
ጥበብ የተፈጠረውን ተረት ተከትለን
አይደለም፤ 17ምክንያቱም ከግርማዊው
ክብር "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው
ልጄ ይህ ነው" የሚል ድምፅ በመጣለት
ጊዜ ከእግዚአብሔር አብ ክብርና ሞገስ
ተቀብሎአል፤ 18እኛም ከእርሱ ጋር በቅዱሱ
ተራራ ላይ በነበርንበት ጊዜ ይህ ድምፅ
ከሰማይ ሲመጣ ሰምተናል።
19እንግዲያስ ትንቢታዊው ቃል ይበልጥ
ተረጋግጦልናል፤ ሌሊቱ እስኪነጋና
የንጋት ኮከብ በልባችሁ እስኪበራ ድረስ፣
በጨለማ ስፍራ ለሚበራ መብራት ጥንቃቄ
እንደሚደረግ እናንተም ለዚህ ቃል
ብትጠነቀቁ መልካም ታደርጋላችሁ።

1፥16 ማቴ17፥1-8፤ ማር13፥26፤ 14፥62
1፥17 ማቴ3፥17
1፥18 ማቴ17፥6
1፥19 መዝ119፥105፤ ሉቃ1፥78፤ 2ቆሮ4፥6፤ 1ጴጥ1፥10፤ ራእ22፥16
1፥20 2ጴጥ3፥3
1፥21 2ሳሙ23፥2፤ ሐዋ1፥16፤ 3፥18፤ 2ጢሞ3፥16፤ 1ጴጥ1፥11
2፥1 ዘዳ13፥1-3፤ ኤር6፥13፤

20ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ልታውቁ
ይገባችኋል፤ በመጽሐፍ ያለው የትንቢት
ቃል ሁሉ ማንም ሰው በገዛ ራሱ መንገድ
የሚተረጕመው አይደለም፤ 21ምክንያቱም
ትንቢት ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ
ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ
በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።

## ሐሰተኛ መምህራንና መጨረሻቸው

2 ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት በሕዝቡ
መካከል እንደ ነበሩ እንዲሁም በእናንተ
መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ፤
እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው ጥፋት
የሚያስከትል የስሕተት ትምህርት በስውር

2፥1 ማቴ7፥15፤ 1ቆሮ6፥20፤ 1ጢሞ4፥1፤ ይሁ1፥4

**1፥19 ትንቢታዊው ቃል ይበልጥ ተረጋግጦልናል፤** ጴጥሮስ ሰውኛ የሆነውን ሐሳብ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያነጻጽራል (ቍ 16)፡ ቅዱሳት መጻሕፍት የመነጩት ከመለኮት መሆኑን በመመስከር ትንቢት ሁሉ ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የመነጨ መሆኑን ያረጋግጣል (ቍ 21)፤ ይህም የእግዚአብሔር መልእክት ሊሳሳት የማይችል (ስሕተት ወይም ግድፈት ከቶ የማይገኝበት)፥ ሕጸጽ አልባ ነው (ከስሕተት፣ ከሐሰት ወይም ከአታላይነት የጸዳ ነው)። መሳሳት አለመቻልና ሕጸጽ አልባነት ሊነጣጠሉ አይችሉም፥ ቅዱሳት መጻሕፍት ሕጸጽ አልባ መሆን የቻሉት ከእግዚአብሔር ቃል መሳሳት አለመቻል የተነሣ ነውና። ከዳር እስከ ዳር ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በርግጥ እውነት ነው፥ የሚሰጠው ትምህርትም አስተማማኝ ነው (ከ2ሳሙ 23፥2፤ ከኤር 1፥7-9፥ ከ1ቆሮ 14፥37 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1941 ላይ፥ *«መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆንና ያለው ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትንታኔ ጽሑፍ ይመ)።

**1፥20 በመጽሐፍ ያለው የትንቢት ቃል ሁሉ ... አይደለም፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትንቢት በጸሐፊው የግል ሐሳብ ወይም አመክንዮ የተገኘ አይደለም፤ ነገር ግን የተገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ነው።

**1፥21 ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት፤** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው ትንቢት ምንጩ መለኮት መሆኑንና ሥልጣኑም የቱን ያህል ከፍ ያለ መሆኑን ጴጥሮስ ያረጋግጣል (በገጽ 1009 ላይ፣ *«ነቢይ በብሉይ ኪዳን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትንታኔ ጽሑፍ ይመ)። አማኞች ሁሉ እንዲሁ ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር እስትንፋስና ሥልጣንም ያላቸው ስለ መሆናቸው የማይናወጥ አቋም ሊኖራቸው ይገባል። ለዚህም የሚከተሉት አጥጋቢ ምክንያቶች ይገኛሉ፤ (1) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ሐዋርያትና መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምሩት እውነት ስለ መሆኑ ማረጋገጫው ይኸው ብቻ ነው (መዝ 119፤ ዮሐ 5፥47 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1941 ላይ፣ *«መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆንና ያለው ሥልጣን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትንታኔ ጽሑፍ ይመ)።

(2) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ጽኑ አመለካከት እስከሌለ ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን ስለ እምነቷ እውነተኛና ርግጠኛ የሆነ መሠረት የላትም፤ ስለ ድነት ርግጠኛ መሆን አትችልም፥ ግብረገባዊ የሆኑ ፍጹም ሕጎችም አይኖሯትም፥ ከጥርጥር ነጻ የሆነ መልእክት አይኖራትም፤ በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅና ስለ ታምራት ሥራ ርግጠኛ በመሆን በተስፋ መጠባበቅ አትችልም፥ እንዲሁም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይቀሬ ዳግም ምጽአት ርግጠኛ በመሆን በተስፋ መጠባበቅ አትችልም።

(3) ስለ ቅዱሳ መጻሕፍት ብርቱ አቋም እስከሌለ ድረስ፥ መጽሐፍ ቅዱስን የእምነታቸው መሠረት ያደረጉ አማኞች፣ እየተለዋወጠ በመሄድ ላይ ያለውን የዓለምን ዕሴት፥ ሰዋዊ ፍልስፍናን እንዲሁም ፈሪሀ እግዚአብሔር አልባ የሆነውን ባህላዊ ልምምድ (መዝ 119፥160) የራሱን የእግዚአብሔርን ሥልጣን መሠረት በማድረግ በትዝረዛሩት ላይ ለመፍረድና እነዚሁንም ለመተው ፍጹምና ነባራዊ የሆነ እውነት አይኖራቸውም።

(4) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ብርቱ አቋም ከሌለ፣ ክርስቲያኖች የመጨረሻ ቀኖችን ብርቱ ፈተናዎች ለመቋቋም ዝግጁ አይሆኑም (1ተሰ 2፥1-12 ይመ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፥ 2ጢሞ 3፥1 እና ማብ ይመ)።

(5) ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ብርቱ አቋም ከሌለ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ ሥልጣንና ትምህርት ደካማ ይሆናሉ፤ ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስ ስሜታዊ በሆነ ሃይማኖታዊ ተመክሮ ወይም ነጻና ሒሳዊ በሆነ አመክንዮ ይተካል (2፥1-3)።

**2፥1 በእናንተ መካከል ሐሰተኞች መምህራን ይነሣሉ፤** እያሌ ሐሰተኞች መምህራን በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሊኖሩ እንደሚችሉ መንፈስ ቅዱስ በተደጋጋሚ ያስጠነቅቃል። በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የክሕደት ትምህርትን የሚያስተምሩ መምህራንንና መሪዎችን በተመለከተ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተጀመረ ሲሆን (ማቴ 24፥11 እና ማብ ይመ፥ 24፥24-25)፣ በጳውሎስ (2ተሰ 2፥7 እና ማብ፥ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ፤ 2ጢሞ 3፥1-5)፣ በጴጥሮስ (ቍ 1-22)፣ በዮሐንስ (1ዮሐ 2፥18፤ 4፥1፤ 2ዮሐ 1፥7-11)፣ በይሁዳ (ይሁ 1፥3-4፡12፡18) እንዲሁም ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በላከው መልእክት በመንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶ ቀጥሎአል (ራእ 2፥2፡6 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1519 ላይ፣ *«የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትንታኔ ጽሑፍ ይመ)።

**2፥1 የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው፤** ጴጥሮስ በመልእክቱ ላይ በገለጸው መሠረት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትና ጌታን በመካድ ላይ የሚገኙት

ያስገባሉ፤ በዚህም በራሳቸው ላይ ድንገተኛ
ጥፋት ያመጣሉ። 2 ብዙዎች አስነዋሪ
ድርጊቶቻቸውን ይከተላሉ፤ በእነርሱም
ምክንያት የእውነት መንገድ ይሰደባል።
3 እነዚህ ሐሰተኞች መምህራን እየተስገበገቡ
በፈጠራ ታሪካቸው ይበዘብዙዋችኋል።
ፍርዳቸው ከጥንት ጀምሮ ዝግጁ ነው፤
መጥፊያቸውም አያንቀላፋም።
4 እግዚአብሔር ኀጢአት የሠሩትን መላእክት
ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም[ሀ] ከጣላቸውና
በጨለማ ጕድጓድ ውስጥ ለፍርድ
ካስቀመጣቸው፣ 5 የጽድቅ ሰባኪ የነበረውንም
ኖኅን ከሌሎች ሰባት ሰዎች ጋር አድኖ
ለቀድሞው ዓለም ሳይራራ በኀጢአተኞች
ላይ የጥፋት ውሃ ካመጣ፣ 6 ደግሞም
ኀጢአት ለሚያደርጉ ሁሉ ምሳሌ እንዲሆኑ
የሰዶምንና የገሞራን ከተሞች ዐመድ
እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎ ከፈረደባቸው፣
7 ጻድቅ የሆነውንና በዐመፀኞች ሴሰኛ
ድርጊት እየተሣቀቀ የኖረውን ሎጥን ካዳነ፣
8 ያ ጻድቅ ሰው በእነርሱ መካከል ሲኖር
በሚያየውና በሚሰማው ነገር ነፍሱ ዕለት
ዕለት በዐመፀኛ ድርጊታቸው ብትጨነቅም፣
9 ጌታ፣ በእውነት እያመለኩት የሚኖሩትን
ከፈተና እንዴት እንደሚያድናቸውና
ዐመፀኞችን እየቀጣ ለፍርድ[ለ] ቀን እንዴት
ጠብቆ እንደ ሚያቈያቸው ያውቃል።
10 በተለይም በር ኩስ ምኞት የሥጋ
ፍላጎታቸውን[ሐ] የሚከተሉትንና ሥልጣንን
የሚንቁትን ለፍርድ ጠብቆ ያቈያቸዋል።
እነዚህ ሰዎች ደፋሮችና እብሪተኞች
ስለሆኑ ሰማያውያንን ፍጡራን ሲሳደቡ
አይፈሩም፤ 11 ነገር ግን መላእክት ከእነርሱ

2፥2 ይሁ1፥4
2፥3 ሮሜ14፤ 2ቆሮ2፥17፤ 1ተሰ2፥5
2፥4 ዘፍ6፥1-4፤ 1ጢሞ3፥6፤ ይሁ1፥6፤ ራእ20፥1:2
2፥5 ዘፍ6፥5-8:19፤ ዕብ11፥7፤ 1ጴጥ3፥20፤ 2ጴጥ3፥6
2፥6 ዘፍ19፥24:25፤ ዘኍ26፥10፤ ማቴ10፥15፤ 11፥23:24፤ ሮሜ9፥29፤ ይሁ1፥7
2፥7 ዘፍ19፥16፤ 2ጴጥ3፥17
2፥8 ዕብ11፥4
2፥9 መዝ37፥33፤ ማቴ10፥15፤ ሮሜ15፥31፤ ራእ3፥10
2፥10 2ጴጥ3፥3፤ ይሁ1፥8:16:18
2፥11 ይሁ1፥9

*ሀ 2፥4 በግሪኩ ታርታሩስ ይለዋል*
*ለ 2፥9 ወይም ዐመፀኞችን ለቅጣት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ*
*ሐ 2፥10 ወይም የኀጢአተኛ ባሕርያቸውን*

(በግሪክ፣ "አርኔወማይ" የቃሉ ትርጕም መካድ ወይም በራስ ፈቃድ መተው ማለት ነው) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ቀጥተኛ መንገዱን ትተው ባዝነዋል (ቍ. 5)፤ በመሆኑም፣ "የደረቁ ምንጮች" (ቍ. 17) ሆነዋል። በአንድ ወቅት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ክፋት አምልጠውት ነበር፤ አሁን ግን በኀጢአት እስራት ውስጥ ገብተዋል (ቍ. 20)።

**2፥2 የእውነት መንገድ ይሰደባል፤** ክርስቲያን ነን የሚሉት ብዙዎች አማኞች የእነዚህን የሐሰተኛ ሰባኪዎች፣ "አስነዋሪ" ድርጊት (ይኸውም የዘመት ኢግብረገባዊነት) ይከተላሉ። ከመሪዎቹና ከተከታዮቻቸው አስነዋሪ የሕይወት ዘይቤ የተነሣ እግዚአብሔርና ወንጌሉ መሣቂያ መሳለቂያ ይሆናሉ (2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ ይመ)።

**2፥3 እየተስገበገቡ በፈጠራ ታሪካቸው፤** የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች አገልግሎታቸውንና የምቾት ኑሮአቸውን ለማራመድ ሲሉ፣ በስግብግብነትና በዘዴ ከአማኞች ገንዘብን ለማግኘት ወንጌልን የጥቅማቸው ማሳደጃ ያደርጉታል። (1) ከሐሰተኞች አገልጋዮች በበይት ዘዴዎች አንዱ፣ "በፈጠራ ታሪካቸው" መጠቀም መሆኑን አማኞች ልብ ማለት አለባቸው፤ ይህንም የሚያደርጉት ይኸውም ማራኪ የሆኑ ነገር ግን ቅንጣት እውነት እንኳ የሌላቸውን ታሪኮች በመንገር ነው፤ ወይም የእግዚአብሔር ሕዝብ ገንዘብ ይለግሱ ዘንድ የተጋነነ አነጋገን በማቅረብ ነው። ራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ፤ በእነዚህ የፈጠራ ታሪኮች አገልግሎታቸውን ያስፋፋሉ (ከ2ቆሮ 2፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ጥንቃቄ የማያደርገውና ቅን የሆነው የእግዚአብሔር ልጅ በቀላሉ የብዝበዛ ዒላማ ይሆናል። (2) እነዚህ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን እውነትና ሕዝብ በስግብግብነትና በአታላይነት በመበከላቸው ለፍርድና ለጥፋት የተጠበቁ ናቸው።

**2፥4 መላእክት … ወደ ገሃነም ከጣላቸውና፤** ይህ የሚያመለክተው በአዲስ ኪዳን ክፉ መናፍስት ተብሎ የተነገረላቸውን፣ በእግዚአብሔር ላይ ከሰይጣን ጋር ያመፁትን መላእክት ሳይሆን አይቀርም (ሕዝ 28፥12 እና ማብ ይመ)። አንዳንዶቹ ክፉ መናፍስት በሲኦል ውስጥ ለምን እንዳሉ፣ የቀሩት ደግሞ ከሰይጣን ጋር በምድር ላይ በነጻ እንዲንቀሳቀሱ ለምን እንደ ተደረገ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አልተገለጸም (ከይሁ 1፥6 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ "*በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥8 ጻድቅ … ነፍሱ … ብትጨነቅም፤** በርግጥ ጻድቃን የሆኑ አማኞች ዐይነተኛ መለያ ባሕርያቸው ጽድቅን ወድደው ክፋትን መጥላታቸው ነው (ዕብ 1፥9 እና ማብ ይመ)። ነፍሳቸው በዓለም ውስጥ ገሀድ ሆኖ በሚገኝ ኀጢአት፣ ኢግብረገባዊነትና ፈሪሀ እግዚአብሔር አልባነት የተነሣ (ሕዝ 9፥4 እና ማብ ይመ፤ የሐ 2፥13-17፤ ሐሥ 17፥16 ይመ) ቆዝማለች፤ ተሠቃይታለችም (ቍ. 7-8)።

**2፥9 በእውነት እያመለኩት የሚኖሩትን፤** ሎጥ ዙሪያውን ከቦት ለነበረው ክፋትና ኢግብረገባዊነት የሰጠው ምላሽ (ቍ. 10)፣ ሳገኘው ትድግናና በዘላለም ሕይወት ውስጥ ለሚኖረው ዕጣ ፈንታ የመለያ ፈተና ሆነ። (1) እግዚአብሔር ሎጥን የታደገው ክፋትን በመጥላቱና፣ "በዐመፀኞች ሴሰኛ ድርጊት" በመሣቀቁ ነው (ቍ. 7፤ ቀደም ያለውን ማብ ይመ)።

(2) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ለመቀበልና ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌላቸው ላይ ቍጣውን ለማፍሰስ ተመልሶ ሲመጣ (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ)፤ እንደ ሎጥ እርሱን ከማመናቸውና ከመውደዳቸው የተነሣ፣ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ስሜታቸው እንደ ነዳቸው በለየለት ኀጢአት በሚኖሩት ሰዎች አማካይነት የተሠቃዩትን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን ለራሱ ይሰበስባል (በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) እግዚአብሔር ከዮትውልዱ ታማኝ የሆኑትን አማኞቹን ኢግብረገባዊ ከሆኑና ከተበከሉ ሰዎች መካከል እንዴት እንደሚታደጋቸው የሚያውቅ መሆኑን ርግጠኞች ልንሆን እንችላለን (ከማቴ 6፥13፤ ከ2ጢሞ 4፥18፤ ከራእ 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥10 ሥልጣንን የሚንቁትን … ሰማያውያንን ፍጡራን፤** ከዚህ ላይ ጴጥሮስ ክፋትን ስለሚቃወሙት፣ ይኸውም ክርስቶስንና ቃሉን ጨምሮ፣ እንደ ሰዶም አመንዝራዎች (ቍ. 8 ይመ፤ ከዘፍ 19፥4-11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ማንኛውንም ዐይነት ሥልጣን ስለሚንቁት ስለ ኀጥአንና ኢግብረ-ገባዊ ስለ ሆኑት ሰዎች ይናገራል።

ይልቅ ብርቱና ኀያል ሆነው ሳሉ፣ በጌታ ፊት
በእነርሱ ላይ የስድብ ቃል አይሰነዝሩም።
12እነ ዚህ ሰዎች ግን ምንም በማያውቁት
ነገር እየገቡ ይሳደባሉ፤ እነርሱም ለመያዝና
ለመገደል እንደ ተወለዱ፣ በስሜታቸው
ብቻ እንደሚመሩና ልቦናም እንደሌላቸው
አራዊት ናቸው፤ የሚጠፉትም
እንደ እንስሳት ነው።
13ለበመፃቸው የሚገባውን የዐመፅ ዋጋ
ይቀበላሉ፤ በጠራራ ፀሓይ ሲፈንጥዙ እንደ
ደስታ ይቈጥሩታል፤ በግብዣ ላይ ሳሉ
ነውረኞችና ርኩሶች ሆነው ከእናንተም
ጋር በፍቅር ግብዣ ላይ[ሠ] ይቀመጣሉ፤
14ዐይናቸው ቅንዝር የተሞላ በመሆኑ
ኀጢአትን ከመሥራት አይቈጠቡም፤
ጽኑ ያልሆኑትን ነፍሳት ያስታሉ፤ ስስትን
የለመደ ልብ አላቸው፤ የተረገሙ ናቸው!
15ቀናውን መንገድ ትተው፣ የዐመፅን
ደመወዝ የወደደውን የቢዖርን ልጅ
የበለዓምን መንገድ ተከትለው ስተዋል፤
16እርሱ ግን ስለ መተላለፉ ተግሥጸአል፤
መናገር የማይችል አህያ በሰው ቋንቋ
ተናግሮ የነቢዩን እብደት ገታ።
17እነዚህ ሰዎች የደረቁ ምንጮችና
በዐውሎ ነፋስ የሚነዱ ደመናዎች ናቸው፤
የሚጠብቃቸውም ድቅድቅ ጨለማ ነው፤
18ከንቱ ቃል እየደረደሩ በስሕተት ከሚኖሩት
መካከል አምልጠው የመጡትን ሰዎች በሴሰኛ
ሥጋዊ ምኞት በማባበል ያታልላሉና።
19እነርሱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው
ሳሉ፣ ሌሎችን ነጻ ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ
ይሰጧቸዋል፤ ሰው ለተገዛለት ለዚያ ነገር
ባሪያ ነውና። 20ጌታችንንና አዳኛችንን
ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ከዓለም ርኵሰት
ካመለጡ በኋላ እንደ ገና ተጠላልፈው
ቢሸነፉ ከመጀመሪያው ይልቅ የኋለኛው ሁኔ
ታቸው የከፋ ይሆንባቸዋል። 21የጽድቅን
መንገድ ካወቁ በኋላ ከተሰጣቸው ቅዱስ
ትእዛዝ ወደ ኋላ ከሚመለሱ፣ ቀድሞውኑ
የጽድቅን መንገድ ባላወቁዋት ይሻላቸው
ነበር። 22"ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል"
እንዲሁም "ዐሣማ ቢታጠብም ተመልሶ
በጭቃ ላይ ይንከባለላል" የሚለው ምሳሌ
እውን ይሆንባቸዋል።

## የጌታ ቀን

3 ወዳጆች ሆይ፤ ይህ አሁን የምጽፍላችሁ
ሁለተኛው መልእክት ነው። ሁለቱንም
መልእክቶች የጻፍሁላችሁ ቅን ልቦናችሁን
እንድታነቃቁ ለማሳሰብ ነው፤ 2ደግሞም
ቀድሞ በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውን ቃል
እንዲሁም በሐዋርያት አማካይነት በጌ
ታችንና በአዳኛችን የተሰጠውን ትእዛዝ
እንድታስቡ ነው።
3ከሁሉ አስቀድሞ ይህን ዕወቁ፤
በመጨረሻው ዘመን የራሳቸውን ክፉ ምኞት
የሚከተሉ ዘባቾች እየዘበቱ ይመጣሉ።
4እነርሱም፣ "'እመጣለሁ' ያለው ታዲያ
የት አለ? አባቶች ከሞቱበት ከፍጥረት
መጀመሪያ አንሥቶ እስካሁን ድረስ ሁሉም
ነገር እንዳለ ይኖራል" ይላሉ። 5ነገር ግን
እነዚህ ሰዎች ሰማያት ከጥንት ጀምሮ
በእግዚአብሔር ቃል ተፈጥረው እንደሚኖሩ፣
መሬትም በውሃ መካከልና በውሃም እንደ
ተሠራች ሆን ብለው ይክዳሉ፤ 6በዚያን ጊዜ
የነበረው ዓለም በውሃ ተጥለቅልቆ ጠፋ።
7በዚያው ቃል ደግሞ አሁን ያሉት ሰማያትና

2፥12 መዝ49፥12፤ ይሁ1፥10
2፥13 ሮሜ13፥13፤ 1ቆሮ11፥20፡21፤ 1ተሰ5፥7፤ ይሁ1፥12
2፥14 ቆላ3፥18፤ ኤፌ2፥3፤ 2ጴጥ3፥16፤ ያዕ1፥8
2፥15 ዘኍ22፥4-20፤ 31፥16፤ ዘዳ23፥4፤ ይሁ1፥11፤ ራእ2፥14
2፥16 ዘኍ22፥21-30
2፥17 ይሁ1፥12፡13
2፥18 ቆላ20፤ 2ጴጥ1፥4፤ ይሁ1፥16
2፥19 ሮሜ6፥16
2፥20 ማቴ12፥45፤ 2ጴጥ1፥2፡11፤ 3፥18
2፥21 ሕዝ18፥24፤ ዕብ6፥4-6፤ 10፥26፡27
2፥22 ምሳ26፥11
3፥1 1ቆሮ10፥14፤ 2ጴጥ1፥13
3፥2 ሉቃ1፥70፤ ሐሥ3፥21፤ ኤፌ4፥11
3፥3 1ጢሞ4፥1፤ 2ጢሞ3፥1፤ 2ጴጥ2፥10፤ ይሁ1፥18
3፥4 ኢሳ5፥19፤ ሕዝ12፥22፤ ማቴ24፥48፤ ማር10፥6፤ ሉቃ17፥30
3፥5 ዘፍ1፥6፡9፤ መዝ24፥2፤ ዕብ11፥3 3፥6 ዘፍ7፥21፡22፤ 2ጴጥ2፥5 3፥7 ቆላ10፥12፤ ማቴ10፥15፤ 2ተሰ1፥7

ሠ2፥13 በአንዳንድ ቅጆች በፍቅር ግብዣቸው ላይ የሚል የለም

2፥15 **የበለዓምን መንገድ**፤ ይህ አንላለጽ በእግዚአብሔር ሕዝብ ትከሻ ላይ ተሁኖ የግል ክብርንና የሀብት ክምችትን የሙጥኝ ብሎ መያዝን ያመለክታል (ከዘኍ 31፥16፤ ከራእ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ፡ ዘኍ 25፥2 እና ማብ ይመ)። ኢግብረገባዊ የወሲብ ግንኙነት፣ ለግል ክብር ሲሉ ላይ ታች ማለትና ገንዘብን ለማግኘት ሲባል መስገብገብ የሐሰት ትምህርት መምህራንና ሰባኪዎች ማንነት መግለጫዎች መሆናቸውን ጴጥሮስ በአጽንዖት ያሳያል።
2፥16 **በሰው ቋንቋ ተናግሮ**፤ ሐዋርያው ጴጥሮስ በብሉይ ኪዳን ላይ ተጽፈው የሚገኙትን ታምራት ግልጽ በሆነ መልክ አምኖ ይቀበላል፤ በዛሬ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙት ሰዎች መካከል ራሳቸውን የሾሙ ሐያሲያን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተጽፈው በሚገኙት ታምራት ላይ ንቀት ያሳያሉ፤ ታምራትን አምነው የሚቀበሉትንም ሰዎች ምንም የማያውቁ ወይም ቂላቂሎች አድርገው ይቈጥራሉ። ይሁን እንጂ እውነተኞች የእግዚአብሔር ልጆች በእግዚአብሔር ያምናሉ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚገኙትንም ታምራት ሁሉ በእምነት ይቀበላሉ። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጸሎትና እምነት በማየት ዛሬም ታምራት እንደሚሠራ ያምናሉ (ዮሐ 6፥2 እና ማብ ይመ)።
2፥19 **ነጻ ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጧቸዋል**፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሚታይበት ገደብ ነጻ መውጣት ይገኛል በማለት ከንቱ ተስፋ የሚሰጠው የሕግ አልባነት መንፈስ፣ በመጨረሻው ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት በኅብረተ ሰብና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየገነነ ይመጣል (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 2ጢሞ 3፥1 እና ማብ ይመ)። ፍጹምነት ያለው የእግዚአብሔር ሕግ ጊዜ ያለፈበትና የግል ማንነትን፣ የግል ብቃትንና ደስታን የሚቀይድ ደንብ ተደርጎ ይቈጠራል። ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ላይ ፍጹም የበላይ አድርገው ሲሾሙ የምግባረ ብልሹነት ሰለባዎች ይሆናሉ (ሮሜ 1፥24፡27 እና ማብ ይመ)።
2፥20 **ካመለጡ በኋላ … ተጠላልፈው**፤ ከቍ 20-22 ያለው ክፍል፣ አንዳንድ የሐሰት ትምህርት መምህራን ከኀጢአት ኀይል ነጻ ወጥተው እንደ ነበርና ከዚያም ድነትን እንደ ቀላል ነገር ቈጥረው እንደ ተዉት በግልጽ ያመለክታል፤ (ከቍ 1፡15 ጋር ያነጻጽሩ)።
3፥4 **«እመጣለሁ» ያለው ታዲያ የት አለ?** በመጨረሻዎቹ ቀናት ማለትም በመጀመሪያውና በሁለተኛው የክርስቶስ ምጽአት ወቅት መካከል፣ የሐሰት ትምህርት መምህራን ክርስቶስ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸውን ሕዝቦችና ዓለምን ለማጥፋት የሚመለስ መሆኑን ይክዳሉ (ከራእ 19፥11-21 ጋር ያነጻጽሩ)።
3፥7 **ለእሳት ተጠብቀዋል**፤ ኀጢአት ሰማያትንና ምድርን የበከለ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር በእሳት ፈጽሞ

ምድር፣ ኀጢአተኞች እስከሚጠፉበት እስከ
ፍርድ ቀን ድረስ ለእሳት ተጠብቀዋል።
8ወዳጆች ሆይ፤ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን
እንደ ሺህ ዓመት፣ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ
ቀን መሆኑን ይህን አንድ ነገር አትርሱ።
9አንዳንድ ሰዎች የዘገየ እንደሚመስላቸው
ጌታ የተሰፋ ቃሉን ለመፈጸም አይዘገይም፤
ነገር ግን ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፣ ሁሉ
ለንስሓ እንዲበቃ ስለ እናንተ ይታገሣል።
10የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ይመጣል፤
በዚያች ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ
ያልፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በእሳት
ይጠፋል፤ ምድርና በእርሷም ላይ ያለ ነገር
ሁሉ ይቃጠላል።[a]
11እንግዲህ ሁሉም ነገር በዚህ ሁኔታ
የሚጠፋ ከሆነ፣ እናንተ እንዴት ዐይነት
ሰዎች ልትሆኑ ይገባችኋል? አዎን፣ በቅድ
ስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት ልትኖሩ
ይገ ባችኋል፤ 12ደግሞም የእግዚአብሔርን
ቀን እየተጠባበቃችሁ መምጫውን
ልታፋጥኑ[b] ይገባል። በዚያን ቀን
ሰማያት በእሳት ተቃጥለው ይጠፋሉ፤
የሰማይም ፍጥረት በታላቅ
ትኵሳት ይቀልጣል። 13እኛ ግን ጽድቅ
የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን።

14ስለዚህ ወዳጆች ሆይ፤ እነዚህን ሁሉ
ነገሮች የምትጠባበቁ ስለ ሆናችሁ፣ ያለ
ነውርና ያለ ነቀፋ ከእርሱ ጋር በሰላም
እንድትገኙ ትጉ። 15የጌታችን ትዕግሥት
እናንተ እንድትድኑ እንደ ሆነ አስቡ፤
እንዲሁም ወንድማችን ጳውሎስ እንደ
ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፤ 16እርሱ
ስለ እነዚህ ነገሮች በመልእክቶቹ ሁሉ
ጽፎአል፤ በመልእክቶቹም ውስጥ በቀላሉ
ለመረዳት የሚያዳግቱ ነገሮች አሉ።
ዕውቀት የጐደላቸውና ጽናት የሌላቸው
ሰዎች ሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት
እንደሚያጣምሙ፣ እነዚህንም ደግሞ ለጥፋ
ታቸው ያጣምማሉ።
17እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፤ ይህን
አስቀድማችሁ ስላወቃችሁ፣ ጸንታችሁ
ከቆማችሁበት መሠረት በዐመፀኞች ስሕተት
ተስባችሁ እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ።
18ነገር ግን በጌታችንና በአዳኛችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ዕውቀት
እደጉ፤ ለእርሱ አሁንም፣ ለዘላለምም
ክብር ይሁን፤ አሜን።

3፥8 መዝ90፥4
3፥9 ዕን2፥3፤ ሮሜ2፥4፤ 1ጢሞ2፥4፤ ዕብ10፥37፤ ራእ2፥21
3፥10 ቍ7፡12፤ ኢሳ34፥4፤ ማቴ24፥35፤ ሉቃ12፥39፤ 2ተሰ1፥7፤ ራእ21፥1
3፥12 ቍ10፤ መዝ50፥3፤ 1ቆሮ1፥7
3፥13 ኢሳ65፥17፤ 66፥22፤ ራእ21፥1
3፥14 1ተሰ3፥13
3፥15 ቍ9፤ ሮሜ2፥4፤ ኤፌ3፥3
3፥16 ቍ2፤ መዝ56፥5፤ ኤር23፥36፤ ያዕ1፥8፤ 2ጴጥ2፥14
3፥17 1ቆሮ10፥12፤ 2ጴጥ2፥7፡18፤ ራእ2፥5
3፥18 ሮሜ3፥24፤ 11፥36፤ 2ጴጥ1፥2፡11፤ 2፥20

[a] 3፥10 በአንዳንድ ቅጆዎች ምድር ወና ትሆናለች ይላል
[b] 3፥12 ወይም የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት በናፍቆት ስትጠብቁ

ያጠፋቸው ዘንድ መስኖአል (ቍ 7፡10፡12)። በኖኅ ዘመን ማዕበል ድንገት እንደ መጣ ሁሉ፣ ይህም ቀን እንዲሁ ሳይታሰብ እንደሚመጣ የተረጋገጠ ነው። እግዚአብሔር ምድርን ለማንጻት ማልቃ መግባቱ ኀጢአትን ለዘላለም ሳይቀጣ እንዲሁ እንደማያልፍ ያመለክታል።

**3፥8 አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፤** እግዚአብሔር ጊዜን የሚያየው ከዘላለም አንጻር ነው (ከመዝ 90፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። "ሺህ ዓመት" በሰው ዘንድ ካለው ግንዛቤ ይልቅ ለእግዚአብሔር የተለየ ሆኖ ይታያል፤ አንድን ጉዳይ ለመፈጸም እኛ ሺህ ዓመት ይወስዳል የምንለውን ጌታ በአንድ ቀን ሊፈጽመው ይችላል፤ ወይም እኛ በአንድ ቀን ተፈጽሞ ልናይ የምንፈልገውን ጉዳይ እርሱ ሺህ ዓመት ሊወስድበት ይችላል።

**3፥9 ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ፤** የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መዘግየት የመንግሥቱ ወንጌል ለዓለም ሁሉ እንዲሰበክ ካለው ዐላማ ጋር የተያያዘ ነው (ማቴ 24፥14)። እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው ወንጌልን እንዲሰማ ይፈልጋል፤ ማንም ሰው ለዘላለም እንዲጠፋ አይፈልግም (1ጢሞ 2፥4፤ ሕዝ 33፥11 እና ማብ፡ ዮና 3፥10 እና ማብ ይመ)። በዚህ እውነት መሠረት ሁሉም ሰው ይድናል ማለት አይደለም፤ አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ጸጋና ድነት አልቀበልም ቢል ጠፍቶ ይቀራልና።

**3፥10 የጌታ ቀን፤** "የጌታ ቀን" ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙት ታማኞቹ በአየር ላይ ይገናኙት ዘንድ፣ ጌታ እነርሱን ለመውሰድ ከሚመለስበት ዕለት ጀምሮ ያለውን ወቅት ያመለክታል (በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንቀቃት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ ይህም አሁን ያለው ሰማይና ምድር ጠፍቶ አዲስ ሰማይና ምድር ሲፈጠር ይደመደማል (ራእ 21—22፤ ኢል 1፥14 እና ማብ፡ ሶፎ 1፥7 እና ማብ፤ 1ተሰ 5፥2 እና ማብ ይመ)። የጌታ ቀን መቼ እንደሚጀምር አይታወቅም፤ ሳይታሰብ ድንገት እውን መሆኑም መለዮው ይሆናል (ማቴ 24፥42፡44 እና ማብ ይመ)።

**3፥11 በቅድስናና በእውነተኛ መንፈሳዊነት፤** እግዚአብሔር በቅርብ ጊዜ ዓለምን ስለሚያጠፋ፣ ጻድቃን ባልሆኑትም ላይ ስለሚፈርድ፣ ከዚህ ዓለም ሥርዐት ወይም በውስጡ ከሚገኘው ነገር ጋር መቈራኘት የለብንም። በሕይወት ጕዟችን ውስጥ ፋይዳችንን፣ ግባችንና ዐላማችን እግዚአብሔርን፣ አዲስ ሰማይንና ምድርን የማግኘት ተስፋን ማእከል ማድረግ አለባቸው (ቍ 13 ይመ፤ በገጽ 1826 ላይ፣ "*የአማኞች መለየት*" በሚልና በገጽ 2000 ላይ፣ "*መቀደስ*" በሚል ርእስና የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

**3፥12 መምጫውን ልታፋጥኑ፤** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ከመምጣቱ በፊት ቤተ ክርስቲያን የሚመጣበትን ጊዜ በማፋጠን ረገድ እንደሚከተለው ልታግዝ ትችላለች፤ (1) አማኞች በዓለም ዙሪያ ሁሉ ለወንጌል ሥርጭትና ለሚስዮናዊ ተግባር ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት (ቍ 9፤ ማቴ 24፥14)፤ (2) በጸሎት፣ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፤ ና" በማለት ዳግም ምጽአቱን በመናፈቅ (ራእ 22፥20 ይመ፤ ከማቴ 6፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**3፥13 አዲስ ሰማይና … እንጠባበቃለን፤** ዕብ 10፥10 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**3፥16 በመልእክቶቹም … ሌሎችን ቅዱሳት መጻሕፍት፤** ጴጥሮስ የጳውሎስ መልእክቶች እንደ ሌሎቹ ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔርና ሥልጣን ያላቸው ናቸው ይላል፤ ይኸውም እንደ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ማለት ነው። ዛሬ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ስንነጋገር፣ ስለ ብሉይና አዲስ ኪዳን መነጋገራችን ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጠው የመጀመሪያ መልእክትና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያከናወነው የማዳን ተግባር ማለት ነው (በገጽ 1941 ላይ፣ "*መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት - አንደኛ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-4)

I. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት (1፥5—2፥28)

(ሀ) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚደረግባቸው መርሖች (1፥5—2፥2)

1. በእግዚአብሔር ዘንድ፣ "ጨለማም .... የለም" (1፥5)
2. በጨለማ ውስጥ ኅብረት የለም (1፥6)
3. በብርሃን ኅብረት (1፥7)
4. ከኃጢአት በመንጻት ረገድ ኅብረት (1፥8—2፥2)

(ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሲደረግ እውን ሆነው የሚታዩ መገለጫዎች (2፥3-28)

1. *መታዘዝ* (2፥3-5)
2. ክርስቶስን *መምሰል* (2፥6)
3. ፍቅር (2፥7-11)
4. ከዓለም *መለየት* (2፥12-17)
5. ለእውነት *ታማኝ መሆን* (2፥18-28)

II. የእግዚአብሔር ልጆች (2፥29—3፥24)

(ሀ) የእግዚአብሔር ልጆች *መለዮዎች* (2፥29—3፥18)

(ለ) የእግዚአብሔር ልጆች ሙሉ እምነት (3፥19-24)

III. የእውነት *መንፈስ* (4፥1-6)

(ሀ) የሐሰትን *መንፈስ መለየት* (4፥1፡3፡5)

(ለ) የእውነትን *መንፈስ ማረጋገጥ* (4፥2፡4፡6)

IV. የእግዚአብሔር ፍቅር (4፥7—5፥3)

(ሀ) ፍቅር ከመለኮት የመነጨ *መሆኑ* (4፥7-10)

(ለ) እግዚአብሔር ለገለጠው ፍቅር የሚሰጥ ተገቢ አጸፋ (4፥11-13፡19-21)

(ሐ) በእግዚአብሔር ፍቅር ጸንቶ *መኖር* (4፥14-16)

(*መ*) የፍቅር ፍጹምነት (4፥17-18)

(*ሠ*) የፍቅር *መታዘዝ* (5፥1-3)

V. ከእግዚአብሔር የተሰጠ *ማረጋገጫ* (5፥4-20)

(ሀ) ዓለምን እንዴት *ማሸነፍ እንደሚቻል* (5፥4-5)

(ለ) ወንጌል የቱን ያህል አስተማማኝ ስለ *መሆኑ* (5፥6-10)

(ሐ) በልጁ አማካይነት የዘላለም ሕይወት ያለ ስለ *መሆኑ* (5፥11-13)

(*መ*) ስለ ጸሎት *መልስ* (5፥14-17)

(*ሠ*) ስለ ሦስት ታላላቅ እውነቶች (5፥18-20)

*መደምደሚያ* (5፥21)

**ጸሐፊ፤** *ዮሐንስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *እውነትና ጽድቅ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *ከ85—95 ዓ.ም.*

*ታሪካዊ ዳራ*

ዮሐንስ ከሚለው ስም ጋር አምስት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተያያዙ ናቸው፤ እነርሱም አንድ የወንጌል መጽሐፍ፣ ሦስት መልእክቶችና የዮሐንስ ራእይ ናቸው። በዚህ መልእክት

ላይ ዮሐንስ ራሱን ባይገልጽም እንኳ፣ በሁለተኛው ምእተ ዓመት የነበሩ ምስክሮች (ለምሳሌ፣ ፒያስ፥ ኢራንዮስ፣ ጠርጥሊያንና የእስክንድርያው ቀለሚንጦስ)፣ ይህ መልእክት ከዐሥራ ሁለቱ የጌታ ኢየሱስ ሐዋርያት በአንዱ ማለትም በዮሐንስ የተጻፈ መሆኑን ያረጋግጣሉ። በአጻጻፍ ስልት፣ በቃላት አመራረጥና በዋና ሐሳብ ረገድ በዮሐንስ መልእክት አንደኛና በዮሐንስ ወንጌል መካከል የሚገኘው ቅርብ ተመሳሳይነት፣ ሁለቱም መጻሕፍት በሐዋርያው ዮሐንስ ተጽፈዋል የሚለውን የጥንት ቤተ ክርስቲያን አስተማማኝ ምስክርነት ያጠንክረዋል (የዮሐንስ ወንጌልን መግቢያ ይመ)።

የዚህ መልእክት ተደራስያን (ተቀባዮች) በስም አልተጠቀሱም፤ በዚህ መልእክት ላይ ሰላምታ የለም፥ የሰዎች ወይም የቦታ ስሞችና ሁኔታዎች ተለይተው አልተመለከቱም። ለዚህ ላልተለመደ የመልእክት አቀራረብ ተቀባይነት ያለው ማብራሪያ፣ ዮሐንስ በቋሚነት ከነበረበት ከኤፌሶን ሆኖ ሐዋርያዊ ኀላፊነትን ተቀብለውባቸው ለነበሩት በእስያ ግዛት ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የጻፈ መሆኑ ነው (ከራእ 1፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚያን ጊዜ የነበሩት ማኅበረ ምእመናን ተመሳሳይ ችግርና ፍላጎት የነበራቸው በመሆኑ፣ ዮሐንስ ተዘዋዋሪ ደብዳቤ በማድረግ ይህን መልእክት ጽፎ ከቃል ሰላምታ ጋር በግል መልእክተኛው በኩል ላከው።

የዚህ መልእክት መነሻ ሐሳብ በክርስቶስ እውን ስለ ሆነው ድነትና በአማኙ ላይ የድነትን አሠራር በተመለከተ የሐሰት ትምህርት ችግር መኖሩ ነው። መልእክቱ ከተጻፈላቸው ጋር ቀደም ሲል የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ጉባኤዎቹ ትተው ሄደዋል (2፥19)፤ ይሁን እንጂ የሐ ሰት ትምህርታቸው ጦስ ማለትም ክርስቲያኖች የዘላለምን ሕይወት ለማግኘታቸው እንዴት ርግጠኞች መሆን እንዳለባቸው ያሠራጩት ሐሳብ የወንጌልን ትምህርት እያጣመመ ነበር። በአስተምህሮ ረገድ የኑፋቄ ትምህርታቸው ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ይክዳል (4፥2-3)፤ በሥነ ምግባር ረገድም የክርስቶስን ትእዛዞች መፈጸም (2፥3-4፤ 5፥3)፣ ከኀጢ አትና (3፥7-12) ከዓለም (2፥15-17) መለየትም ድነትን ለሚያስገኝ እምነት አስፈላጊ አይደሉም በማለት አስተምረዋል (ከ1፥6፤ 5፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

### ዐላማ

ዮሐንስ ይህን መልእክት ሲጽፍ ጣምራ ዐላማ ነበረው፤ እነዚህም (1) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን አስተምህሮአዊና ሥነ ምግባራዊ ስሕተት ማጋለጥና ማውገዝ፤ (2) የዮሐንስ መንፈሳዊ ልጆች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በሚቀበል የታዛዥነት መንፈስ ባለው እምነት አማካይነት (4፥15፤ 5፥3-5:12)፣ በእውነትና በጽድቅ፣ በሙሉ ደስታ (1፥4) የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ እንዲኖራቸው (5፥13) እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ህልዎት ማደሪያ እንዲሆኑ (2፥20፤ 4፥4:13) ጥረት ያደርጉ ዘንድ መምከርና ማሳሰብ ናቸው። ይህ መልእክት የዮሐንስ ወንጌል ማከያ በመሆንም ታስቦ የተጻፈ መልእክት ነው በማለት አንዳንዶች ያምናሉ።

### ቅኝት

በዚህ መልእክት ላይ እምነትና አካሄድ የማይነጣጠሉ ሆነው ተሳስረው ቀርበዋል። ዮሐንስ፣ "የክርስቶስ ተቃዋሚዎች" የሚላቸው (2፥18-22) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የክርስቶስን ማንነትና የቅድስናን አካሄድ በተመለከተ ከሐዋርያዊ ትምህርት እየራቁ ነበር። እንደ ሁለተኛ ጴጥሮስና እንደ ይሁዳ መልእክት፣ አንደኛ ዮሐንስ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን አጥፊ ከሆነው እምነታቸውና አካሄዳቸው ጋር በብርቱ ያወግዛቸዋል፤ ይኰንናቸዋልም (ለምሳሌ 2፥18-19:22-23:26፤ 4፥1:3:5)።

በአወንታዊ መልኩ ሲታይ፣ አንደኛ ዮሐንስ ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ኅብረት ማድረግ ምን ማለት እንደ ሆነ በመግለጽ (ምሳሌ 1፥3—2፥2)፣ አማኞች የዘላለም ሕይወት ያላቸው ለመሆናቸው የሚያረጋግጡባቸውን አምስት ግልጽ መስፈርቶች ያሳያል፤ (1) ስለ ክርስቶስ የተገለጠውን የሐዋርያዊ እውነት መስፈርት (1፥1-3፤ 2፥21-23፤ 4፥2-3:15፤ 5፥1:5:10:20)፤ (2) የክርስቶስን ትእዛዞች የሚጠብቀውን የታዛዥነት መስፈርት (2፥3-11፤ 5፥3-4)፤ (3) የቅድስና አካሄድን መስፈርት፣ ይኸውም ከኀጢአት ተመልሶ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግን (1፥6-9፤ 2፥3-6:15-17:29፤ 3፥1-10፤ 5፥2-3)፤ (4) ለእግዚአብሔርና ለአማኞች ያለን ፍቅር የተን ያህል እንደ ሆነ የሚለካበትን መስፈርት (2፥9-11፤ 3፥10-11: 14:16-18፤ 4፥7-12:18-21) እንዲሁም (5) የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነትን መስፈርት (2፥20:27፤ 4፥13፤ 5፥7-12)። ክርስቲያኖች የእነዚህ የአምስቱ ዘርፎች ፍሬ በሕይወታቸው እውን ሆኖ ሲታይ፣ የዘላለም ሕይወት ያላቸው መሆኑን በሙሉ ልብ ሊያውቁ እንደሚችሉ በማስገንዘብ ዮሐንስ መልእክቱን ይደመድማል።

## ልዩ ገጽታ

አንደኛ የዮሐንስ መልእክትን ልዩ የሚደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ይህ መልእክት ተነጻጻሪ አባባሎችን የሐሳብ መግለጫ መሣሪያ በማድረግና በብርሃንና በጨለማ፣ በእውነትና በውሸት፣ በጽድቅና በኀጢአት፣ በፍቅርና በጥላቻ፣ እግዚአብሔርን በመውደድና ዓለምን በመውደድ፣ በእግዚአብሔር ልጆችና በዲያብሎስ ልጆች መካከል የሚጣጣም ነገር የሌለ መሆኑን በማስገንዘብ የክርስትና ሕይወትን ምንነት ይገልጻል። (2) ቅን አማኞች ሆነን ሳለ ድንገት ኀጢአት ስንሠራ፣ ጌታ ኢየሱስ በአብ ዘንድ ጠበቃ ሆኖ የሚቆምልን (በግሪክ፣ "ጰራቅሊጦስ") መሆኑን በከፍተኛ ደረጃ የሚናገረው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ይህ ብቻ ነው (2፥1-2 ይመ፡ ከዮሐ 14፥16-17:26፤ 15፥26፤ 16፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ)። (3) የመጽሐፉ መልእክት የተመሠረተው ቀድሞ በነበረው በብሉይ ኪዳን መገለጥ ላይ ሳይሆን፣ ሙሉ በሙሉ በሐዋርያዊ ምስክርነት ላይ ነው፤ ይኸውም ብሉይ ኪዳንን የሚመለከት ጥቅስ አለመገኘቱ በጉልህ ይታያል ማለት ነው። (4) አንድ ግልጽ የሆነን ኑፋቄ ለመሻር የተነሣ አስተምህሮተ ክርስቶስ እንደ መሆኑ መጠን፣ የክርስቶስን ትንሣኤ ሳያሠሳ በትሥጉትና በደሙ (ይኸውም በመስቀሉ ማለት ነው) ብቻ ላይ ያተኵራል። (5) ዮሐንስ የተወሰኑ ሠረ ሐሳቦችንና ሐረጎችን ማለትም እንደ፣ "ብርሃን፣" "እውነት፣" "ማመን፣" "መጽናት፣" "ማወቅ፣" "ፍቅር፣" "ጽድቅ፣" "ምስክር፣" "ከእግዚአብሔር የተወለደ፣" እና "የዘላለም ሕይወት" የመሳሰሉትን ሲያብራራ፣ የአጻጻፉ ስልት ቀላልና ድግግሞሽ የሚታይበት ነው።

## አንደኛ ዮሐንስን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ አንደኛ ዮሐንስ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአምስት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1፥1—2፥14 ❑ 2፥15—3፥10 ❑ 3፥11-24 ❑ 4 ❑ 5

### ማስታወሻ

## የሕይወት ቃል

**1** ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው
የነበረውን፣ የሰማነውን፣ በዐይኖቻችን
ያየነውን፣ የተመለከትነውንና እጆቻችን
የዳሰሱትን እንናገራለን። ²ሕይወት ተገለጠ፤
እኛም አይተነዋል፤ እንመሰክርለታለንም።
ራእ 1፥9 በአብ ዘንድ የነበረውን፣ ለእኛም የተገለጠልንን
የዘላለም ሕይወት እንነግራችኋለን፤
³እናንተም ከእኛ ጋር ኅብረት እንዲኖራችሁ፣
ያየነውንና የሰማነውን እንነግራችኋለን፤
ኅብረታችንም ከአብ፣ ከልጁም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጋር ነው። ⁴ደስታችንም[a] ፍጹም
ይሆን ዘንድ ይህን እንጽፍላችኋለን።

## በብርሃን መመላለስ

⁵ከእርሱ የሰማነው ለእናንተም
የምንነግራችሁ መልእክት፣ እግዚአብሔር ብርሃን
ነው፤ ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም፤ የሚል
ነው። ⁶በጨለማ እየተመላለስን ከእርሱ ጋር
ኅብረት አለን ብንል እንዋሻለን፤ እውነትንም
እንኖረውም። ⁷ነገር ግን እርሱ በብርሃን
እንዳለ፣ እኛም በብርሃን ብንመላለስ እርስ
በእርሳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ
ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ[b] ያነጻናል።
⁸ኀጢአት የለብንም ብንል፣ ራሳችንን
እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።
⁹ኀጢአታችንን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን
ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነጻን እርሱ
ታማኝና ጻድቅ ነው። ¹⁰ኀጢአት አልሠራንም
ብንል፣ እርሱን ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤
ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።

**2** ልጆቼ ሆይ፤ ይህን የምጽፍላችሁ
ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤ ነገር ግን

1፥1 ሉቃ24፥48፡ ዮሐ1፥2፡14፡ 19፥35፡ 20፥27፡ ሐሥ4፥20፡ 2ጴጥ1፥16፤ 1ዮሐ4፥14
1፥2 ማቴ25፥46፡ ዮሐ1፥1-4፡ 11፥25፡ 14፥6፡ 15፥27፡ ቲቶ3፥16፡ 1ጴጥ1፥20፡ 1ዮሐ3፥5፡8፡14፡ 11፥25፡ 14፥6፡ 15፥27፡ ቲቶ3፥16፡ 1ጴጥ1፥1፥20፡ 1ዮሐ3፥5፡8
1፥3 ቆላ1፡ 1ቆሮ1፥9
1፥4 ዮሐ3፥29፡ 1ዮሐ2፥11
1፥5 1ጢሞ6፥16፡ 1ዮሐ3፥11
1፥6 ዮሐ3፥19-21፡ 8፥12፡ 2ቆሮ6፥14፡

1፥6 ኤፌ5፥8፡ 1ዮሐ2፥4፡11፡ 4፥20 1፥7 ኢሳ2፥5፡ ዕብ9፥14፡ ራእ1፥5፡ 7፥14 1፥8 ምሳ20፥9፡ ኤር2፥35፡ ዮሐ8፥44፡ ሮሜ3፥9-19፡ ያዕ3፥2፡ 1ዮሐ2፥4 1፥9 ቆላ7፡ መዝ32፥5፡ 51፥2፡ ምሳ28፥13፡ ሚክ7፥18-20፡ ዕብ10፥22 1፥10 ቆላ8፡ ዮሐ5፥38 ዮሐ5፥38፡ 1ዮሐ2፥14፡ 5፥10 2፥1 ቆላ12፥13፥28፡ ሮሜ8፥34፡ 1ተሰ2፥11፡ 1ጢሞ2፥5፡ 1ዮሐ3፥7፡18፡ 4፥4፡ 5፥21

[a] 1፥4 አንዳንዶች ቅጆች *የእናንተ* ይላል
[b] 1፥7 ወይም *ከማንኛውም*

**1፥2 የዘላለም ሕይወት፤** ዮሐንስ የዘላለም ሕይወትን የሚገልጸው በቀጥታ በክርስቶስ የሚገኝ መሆኑን በማሳየት ነው፤ ይህ የዘላለም ሕይወት ሊገኝ የሚችለው በክርስቶስ በማመንና ከራሱ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ኅብረት በማድረግ ነው (ቍ. 2፥6-7፤ 2፥22-25፤ 5፥20)።

**1፥3 ከእኛ ጋር ኅብረት፤** "ኅብረት" (በግሪክ፣ "ኮይኖኒያ") በቁሙ ሲተረጐም፣ "በጋራ ንብረት ማድረግ" ማለት ሲሆን ማካፈልንና አብሮ መካፈልን ያካትታል። ክርስቲያኖች ኅብረት አላቸው፤ ምክንያቱም የጋራ እምነት (ቲቶ 1፥4፤ ይሁ 1፥3)፣ በክርስቶስ የጋራ የእግዚአብሔር ጸጋ (1ቆሮ 1፥9፤ ፊል 1፥7)፣ የመንፈስ ቅዱስ የጋራ ማደሪያ ስለሆኑና (ዮሐ 20፥22፤ ሮሜ 8፥9፡11)፣ የመንፈስ ቅዱስ የጋራ ስጦታዎችና (ሮሜ 15፥27) የጋራ ጠላት ስላላቸው ነው (2፥15-18፤ 1ጴጥ 5፥8)። የአዲስ ኪዳንን የእምነት ትምህርት ከማይቀበሉት ጋር እውነተኛ ኅብረት ሊኖር አይችልም (2ዮሐ 1፥7-11 ይመ፤ ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

**1፥6 ከእርሱ ጋር ኅብረት፤** "በጨለማ መመላለስ" ማለት በኀጢአትና በኢግብረገባዊ ደስታ መኖር ማለት ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች፣ "ከእርሱ ጋር" ይኸውም ከጌታችን ጋር፣ "ኅብረት" የላቸውም፤ ከዚህ የተነሣ ከእግዚአብሔር አልተወለዱም ማለት ነው (ከ3፥7-9፤ ከዮሐ 3፥19፤ ከ2ቆሮ 6፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያላቸው የእግዚአብሔርን ጸጋ የሕይወታቸው ልምምድ ያደርጋሉ፤ በእርሱም ፊት የቅድስና ሕይወት ይኖራሉ (ቍ. 7፤ 2፥4፤ 3፥10)።

**1፥7 በብርሃን ብንመላለስ፤** ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በቃሉ ላይ በተገለጠው መሠረት ማመንና በቃልና በተግባር ቃሉን ለመከተል በጸጋው አማካይነት ቅንና የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ ማለት ነው። "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻል" ማለት አማኙ በማያቋርጥ የዕድሜ ልክ መቀደስ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ያመለክታል፤ እኛም ድንገት ከሚያጋጥመን ኀጢአት በክርስቶስ ደም በማያቋርጥ መንጻት ውስጥ ማለፍ አለብን ማለት ነው። ዮሐንስ በብርሃን ብንመላለስ ስለሚል፣ ከዚህ ላይ የሚናገረው ሆን ተብሎ ስለሚሠራ ኀጢአት ላይሆን ይችላል፤ ይህ የማያቋርጥ መንጻት ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ኅብረት እንዲኖረን ያስችለናል (በገጽ 2000 ላይ፣ "*መቀደስ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**1፥8 ኀጢአት የለብንም ብንል፤** ዮሐንስ ኀጢአት በእኛ ውስጥ ያለ የማንነታችን አካል መሆኑን በአጽንዖት ለማሳየት ሲል፣ "ብንበድል" የሚለውን ግስ ትቶ፣ "ኀጢአት" የሚለውን ስም ተገልግሎበት ይገኛል። (1) ምናልባት ዮሐንስ ኀጢአት የሰው ማንነት አካል ሆኖ ወይም ኀይል ያለው ሆኖ በሰው ዘንድ የለም፤ ወይም ክፉ ሥራቸው እንደ እውነቱ ከሆነ ኀጢአት አይደለም ከሚሉት ጋር ሳይከራከር አልቀረም። ዛሬም ቢሆን በእኛ ዘንድ ኀጢአት መኖሩን በሚክዱ ክፉትንም የሁኔታ፣ የሥነ ልቡና ወይም የማኅበራዊ መንሥኤ አድርገው በሚተረጕሙት ዘንድ ኑፋቄ አለ (ሮሜ 6፥1 እና ማብ፤ 7፥9-11 እና ማብ ይመ)። (2) አማኞች ኀጢአታዊ ተፈጥሮ በሕይወታቸው ውስጥ የዘወትር ባላጋራ መሆኑን በመገንዘብ፣ በውስጣቸው በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ክፉ ሥራውን ማምከን አለባቸው (ሮሜ 8፥13፤ ገላ 5፥16-25)።

**1፥9 ኀጢአታችንን ብንናዘዝ፤** ኀጢአተኞች መሆናችንን ማመን አለብን፤ ከዚያም እግዚአብሔር ይቅርታንና መንጻትን እንዲሰጠን መለመን ይኖርብናል፤ ከዚህ የተነሣ የሚገኙት ሁለት ውጤቶችም፣ (1) ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ማግኘት፥ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ (2) የቅድስና ሕይወት ለመኖር ከበደልና አጥፊ ከሆነ የኀጢአት ኀይል መንጻት ናቸው (መዝ 32፥1-5፤ ምሳ 28፥13፤ ኤር 31፥34፤ ሉቃ 15፥18፤ ሮሜ 6፥2-14)።

**1፥10 ኀጢአት አልሠራንም ብንል፤** ኀጢአት ክፉ ሥርተን እናውቅም፣ ከኀጢአት ሁሉ የሚያነጻው የክርስቶስ ሞትም አያስፈልገንም ብንል፣ እግዚአብሔርን ሐሰተኛ ለማድረግ እንደ መሞከር ነው (ከሮሜ 3፥23 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥1 ኀጢአት እንዳትሠሩ ነው፤** ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ኀጢአት የመሥራት ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ ያላቸው መሆናቸውን ዮሐንስ ያምናል። ይሁን እንጂ ክርስቲያን ኀጢአት መሥራት አለበት ብሎ አያስተምርም፤ በዚህ ፈንታ ክርስቲያን ኀጢአት ሳይሠራ መኖር እንዳለበት ይመክራል (ከሮሜ 6፥15

ማንም ኀጢአት ቢሠራ፣ በአብ ዘንድ ጠበቃ
አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ
ነው። 2እርሱም የኀጢአታችን ማስተስረያ
ነው፤ ይኸውም[a] ለዓለም ሁሉ ኀጢአት
እንጂ ለእኛ ብቻ አይደለም።
3ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃች
ንን በዚህ ርግጠኞች እንሆናለን። 4"እርሱን
ዐውቃለሁ" እያለ ትእዛዙን የማይፈጽም
ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ
የለም። 5ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣
በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር[b] በእርሱ ፍጹም
ሆኖአል። በእርሱ መሆናችንን የምናውቀው
በዚህ ነው፤ 6ማንም በእርሱ እኖራለሁ
1ዮሐ 3፡9-18 የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ
ይገባዋል።
7ወዳጆች ሆይ፤ የምጽፍላችሁ፣
ከመጀመሪያ የነበራችሁን የቈየውን ትእዛዝ
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አይደለም፤ የቈየው
ትእዛዝ የሰማችሁት ቃል ነው። 8በሌላ
በኩል የምጽፍላችሁ ጨለማው ዐያለፈና
እውነተኛው ብርሃን እየበራ ስለሆነ፣
በእርሱም፣ በእናንተም ዘንድ እውነት
የሆነውን አዲስ ትእዛዝ ነው። 9በብርሃን
አለሁ የሚል፣ ወንድሙን ግን የሚጠላ
አሁንም በጨለማ ውስጥ አለ። 10ወንድሙን
የሚወድ በብርሃን ይኖራል፤ በእርሱም
ዘንድ የመሰናከያ ምክንያት የለውም። 11ነገር
ግን ወንድሙን የሚጠላ በጨለማ ውስጥ
ነው፤ በጨለማ ይመላለሳል፤ ጨለማው
ስላሳወረውም የት እንደሚሄድ አያውቅም።

12ልጆች ሆይ፤
ኀጢአታችሁ ስለ ስሙ
ተሰርዮላችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
13አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ጐበዛዝት ሆይ፤ ክፉውን
አሸንፋችኋልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ልጆች ሆይ፤
አብን ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
14አባቶች ሆይ፤
ከመጀመሪያ ያለውን እርሱን
ዐውቃችሁታልና፣
እጽፍላችኋለሁ።
ጐበዛዝት ሆይ፤
ብርቱዎች ስለሆናችሁ፣
የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ
ስለሚኖር፣
ክፉውንም ስላሸነፋችሁ፣
ጽፍላችኋለሁ።

## ዓለምን አትውደዱ

15ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን
ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም
ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ
የለም፤ 16ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ:-
የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ
ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ
አይደለም። 17ዓለምና ምኞቱ ያልፋሉ፤

2፡2 ማቴ1፡21፤ ዮሐ3፡17፤ ሮሜ3፡25፤ 1ዮሐ4፡10፤ ሚክ7፡18-20
2፡3 ቍ4፡5፤ ዮሐ14፡15፤ 1ዮሐ3፡24፤ 4፡13፤ 5፡2
2፡4 ቍ3፤ ቲቶ1፡16፤ 1ዮሐ1፡6፡8፤ 3፡6፤ 4፡7፡8
2፡5 ቍ3፤ ዮሐ14፡15፤ 1ዮሐ4፡12
2፡6 ማቴ11፡29
2፡7 ቍ24፤ 1ቆሮ10፡14፤ 1ዮሐ3፡11፡23፤ 4፡21፤ 2ዮሐ1፡5፡6
2፡8 ዮሐ19፤ 13፡34፤ ሮሜ13፡12፤ ኢሳ58፤ 1ተሰ5፡5፤ ዕብ10፡25
2፡9 ቍ11፤ ዘሌ19፡17፤ 1ዮሐ1፡5፤ 3፡10፡15፡16፤ 4፡20፡21
2፡10 ቍ11፤ መዝ119፡165፤ 1ዮሐ3፡14
2፡11 ቍ9፤ ዮሐ11፡9፤ 12፡35፤ 1ዮሐ1፡6
2፡12 ቍ1፤ 1ዮሐ3፡23
2፡13 ቍ1፡14፤ ማቴ5፡37፤ ዮሐ1፡1፤ 16፡33
2፡14 ቍ13፤ ዮሐ1፡1፤ 5፡38፤ ኤፌ6፡10፤ ዕብ4፡12፤ 1ዮሐ1፡10
2፡15 ሮሜ12፡2፤ ያዕ4፡4 2፡16 ዘፍ3፡6፤ ምሳ27፡20፤ ሮሜ13፡14፤ ኤፌ2፡3 2፡17 ማቴ12፡50፤ ዕብ12፡27

[a] 2፡2 ኀጢአታችንን አስወግዶ የእግዚአብሔርን ቍጣ ከእኛ የሚያርቅ እርሱ ነው ይኸውም የእኛን ኀጢአት ብቻ ሳይሆን ማለትም ነው።
[b] 2፡5 ወይም ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ማለት ነው።

እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ፤ ከ1ተሰ 2፡10 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)። በኀጢአት ለሚሰናከሉት ሁሉ ያለው መፍትሄ ያን ኀጢአት መናዘዝና መተው ነው (1፡9 እና ማብ ይመ)። የኀጢአት ይቅርታ ዋስትና የሚገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደምና (ቍ 2፤ 1፡7) ጌታችን በሰማያዊ አገልግሎቱ ለእኛ፣ "በአብ ዘንድ" ባለው ጥብቅና (በግሪክ፡ "ጰራቅሊጦስ") ነው። ኢየሱስ ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት የሚማልደው፣ ስርየትን በሚያስገኝ ሞቱ፤ እኛ ንስሓ በመግባታችንና በእርሱም ላይ ባለን እምነት ምክንያት ነው (ከሮሜ 8፡34፤ ከዕብ 7፡25 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ዮሐ 3፡15 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1280 ላይ፣ ***"የምልጃ ጸሎት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

2፡2 **የኀጢአታችን ማስተስረያ**፤ ኢየሱስ፣ "የኀጢአታችን ማስተስረያ" ሆኖ የበደላችንን ቅጣት በመቀበል በኀጢአት ላይ የመጣውን የእግዚአብሔርን ጻድቅ ፍርድ ተቀበለ። ከእንግዲህ ይቅርታ በዓለም ውስጥ ለእያንዳንዱ ሰው ቀርቦለታል፤ በንስሓና በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚመለሱትም ተቀብለውታል፤ ይቀበሉታልም (4፡9፡14፤ ዮሐ 1፡29፤ 3፡16፤ 5፡24 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1735 ላይ፡ ***"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

2፡4 **ትእዛዙን የማይፈጽም**፤ ዮሐንስ የጸጋንና የድነትን አስተምህሮ በትክክል ካልተረዱት ጋር ይታገል ነበር። ለአንድ ክርስቲያን የኀጢአትን መንገድ የሚከተል ሕይወትን መተው ሲያደርስ የሚሆን እንጂ (አማራጭ እንጂ) ግዴታ አይደለም ብለው የሚከራከሩትንና እምነት በሥራ የሚገለጽ መሆኑን ዘንግተው በከንቱ እምነት ላይ ብቻ የሚያተኵሩትን አስተማሪዎች ዮሐንስ ይቃወማል። (1) እነዚህ መምህራን አንድ ሰው አዳኝ በሆነ ግንኙነት እግዚአብሔርን በሚገባ "ሊያውቅ" ይችላል፤ ይህም እንደ ተጠበቀ ሆኖ ለእግዚአብሔር ፈቃድና ለትእዛዞቹ ደንታ ቢስ ሊሆን፣ ዐልፎ ተርፎም እነዚህን ትእዛዞች ሊተላለፋቸው ይችላል በማለት በአደባባይ ተናገሩ (ዮሐ 17፡3 እና ማብ ይመ)። (2) እንዲህ ያለውን ትምህርት ቁም ነገር ብለው የያዙት ሁሉ ሐሰተኞች መሆናቸውንና በእነርሱም ዘንድ የእግዚአብሔር እውነት የሌለ መሆኑን ዮሐንስ ገለጸ። ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ዐልፎ ሳይሰጥ በክርስቶስ አምነን ጽድቅን አግኝተናል ማለት ከንቱ እንደሚሆን የታወቀ ነው።

2፡10 **ወንድሙን የሚወድ**፤ ዮሐንስ 13፡34-35 እና ማብራሪያዎቻቸውን ይመልከቱ።

2፡15-16 **ዓለምን**፤ በገጽ 2022 ላይ፣ ***"ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

# ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት

*1ዮሐ 2፥15-16 "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማናቸውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ፣ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፦ የሥጋ ምኞች፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም።"*

---

"ዓለም" (በግሪክ፣ "ኮስሞስ") የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ የሚያመለክተው፣ በሰይጣን የሚመራውን ከእግዚአብሔር ግኝኑነት ነጻ ሆኖ የሚኖረውን ሰፊውን የዚህን ዓለም ሥርዐት ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው የታወቀውን ክፋውን፣ ኢግብረገባዊውንና ኀጢአተኛ የሆነውን የዓለምን ደስታ ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርና የመገለጡ ተቃዋሚ የሆነውን ወይም ለእግዚአብሔርና ለመገለጡ ደንታ ቢስ የሆነውን፣ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነት ውጭ በመሆን በሰው ዘር የንግድ ድርጅት ሁሉ የሚሠራውን የዐመፅን መንፈስ ጭምር ነው፤ በዚህ ዘመን እግዚአብሔርን፣ ሕዝቡን፣ ቃሉንና ጻድቅ መለኪያዎቹን (መንገዶቹን) ለመቃወም፣ ሰይጣን የዓለምን ሐሳብ፣ ግብረገብን፣ ፍልስፍናን፣ ሥነ ልቦናን፣ ምኞትን፣ መንግሥትን፣ ባህልን፣ ትምህርትን፣ ሳይንስን፣ ኪነጥበብን፣ ልዩ ልዩ መድኀኒቶችን፣ ሙዚቃን፣ ምጣኔ ሀብታዊ ሥርዐትን፣ መዝናኛን፣ የመገናኛ ብዙኀንን፣ ሃይማኖቶችን፣ ስፖርትን፣ ግብርናን፣ ወዘተ መሣሪያ አድርጎ ይጠቀማል (ማቴ 16፥26፤ 1ቆሮ 2፥12፤ 3፥19፤ ቲቶ 2፥12፤ 1ዮሐ 2፥15-16)። ለምሳሌ ሰይጣን የሕክምናን ሙያ ገና በማሕፀን ያሉትን ሕፃናት ለመግደል፣ ግብርናን ደግሞ ሕይወትን የሚያጠፉ ዕፆችን ማለትም አልኮልንና ልዩ ልዩ አደንዛዥ ዕፆችን ለማምረት፣ የትምህርት ሥርዐትንም ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለውን ሰው ሠራሽ የሆነውን ፍልስፍናን ለማፋመድ፣ የመዝናኛ መሣሪያንም የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ሥርዐት ለማጥፋት ይጠቀማል። ከንግድ ድርጅቶች በስተጀርባ ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ጋር ተቃራኒ ሆኖ አንዳንዶቹን በብዛት፣ ሌሎቹን ደግሞ በመጠኑ የሚጠቀም መንፈስ ወይም ኀይል ያለ መሆኑን አማኞች ልብ ይሉ ዘንድ ይገባል። በመጨረሻም፣ "ዓለም" ሲባል ሰው ሠራሽ የሃይማኖት ሥርዐትን፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ዓለማዊ የሆነውን ወይም በለብታ ደረጃ የሚገኙ ክርስቲያን ተብየ ድርጅቶችንና አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ያካትታል።

(1) ሰይጣን (ማቴ 4፥10 እና ስለ ሰይጣን የተሰጠውን ማብራሪያ ይመ) የአሁኑ ዓለም ሥርዐት አምላክ ነው (ዮሐ 12፥31 እና ማብ፤ 14፥30፤ 16፥11፤ 2ቆሮ 4፥4፤ 1ዮሐ 5፥19 ይመ)። ከክፉ መናፍስት ሰራዊቱ ጋር በመሆን ዓለምን ይቈጣጠራል (ዳን 10፥13፤ ሉቃ 4፥5-7፤ ኤፌ 6፥12-13 ይመ፤ በገጽ 1499 ላይ፣ "በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ሰይጣን የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ጠላቶች በሆኑት ዓለምን በፖለቲካ፣ በባህል፣ በምጣኔ ሀብትና በሃይማኖት ረገድ ዓለምን አደራጅቶአል (ዮሐ 7፥7፤ 15፥18፤ ያዕ 4፥4፤ 1ዮሐ 2፥16፥18)፤ ይህም ዓለም ክፋቱን ለሚያጋልጥበት ለእግዚአብሔር እውነት እምቢተኛ ሆኖአል (ዮሐ 7፥7)።

(3) ዓለምና እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ለየቅል የሆኑ አካላት ናቸው፤ ዓለም በሰይጣን ግዛት ሥር ነው (ዮሐ 12፥31 እና ማብ ይመ)፤ ቤተ ክርስቲያን ግን ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር ሀብት ናት (ኤፌ 5፥23-24፤ ራእ 21፥2 ይመ፤ በገጽ 1782 ላይ፣ "ሦስት ዐይነት ሰዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ስለዚህ አማኞች ራሳቸውን ከዓለም መለየት አለባቸው (በገጽ 1826 ላይ፣ "የአማኞች መለየት" በሚል ርእስና በገጽ 2000 ላይ፣ "መቀደስ" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)።

(4) አማኞች በዚህ ዓለም ሲኖሩ መጻተኞችና ባዕዳን ናቸው (ዕብ 11፥13፤ 1ጴጥ 2፥11)። (ሀ) ከዓለም መውጣት አለባቸው (ዮሐ 15፥19)፤ ዓለምን መምሰል የለባቸውም (ሮሜ 12፥2 እና ማብ ይመ)፤ ዓለምን መውደድ የለባቸውም (1ዮሐ 2፥15)፤ ዓለምን ማሸነፍ አለባቸው (1ዮሐ 5፥4)፤ የዓለምን ክፋት መጥላት አለባቸው (ዕብ 1፥9 እና ማብ)፤ ለዓለምና የዓለም ለሆነው ነገር ሙት መሆን አለባቸው (ገላ 6፥14)፤ የዓለም ከሆነው ነገር ትድግናን ማግኘት አለባቸው (ቈላ 1፥13-14)። (ለ) ዓለምን መውደድ (ከ1ዮሐ 2፥15 ጋር ያነጻጽሩ) ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ይበክላል፤ ወደ መንፈሳዊ ጥፋትም ያደርሳል። ዓለምንና አብን በአንድ ጊዜ መውደድ ከቶ አይቻልም (ማቴ 6፥24፤ ሉቃ 16፥13 ይመ፤ ያዕ 4፥4 እና

ማብ ይመ)። ዓለምን መውደድ ማለት ከፋይዳው፣ ከፍላጎቱ፣ ከመንገዱና ከደስታው ጋር ኅብረት ማድርግና ለእነዚህ ማሸርገድ ማለት ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን በሚጠላው አካልና የእግዚአብሔር ጠላት በሆነው ኀይል መደሰት ወይም ሐሤት ማድረግ ማለት ነው (ሉቃ 23፥35 እና ማብ ይመ)። ርግጥ ነው፤ "ዓለምና" "ምድር" ሁለቱ ተመሳሳዮች አለመሆናቸውን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር የፈጠረውን ምድር ማለትም ተፈጥሮን፣ ተራሮችን፣ ጫካዎችንና የመሳሰሉትን እንድንጠላ አያዝም።

(5) በ1ዮሐ 2፥16 መሠረት የኀጢአተኛ ዓለም ሦስት ገጽታዎች ከእግዚአብሔር ጋር ጕሉሕ የሆነ ጠላትነት ይፈጥራሉ፤ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤ (ሀ) "የሥጋ ምኞት" ይህም ንጹሕ ያልሆነ ምኞት፣ ኀጢአተኛ ደስታንና የሥጋ ርካታን ለማግኘት ሲሉ መሯሯጥ (1ቆሮ 6፥18፤ ፊል 3፥19፤ ያዕ 1፥14)። (ለ) "የዐይን አምሮት" ይህም እግዚአብሔር የከለከለውን ግን ዐይንን የሚማርከውን መመኘት ወይም መጐመጀት ይመለከታል፤ ኀጢአተኛ የሆነ ርካታን የሚሰጠውን በዐይን መከታተልንም ያካትታል (ዘፀ 20፥17፤ ሮሜ 7፥7)። በዚህ በሠለጠነ ዓለም ውስጥ የወሲብ ፍላጎትን የሚያነሣሡ ጽሑፎችን፣ ሥዕሎችንና የመሳሰሉትን፣ ዐመፅን፣ ቅድስና የሌለበትንና ኢግብረገባዊ የሆነውን ነገር በመድረክ ላይ የማየት አምሮትን፣ በቴሌቪዥን ወይም በፊልም ላይ በማየት ወይም መጽሔት በማንበብ ራስን ለማዝናናት ያለውን ፍላጎትም ያካትታል (ዘፍ 3፥6፤ ኢያ 7፥21፤ 2ሳሙ 11፥2፤ ማቴ 5፥28)። (ሐ) "የኑሮ ትምክሕት" ይህም እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን የማይቀበል ወይም ቃሉን የመጨረሻ ባለሥልጣን አድርጎ የማያምን መንፈስ ሲሆን፣ ትዕቢተኛና ምሉዕ በኩለሄ የሆነ መንፈስ ማለት ነው። ራስን ለመካብና የሕይወት ማእከል ለማድረግ የሚሻም መንፈስ ነው (ያዕ 4፥16)።

(6) አማኞች የዓለም ክፉ ሥርዐት ተካፋዮች ከሆኑት ጋር የጠበቀ ኅብረት ማድረግ የለባቸውም (ማቴ 9፥11 እና ማብ፤ 2ቆሮ 6፥14 እና ማብ ይመ)፤ ኀጢአታ ቸውን በግልጽ ማውገዝ አለባቸው (ዮሐ 7፥7 ይመ፤ ኤፌ 5፥11 እና ማብ ይመ)፤ ዓለማውያን ለሆኑት ብርሃንና ጨው መሆን አለባቸው (5፥13-14)፤ ይወዷቸውም ዘንድ ይገባል (ዮሐ 3፥16)፤ ወደ ክርስቶስ ያመጧቸውም ዘንድ መጣር አለባቸው (ማቴ 16፥15፤ ይሁ 1፥22-23)።

(7) እውነተኛ ክርስቲያን በዓለም ሲኖር ችግር (ዮሐ 16፥2-3)፣ ጥላቻ (15፥19)፣ ስደት (ማቴ 5፥10-12) እና ሥቃይ (ሮሜ 8፥22-23፤ 1ጴጥ 2፥19-21) ይደርስበታል። የዓለምን ማታለያ ነገር መሣሪያ በማድረግ፣ እግዚአብሔር በክርስቲያን ውስጥ ያስቀመጠውን ሕይወት እንዳይኖር ለማድረግ ሰይጣን የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋል (2ቆሮ 11፥3፤ 1ጴጥ 5፥8)።

(8) የዓለም ሥርዐት ጊዜያዊ ነው፤ እግዚአብሔር ያጠፋዋል (ዳን 2፥34-35፥44፤ 1ቆሮ 7፥31፤ 2ተሰ 1፥7-10፤ 2ጴጥ 3፥10 እና ማብ፤ ራእ 18፥2 ይመ)፤ ይህ የዓለም ሥርዐት አሁንም እንኳ በማለፍ ላይ ይገኛል (1ዮሐ 2፥17)።

1ዮሐ 5፡4-5 የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን
ለዘላለም ይኖራል።

## ከክርስቶስ ተቃዋሚዎች መጠንቀቅ

18 ልጆች ሆይ፤ ይህ የመጨረሻው ሰዓት
ነው፤ እንደሰማችሁትም የክርስቶስ ተቃዋሚ
ይመጣል፤ አሁን እንኳ ብዙ የክርስቶስ
ተቃዋሚዎች መጥተዋል፤ የመጨረሻው
ሰዓት እንደሆነ የምናውቀውም በዚህ ነው።
19 ከእኛ መካከል ወጡ፤ ይሁን እንጂ ከእኛ
ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገን ቢሆኑማ ኖሮ
ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር። ነገር ግን
ሁሉም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ ይታወቅ
ዘንድ ከእኛ ተለዩ።
20 እናንተ ግን ከእርሱ ከቅዱሱ፣
ቅባት አላችሁና፤ ሁላችሁም እውነትን[ሠ]
ታውቃላችሁ። 21 እኔ የምጽፍላችሁ እውነትን
ስለማታውቁ አይደለም፤ ነገር ግን እውነትን
ስለ ምታውቁትና ከእውነት ምንም ውሸት
ስለማይወጣ ነው። 22 ክርስቶስ አይደለም ብሎ
ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ሐሰተኛ ማነው?
ይህ አብንና ወልድን የሚክደው የክርስቶስ
ተቃዋሚ ነው። 23 ወልድን የሚክድ ሁሉ
አብ የለውም፤ ወልድን የሚያምን ሁሉ
አብም አለው።
24 ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ
ውስጥ ይኑር፤ ከመጀመሪያ የሰማችሁት
በእናንተ ውስጥ ቢኖር፣ እናንተም በወልድና
በአብ ትኖራላችሁ። 25 ይህ እርሱ የሰጠን
ተስፋ የዘላለም ሕይወት ነው።
26 ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን
ጽፌላችኋለሁ። 27 እናንተ ግን ከእርሱ
የተቀበላችሁት ቅባት በውስጣችሁ
ይኖራልና፤ ማንም እንዲያስተምራችሁ
አያስፈልጋችሁም፤ ነገር ግን እውነት እንጂ
ሐሰት ያልሆነው የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉም
ነገር እንደሚያስተምራችሁ፣ ያም እውነት
እንጂ ሐሰት እንዳልሆነ፣ እናንተንም
እንዳስተማራችሁ በእርሱ ኑሩ።

## የእግዚአብሔር ልጆች

28 እንግዲህ ልጆች ሆይ፤ እርሱ ሲገለጥ
ድፍረት እንዲኖረን፣ በሚመጣበትም ጊዜ
በፊቱ እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።
29 እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣
ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ
ተወለደ ታውቃላችሁ።
3 1 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን እንድንጠራ
አብ አትረፍርፎ ያፈሰሰልን ፍቅር

2፡18 ቍ22፤ ሮሜ13፡11፤ 1ዮሐ4፡1፡3፤ 2ዮሐ1፡7
2፡19 ሐሥ20፡30፤ 1ቆሮ11፡19
2፡20 ቍ27፤ ኤር 31፡34፤ ማቴ13፡11፤ ማር1፡24፤ ዮሐ14፡26፤ 2ቆሮ1፡21
2፡21 2ጴጥ1፡12፤ ይሁ1፡5
2፡22 1ዮሐ4፡3፤ 2ዮሐ1፡7
2፡23 ዮሐ8፡19፤ 14፡7፤ 1ዮሐ4፡15፤ 5፡1፤ 2ዮሐ1፡9
2፡24 ቍ7፤ ዮሐ14፡23፤ 15፡4፤ ዮሐ1፡3፤ 2ዮሐ1፡9
2፡25 ማቴ25፡46
2፡26 1ዮሐ3፡7
2፡27 ቍ20፤ ዮሐ15፡4፤ 1ቆሮ2፡12
2፡28 ቍ1፤ ኤፌ3፡12፤ ቈላ3፡4፤ 1ተሰ2፡19፤
2፡28 ትዮሐ3፡2 2፡29 ዮሐ1፡13፤ 1ዮሐ3፡7
3፡1 ቍ2፡10፤ ዮሐ1፡12፤ 3፡16፤ 15፡21፤ 16፡3

ሠ2፡20 አንዳንድ ቅጆች፣ *እናንተ ሁሉንም ነገር ታውቃላችሁ* ይላሉ።

---

**2፡18 ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች፤** *የዘመኑ መጨረሻ ሲቃረብ የክርስቶስ ተቃዋሚ ወይም ሐሰተኛ* ክርስቶስ *ይመጣል፤ የሚመጣውም ዓለምን ለመግዛትና* በክርስቶስና በአዲስ ኪዳን እምነት ላይ *የሚካሄደውን ታላቅ ዐመፅ ለመምራት ነው (ራእ* 13፡1፡8፡18 እና *ማብራሪያዎቹ፤* 19፡20፤ 20፡10 *ይመ፤* እንዲሁም በገጽ 1913 ላይ፣ «*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ *ይመ*)። ይሁን እንጂ ዮሐንስ፣ «ብዙ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች» አሁንም ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተዋል ይላል። እነዚህ ዓለምንና በነጢአት የተሞላውን ደስታ የሚወዱ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ አማኞች ሲሆኑ፣ ራሳቸውን የክርስቶስና የጽድቁ ተቃዋሚዎች አድርገው በማቆም ወንጌልንና የወንጌልን መልእክት የሚያጣምሙ ናቸው።

**2፡19 ከእኛ መካከል ወጡ፤** የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ከእውነተኛ አማኞች ኅብረት ከተለዩ፣ አዳኝ የሆነ ኅብረት ከክርስቶስ ጋር አልነበራቸውም ማለት ነው። ይህም ሁለት ሐሳብ ነገሮችን ያስከትላል፤ (1) ከመጀመሪያው እውነተኛ አማኞች ከቶ አልነበሩም ማለት ነው፤ ወይም (2) አንድ ጊዜ ከክርስቶስ ጋር አዳኝ የሆነ ኅብረት ነበራቸው፤ በኋላ ግን በክርስቶስ የነበራቸውን እምነት ትተውታል ማለት ነው (በገጽ 1962 ላይ፣ «*ክሕደት*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ *ይመ*)።

**2፡20 ቅባት፤** አማኞች ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅባት ይቀበላሉ፤ ይኸውም መንፈስ ቅዱስን ማለት ነው (ከ2ቆሮ 1፡21-22 ጋር *ያነጻጽሩ*)። በመንፈስ ቅዱስ፣ እውነትን እናውቃለን (ቍ 27 እና ማብ *ይመ*)።

**2፡24 ከመጀመሪያ የሰማችሁት፤** አማኞች በክርስቶስ የሚጸኑትና ድነትን ተመክሮአቸው የሚያደርጉት የክርስቶስንና የሐዋርያትን ትምህርት አክብረው እስከ ጠበቁ ድረስ ነው (ኤፌ 2፡20 እና ማብ *ይመ*)። ይህም ሁለት ነገርን ልብ እንድንል ያሳስባል፤ (1) የአዲስ ኪዳንን እምነት የመጀመሪያው ወንጌል መተው ማለት መንፈሳዊ ሞት ነው፤ አማኙንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ይለያል (ከገላ 1፡6-8፤ 5፡1-4 ጋር *ያነጻጽሩ*)። አማኞች የአዲስ ኪዳንን ትምህርት ምንጊዜም አጥብቀው ይይዙ ዘንድ ይበጃል በሚሉት ሥነ መለኮት ረገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆን ይኖርባቸዋል። (2) በክርስትና እምነት ውስጥ የማይገኘውን አዲስ ትምህርት መቃወም ይህን አዲስ ትምህርት ለሚያስተምሩት አስተማሪዎች ጆሮን መስጠት ምንጊዜም አደገኛ ነው (ከይሁ 1፡3 ጋር *ያነጻጽሩ*)። ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናትና ከቃሉ ጋር በጥብቅ መቈራኘት እጅግ አስፈላጊ ነው፤ ነፍሳችንና ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታችን የተመሠረተው በእርሱ ላይ ነው።

**2፡27 የእርሱ ቅባት ... እንደሚያስተምራችሁ፤** ወደ እውነት እንዲደርሱ ይመራቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ ቅባት (ይኸውም መንፈስ ቅዱስ) ተሰጥቶአቸዋል ዮሐ (14፡26፤ 16፡13)። አማኞችን መንፈስ ቅዱስ የቃሉን የቤዛነት እውነት ይረዱ ዘንድ የሚያግዛቸው በክርስቶስ እስከ ጸኑ ድረስና የእግዚአብሔርንም ቃል እስካነበቡ ድረስ፣ ነው። (1) አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔርን እውነት ሊያጠኑና ሊያውቁ ይችላሉ፤ እርስ በርስ በመማርና በመመካከርም አንዱ ከሌላው ይማራል (ማቴ 28፡20፤ ኤፌ 3፡18፤ ቈላ 3፡16)። (2) ስለዚህ አማኞች ከአስተምህሮአዊ ስሕተት የሚጠበቁባቸው ሁለት ምሽጎች አሏቸው፤ እነርሱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥና (ከቍ 24 ጋር *ያነጻጽሩ*) መንፈስ ቅዱስ ናቸው። (3) አማኞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ሌላ አስተምህሮ የሚያስተምሯቸው መምህራን አያስፈልጓቸውም። ሐዋርያው ዮሐንስ፣ «*ማንም እንዲያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም*» ሲል ይህንኑ ማስረዳቱ ነው።

ምንኛ ታላቅ ነው! እኛም እንዲሁ ልጆቹ
ነን። ዓለም እኛን የማያውቀንም እርሱን
ስላላወቀው ነው። 2ወዳጆች ሆይ፤ እኛ አሁን
የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን
ይሀ እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። እርሱ
፥14- በሚገለጥበት[c] ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን
15 እንደ ምንመስል እናውቃለን። 3በእርሱ
ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ
እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል።
4ኀጢአት የሚያደርግ ሁሉ ዐመፅን ያደ
ርጋል፤ ኀጢአትም ዐመፅ ነው። 5እርሱ
ኀጢአትን ሊያስወግድ እንደ ተገለጠ ታው
ቃላችሁ፤ በእርሱም ኀጢአት የለም። 6በእ
ርሱም የሚኖር ኀጢአትን አያደርግም፤
ኀጢአት የሚያደርግ ግን እርሱን አላየውም

3፥2 ቍ1፡10፤ መዝ17፥15፤ ዮሐ1፥12፤ 17፥24፤ ሮሜ8፥29፤ 1ቆሮ10፥14፤ 2ቆሮ3፥18፤ ቈላ3፥4፤ 2ጴጥ1፥4፤ 1ዮሐ2፥28
3፥3 መዝ18፥26፤ 2ቆሮ7፥1፤ 2ጴጥ3፥13፡14
3፥4 1ዮሐ5፥17
3፥5 ቍ8፤ ዮሐ3፥17፤ 2ቆሮ5፥21
3፥6 ቍ9፤ 1ዮሐ2፥4፤ 5፥18፤ 3ዮሐ1፥11

ወይም አላወቀውም። 7ልጆች ሆይ፤ ማንም
እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤ እርሱ ጻድቅ
እንደ ሆነ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው፤
፤ 8ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው።
ምክንያቱም ዲያብሎስ ከመጀመሪያ አንሥቶ
ኀጢአትን የሚያደርግ ነው። የእግዚአብሔር ይሀ
ልጅ የተገለጠውም የዲያብሎስን ሥራ ያፈ 1፥9
ርስ ዘንድ ነው። 9ከእግዚአብሔር የተወለደ
ሁሉ ኀጢአትን አያደርግም፤ የእርሱ ዘር
በውስጡ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔር ስለ
ተወለደም ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም።
10የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች

3፥7 1ዮሐ2፥6፡29 3፥8 ቍ10፤ ማቴ4፥3፤ ዮሐ8፥44፤ ዕብ2፥14 3፥9 ቍ6፤ መዝ119፥3፤ ዮሐ1፥13፤ 1ጴጥ1፥23፤ 1ዮሐ5፥18 3፥10 ቍ1፡2፡8፤ ዮሐ1፥12፤ 1ዮሐ2፥9፤ 4፥8

[c]3፥2 ወይም በሚታወቅበት ጊዜ

**3፥1 የእግዚአብሔር ልጆች፤** እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችን እኛም ልጆቹ የመሆናችን እውነት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ታላላቅ መገለጦች አንዱ ነው፡፡ (1) የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን የድነታችን ታላቁ መብት ነው (ዮሐ 1፥12፤ ገላ 4፥7)፡፡ (2) የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችን የእምነታችንንና በእግዚአብሔር የመታመናችን መሠረት ነው (ማቴ 6፥25-34)፤ የወደፊቱ የክብር ተስፋችንም መሠረት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች እንደ መሆናችን መጠን የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፤ ከክርስቶስም ጋር አብረን የምንወርስነን (ሮሜ 8፥16-17፤ ገላ 4፥7)፡፡ (3) እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ስለ "ልጅነት መንፈስ" (ሮሜ 8፥15) ይኸውም የእግዚአብሔር ልጆች ስለ መሆናችን እያደር የላቀ ግንዛቤ እንዲኖረን ይፈልግብናል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በልባችን፣ "አባ አባት" የሚለውን ጩኸት ያሰድራል (ገላ 4፥6 እና ማብ ይመ)፤ "በመንፈስ ቅዱስ እንድንመራም" መሻትን ሰጥቶናል (ሮሜ 8፥14)፡፡ (4) በአብ ተግሣጽ የሚደርስብንና (ዕብ 12፥6-7፡11) እግዚአብሔርን ለማስደሰት የምንኖርበት ምክንያት (ቍ 9፤ 4፥17-19)፣ የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ነው፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹ ሲያደርገን ከፍተኛ ዐላማው ለዘላለም እንድንድን (ዮሐ 3፥16)፣ ልጁንም እንድንመስል ነው (8፥29)፡፡

**3፥6 በእርሱም የሚኖር፤** "በእርሱም የሚኖር" እና "ከእግዚአብሔር የተወለደ" (ቍ 9) የሚሉት ሐረጎች ተተካካይ የሆኑ አገላለጾች ናቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ተወልደው ዘለቄታ ላይ የሚደርሱት በእግዚአብሔር በመኖር የሚጸኑት ብቻ ናቸው (ዮሐ 15፥4 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1606 ላይ፤ "*ዳግም ልደት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

**3፥6 እርሱን አላየውም ወይም አላወቀውም፤** "አላየውም" እና "አላወቀውም" የሚሉት ግሶች ድርጊቱ የተፈጸመ ወይም የተከናወነ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው (የግሪኩ የኀላፊ ጊዜ ግስ የተፈጸመውን ድርጊት የሚያመለክት ሲሆን፣ ውጤቱ ደግሞ በአሁን ጊዜያት የሚቀጥል መሆኑን ያሳያል)፡፡ ስለዚህ ዮሐንስ (በኀጢአት የሚኖር ማንም ሰው) አንድ ሰው በኀጢአት የሚኖር ከሆነ፣ እግዚአብሔርን አላየውም (እርሱን በማየትም አይቀጥልም)፤ አላወቀውምም (እርሱን በማወቅም አይቀጥልም) ይላል፡፡ ስለዚህ ይህ ሐሳብ ክርስቶስን በእውነት ከቶ አምነውት የማያውቁትን ወይም ቀደም ሲል እግዚአብሔርን በውቀውት አሁን ግን እርሱን በማወቅ ያልቀጠሉትን ከሓዲዎች ሊመለከት ይችላል፡፡

**3፥9 ኀጢአትን ሊያደርግ አይችልም፤** "ኀጢአትን *መሥራት*" የሚለው ሐረግ (በግሪክ፣ "*ሃማርታኖ*") የአሁን ጊዜያት ንኡስ አንቀጽ ሲሆን፣ ቀጣይ የሆነ ድርጊትን የሚያመለክት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር የተወለዱት ኀጢአት *መሥራትን* የዘወትር ልማድ በማድረግ እንደማይቀጥሉበት ዮሐንስ በአጽንዖት ያሳስባል፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕይወት ኀጢአትን አዘውትረው በሚሠሩት ዘንድ አይኖርም (ከ1፥5-7፤ 2፥3-11፡15-17፡24-29፤ 3፥6-24፤ 4፥7-8፡20 ጋር ያነጻጽሩ)፡፡

(1) አዲስ ልደት ከእግዚአብሔር ጋር ምንጊዜም የማያቋርጥ ግንኙነትን እውን የሚያደርገውን መንፈሳዊ ሕይወት ያስገኛል፡፡ በዚህ መልእክት ላይ ዮሐንስ ስለ አማኙ አዲስ ልደት ይናገራል፤ አዲስ ልደት ተጀምሮ ቀጣይ በሆነበትና ዘላቂ በሆነው ግንኙነት ላይ ዮሐንስ አጽንዖት ለማድረግ ሲል፣ የከንዋኔን ፍጻሜ የሚያሳየውን የግሪኩን ጊዜ አመልካች ግስ ይጠቀማል (2፥29፤ 3፥9፤ 4፥7፤ 5፥1፡4፡18 ይመ፤ በገጽ 1606 ላይ፤ "*ዳግም ልደት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፡፡

(2) ሰዎች በኀጢአት እየኖሩ ሳለ የእግዚአብሔር ሕይወት (ይኸውም ከእግዚአብሔር የተወለዱ) አላቸው ማለት በመንፈሳዊ ረገድ ከቶ የማይታሰብ ነው፡፡ አማኞች አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ከሆነው የእግዚአብሔር የቅድስና ደረጃ ሊወርዱ ቢችሉም፣ ኀጢአትን በተከታታይ እየሠሩ መኖር ግን አይችሉም (ቍ 6፡10)፡፡

(3) ታማኝ የሆኑትን ኀጢአት የማይሠሩት፣ "የእርሱ ዘር" ይኸውም የራሱ የእግዚአብሔር ሕይወት፣ መንፈስ ቅዱስና የእግዚአብሔር ባሕርይ በእነርሱ ውስጥ በመኖራቸው ነው (5፥11-12፤ ዮሐ 15፥4፤ 2ጴጥ 1፥4)፡፡

(4) በእምነት (5፥4)፣ በአማኝ ልብ በሚያድረው ክርስቶስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና በተጻፈው ቃል አማካይነት (1ተሰ 2፥10 እና ማብ ይመ)፣ አማኞች ሁሉ ሕግን ከመጣስና ኀጢአትን ከመሥራት ነጻ ሆነው ከጊዜ ወደ ጊዜ መኖር ይችላሉ፡፡

**3፥10 የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች፤** በ2፥28—3፥10 ላይ ባለው ክፍል ውስጥ የዮሐንስ ትምህርት ዋና መደምደሚያ የሆነው ሐሳብ ይህ ነው፡፡ የድነትን ባሕርይ በቅጡ ሳይረዱ እንዳይቀሩና ባለመረዳታቸውም እንዳይታለሉ ሐዋርያው አንባቢዎቹን አስጠንቅቆአል (ቍ 7)፡፡ ከዚህም የተነሣ አንድ አማኝ የስሕተት አመለካከት ያለበትን ሥነ መለኮት ወይም ትምህርት በፍጥነት መተው ይኖርበታል፤ የስሕተት አመለካከቶችም የሚከተሉት ናቸው፡- አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሳይኖረው ይችላል (1፥3)፤

ተለይተው የሚታወቁት በዚህ ነው:-
ጽድቅን የማያደርግ ሁሉ፣ ወንድሙንም
የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።

## እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

[11]ከመጀመሪያ የሰማችኋት፣ እርስ
በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል የምትለዋ
መልእክት ይህች ናትና፤ [12]የክፉው ወገን
ሆኖ ወንድሙን እንደ ገደለው እንደ ቃየን
አትሁኑ፤ ለምን ገደለው? ምክንያቱም
የእርሱ ሥራ ክፉ፣ የወንድሙ ግን ጽድቅ
ስለ ነበረ ነው። [13]ወንድሞች ሆይ፤ ዓለም
ቢጠላችሁ አትደነቁ። [14]ወንድሞቻችንን
ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ
ተሻገርን እናውቃለን፤ ፍቅር የሌለው ሁሉ
በሞት ይኖራል። [15]ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ
ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት
እንደሌለው ታውቃላችሁ።
[16]ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ስለ እኛ
አሳልፎ ስለ ሰጠ፣ ፍቅር ምን እንደ ሆነ በዚህ
እናውቃለን፤ እኛም ሕይወታችንን ስለ
ወንድሞቻችን አሳልፈን ልንሰጥ ይገባናል።
[17]ማንም ሀብት እያለው፣ ወንድሙ
ሲቸገር አይቶ ባይራራለት፣ የእግዚአብሔር
ፍቅር እንዴት በእርሱ ይኖራል? [18]ልጆች
ሆይ፤ በተግባርና በእውነት እንጂ በቃልና
በአንደበት ብቻ አንዋደድ። [19]እኛ የእውነት ራእ 3፥1-4
ወገን መሆናችንን በዚህ እናውቃለን፤
ልባችንንም በፊቱ እናሳርፋለን፣ [20]ይህም
ልባችን በእኛ ላይ በሚፈርድብን ነገር ሁሉ
ነው። እግዚአብሔር ከልባችን ይልቅ ታላቅ
ነውና ሁሉን ነገር ያውቃል።
[21]ወዳጆች ሆይ፤ ልባችን የማይፈርድብን
ከሆነ በእግዚአብሔር ፊት ድፍረት አለን፤
[22]ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና በፊቱም ደስ

3፥11 ዮሐ13፥34-35፤ 15፥12፤ 1ዮሐ1፥5፤ 2፥7፤ 4፥7፡11፡21፤ 2ዮሐ1፥5
3፥12 ዘፍ4፥8፤ መዝ38፥20፤ ምሳ29፥10፤ ማቴ5፥37
3፥13 ዮሐ15፥18-19፤ 17፥14
3፥14 ዮሐ5፥24፤ 1ዮሐ2፥9
3፥15 ማቴ5፥21-22፤ ዮሐ8፥44፤ ገላ5፥20-21፤ 1ዮሐ2፥9፤ ራእ21፥8
3፥16 ዮሐ10፥11፤ 15፥13፤ ፊል2፥17፤ 1ተሰ2፥8
3፥17 ዘዳ15፥7-8፤ ያዕ2፥15-16፤ 1ዮሐ4፥20
3፥18 ሕዝ33፥31፤ ሮሜ12፥9፤ 1ዮሐ2፥1
3፥21 1ቆሮ10፥14፤ ኤፌ3፥12፤ 1ዮሐ5፥14
3፥22 ማቴ7፥7፤ ዮሐ8፥29፤ 14፥15፤ ዕብ13፥21

በኃጢአት ሊመላለስ፣ የሰይጣንን ሥራ ሊሠራ (ቍ. 8)፣ ዓለምን ሊወድ (2፥15)፣ በሌሎች ላይ ጕዳት ሊያደርስ (ቍ. 14-18) ይችላል፤ ይህም ሁሉ ሆኖ ግን ድነትን ያገኘ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ዕጣ ፈንታውም መንግሥተ ሰማይ ነው።

ከዚህ የሐሰት ትምህርት አኳያ በተፃራሪ መልኩ ዮሐንስ ማንም ሰው ኀጢአት መሥራትን የሚቀጥል ከሆነ (ቍ. 9 እና ማብ ይመ)፣ "ከዲያብሎስ ነው" (ቍ. 8)፤ "ከእግዚአብሔር አይደለም" በማለት በግልጽ ያምናል። ዘወትር ኀጢአት እየሠሩ የዘላለም ሕይወት አለን፤ የእግዚአብሔርም ልጆች ነን የሚሉ ሰዎች ተታለዋል፤ ውሸታሞችም ናቸው (ከ2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)። ከዚህም በላይ እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር የሚገልጹት ትእዛዞቹን በመፈጸም (5፥2)፣ ለሌሎች መንፈሳዊና አካላዊ ፍላጎት የሚጨነቁ መሆናቸውን በማሳየት ነው (ቍ. 16-17)።

**3፥15 ነፍሰ ገዳይም የዘላለም ሕይወት እንደሌለው፤** መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ በደሎች ላይ ጠቅለል ባለ መልኩ ልዩነት በማድረግ ያመለክታል፤ እነርሱም ሳይታሰብ የሚሠራ በደል (ዘሌ 4፥2፡13፡22፤ 5፥4-6 ይመ፤ ዘሌ 4፥3 እና ማብ፤ ዘኍ 15፥31 እና ማብ ይመ)፤ ቀለል ያለ በደል (ማቴ 5፥19)፣ ሆን ተብሎ የሚፈጸም በደል (ከ1ዮሐ 5፥16-17 ጋር ያነጻጽሩ) እንዲሁም መንፈሳዊ ሞትን የሚያመጡ በደሎች ናቸው (5፥16)። በእውነት ዳግም የተወለዱ አማኞች የክርስቶስ ዘላለማዊ ሕይወት በእነርሱ ላይ ከማደሩ የተነሣ የማይፈጽሟቸው አንዳንድ በደሎች ያሉ ስለ መሆናቸው ዮሐንስ በአጽንዖት ያሳስባል (ከ2፥11፡15-16፤ ከ3፥6-10፡14-15፤ 4፥20፤ 5፥2፤ ከ2ዮሐ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)። እነዚህ በደሎች ክብደታቸውና ምንጫቸው በአንድ አማኝ የመንፈስ እምብርት ላይ የሚያርፍ በመሆኑ፣ ሆን ተብሎ በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመ በደል ሆነው፣ ከክርስቶስ ኅብረት ተቈርጦ መለየትን፣ ከጸጋ መለየትንና፣ ከድነት ዐቢይ ሕይወት መውጣትን ያሳያሉ (ገላ 5፥4)።

(1) አንድ ሰው አሁንም የክፋት እስረኛ ወይም ከጸጋና ከዘላለም ሕይወት የተለየ ለመሆኑ የተሟላ ማስረጃ የሚሰጡት የሚከተሉት ናቸው፤ ክሕደት (2፥19፤ 4፥6፤ ዕብ 10፥26-31)፣ ነፍስ ግድያ (ቍ. 15፤ 2፥11)፣ ዝሙት ወይም ኢግብረገባዊነት (ሮሜ 1፥21-27፤ 1ቆሮ 5፤ ኤፌ 5፥5፤ ራእ 21፥8)፣ ለቤተ ሰብ ግድየለሽ ሆኖ ቤተሰቡን መተው (1ጢሞ 5፥8)፤ ሌሎችን ወደ ኀጢአት መምራት (ማቴ 18፥6-10) እና ጭካኔ (ማቴ 24፥48-51)። እነዚህ ዘግናኝ በደሎች ለእግዚአብሔር ክብር ፍጹም ደንታ ቢስ መሆንንና ለሌሎችም መታየት ሳለበት የፍቅር እንክብካቤ ግድ የለሽ መሆንን ያሳያሉ (ከ2፥9-10፤ ከ3፥6-10፤ ከ1ቆሮ 6፥9-11፤ ከገላ 5፥19-21፤ ከ1ተሰ 4፥5፤ ከ2ጢሞ 3፥1-5፤ ከዕብ 3፥7-19 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ማንም፣ "ከጌታ ኢየሱስ ጋር ኅብረት አለኝ፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነኝ፤ ከእርሱም ጋር የሚያድን ኅብረት አለኝ" እያለ ከላይ በተዘረዘሩት በደሎች ውስጥ ተዘፍቆ የሚገኝ ከሆነ፣ ራሱን ያታልላል፤ "ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም" (2፥4 ይመ፤ ከ1፥6፤ ከ3፥7-8 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ይሁን እንጂ አማኞች ኀጢአት ሁሉ፣ ቀላል ኀጢአት ነው የተባለው ሁሉ እንኳ ሳይቀር፤ መንፈሳዊ ሕይወትን ወደ ማዳከም ሊያደርስ፣ የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ወደ መተው ደረጃ፣ ከዚያም ወደ መንፈሳዊ ሞት ሊያመራ እንደሚችል ልብ ማለት ይኖርባቸዋል (ሮሜ 6፥15-23፤ 8፥5-13)።

**3፥17 ወንድሙ ሲቸገር፤** ፍቅር የሚገለጸው የተቸገሩትን ከልብ በመርዳት ነው፤ ይኸውም ምድራዊ ሀብታችንን ለእርሱ በማካፈል ነው (ከያዕ 2፥14-17 ጋር ያነጻጽሩ)። ከምግባችን፣ ከልብሳችን ወይም ከገንዘባችን ከፍለን በእውነት የተቸገሩትን ለመርዳት እምቢተኞች መሆን ማለት የልባችንን በር በእነርሱ ላይ መዝጋት ማለት ነው (ከዘዳ 15፥7-11 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ ወንጌልን ያልሰሙ ወንጌል ይደርሳቸው ዘንድም ገንዘባችንን መስጠትን ያካትታል (4፥9-10)።

**3፥22 ትእዛዛቱንም ስለምንጠብቅና፤** አንዳንድ ጸሎት የተመለሰው ሌላው ደግሞ ያልተመለሰው ለምንድን ነው? ዮሐንስ መልስ የሚያስገኝ ጸሎት ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ከመስጠት ጋር የተያያዘ መሆኑን ይገልጻል። እግዚአብሔርን መታዘዝ፣ መውደድና ማስደሰት (ዮሐ 8፥29፤ 2ቆሮ 5፥9፤ ኤፌ 5፥10፤ ዕብ 13፥21)፤ በጸሎት የጠየቅነውን መልስ ለማግኘታችን እጅግ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው (ከመዝ 50፥14-15፤ ከምሳ 15፥29፤ ከኢሳ 59፥1-2፤ ከማቴ 6፥15፤ ከማር 11፥25፤ ከያዕ 5፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 528 ላይ፣ "መልስ የሚያስገኝ ጸሎት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

የሚያስኘውን ስለምናደርግ የምንለምነውን
ሁሉ ከእርሱ እንቀበላለን። 23ትእዛዙም በልጁ
በኢየሱስ ክርስቶስ እንድናምንና እርሱ
እንዳዘዘንም እርስ በርሳችን እንድንዋደድ
ነው። 24ትእዛዞቹንም የሚጠብቁ ሁሉ በእርሱ
ይኖራሉ፤ እርሱም በእነርሱ ይኖራል።
በእኛ መኖሩን በዚህ ይኸውም እርሱ በሰጠን
መንፈስ እናውቃለን።

## መናፍስትን መርምሩ

4 ወዳጆች ሆይ፤ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፤
ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር
መሆናቸውን መርምሩ፤ ምክንያቱም ብዙ
ሐሰተ ኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።
2የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤
ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ
የሚቀበል መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር
ነው፤ 3ኢየሱስን የማይቀበል መንፈስ ግን
ከእግዚአብሔር አይደ ለም፤ እንደሚመጣ
የሰማችሁት የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ
ይህ ነው፤ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።
4ልጆች ሆይ፤ እናንተ ከእግዚአብሔር
ናችሁ፤ እነርሱንም አሸንፋችኋቸዋል፤
ምክንያቱም በእናንተ ውስጥ ያለው በዓለም
ካለው ይበል ጣል። 5እነርሱ ከዓለም ናቸው፤
ስለዚህ የሚ ናገሩት እንደ ዓለም ነው፤
ዓለምም ይሰማቸ ዋል። 6እኛ ከእግዚአብሔር
ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤
ከእግዚአብሔር ያልሆነ ግን አይሰማንም፤
በዚህም የእውነትን መንፈስና የሐሰትን
መንፈስ እናውቃለን።

## የእግዚአብሔር ፍቅርና የሰው ፍቅር

7ወዳጆች ሆይ፤ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ
ሆነ እርስ በርሳችን እንዋደድ፤ የሚወድ ሁሉ
ከእግዚአብሔር የተወለደ ነው፤ እግዚአብሔርንም

3፥23 ሉቃ24፥47፤ ዮሐ1፥12፤ 3፥18፤ 6፥29፤ 13፥34፤ 20፥3 1ቆሮ6፥11፤ 1ዮሐ5፥13
3፥24 1ተሰ4፥8፤ 1ዮሐ2፥3፡6፤ 14፥13፡15
4፥1 ኤር29፥8፤ ማቴ7፥15፤ 1ቆሮ10፥14፤ 12፥10፤ 2ተሰ2፥2፤ 1ዮሐ2፥18
4፥2 ዮሐ1፥14፤ 1ቆሮ12፥3፤ 1ዮሐ2፥23
4፥3 1ዮሐ2፥18፡22፤ 2ዮሐ1፥7
4፥4 2ነገ6፥16፤ ዮሐ12፥31፤ 16፥33፤ ሮሜ8፥31፤ 1ዮሐ2፥1
4፥5 ዮሐ15፥19፤ 17፥14፡16
4፥6 ማር13፥5፤ ዮሐ8፥47፤ 14፥17
4፥7 ዮሐ1፥13፤ 1ዮሐ2፥4፤ 3፥11

**4፥1 መንፈስን ... መርምሩ፤** ማንኛውንም መንፈስ ለመመርመር ያስፈለገበት ምክንያት (ይኸውም አንድ ሰው በመንፈስ ሲንቀሳቀስ ወይም ሲነዳ ማለት ነው)፥ "ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት" ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡ በመሆናቸው ነው (በገጽ 1519 ላይ፣ *"የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ይህም በተለይ እውነት ሆኖ የሚገኘው፣ በዘመኑ መጨረሻ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው አስተምህሮ እያደገ ችላ እየተባለ በሚሄድበት ጊዜ ነው (ማቴ 24፥11 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ፤ 2ጴጥ 2፥1-2 ይመ)። ክርስቲያኖች ክርስቲያን መምህራን፣ ጸሐፊዎች፥ ሰባኪዎችና ነቢያት ነን የሚሉትንና እንዲያውም ሥራዬ ወይም መልእክቱ የመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው የሚለውን ማንኛውንም ግለሰብ ይመረምሩ ዘንድ ታዘዋል። አማኞች አንድ ሰው አገልግሎቱ ወይም መንፈሳዊ ተመክሮዬ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው ስላለ፣ ይህንኑ ልክ እንደ ሆነ መቀበል የለባቸውም። ከዚህም በላይ ማንኛውም ዐይነት ትምህርት ወይም አስተምህሮ ስኬታማነትን፣ ታምራትን፣ ወይም ትክክል የሚመስል መቀባትን ብቻ መሠረት አድርጎ ቢቀርብ፣ ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ግድ ታ አይደለም (ማቴ 7፥22፤ 1ቆሮ 14፥29፤ 2ተሰ 2፥8-10፤ 2ዮሐ 1፥7፤ ራእ 13፥4፤ 16፥14፤ 19፥20)።

(1) ትምህርት ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ከተገለጠው ከእግዚአብሔር እውነት አንጻር መመርመር አለበት (ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ)።

(2) መመርመር ያለበት የትምህርቱ መንፈስ ነው። ትምህርቱ እንደ አዲስ ኪዳን ሐዋርያዊ ትምህርት ያለ አንድ ዐይነት መንፈስና አጽንዖት ይዞ ይገኛልን? አንድ ሰው ይህን ትምህርት ከመንፈስ ቅዱስ ወይም ከመላእክት የተቀበልሁት ነው ብሎ ያ ትምህርት በጤናማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍታቴ የማይደገፍ ከሆነ፣ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

(3) የአስተማሪዎች ሕይወት ፈሪሀ እግዚአብሔር ከሌለው ዓለም ጋር መምህራኑ ራሳቸው ካላቸው ግንኙነትና (ቊ 5 ይመ፤ በገጽ 2022 ላይ፣ *"ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) የክርስቶስንም ጌትነት ከማክበራቸው (ቊ 2፡6፤ ሮሜ 10፥9 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1694 ላይ፣ *"እውነተኛውን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት መመዘኛ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) አንጻር ይመረመር ዘንድ ያስፈልጋል።

**4፥2 ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ፤** ሥነ መለኮታዊ "ሊብራሊዝም" እና ሃይማኖታዊ ባዕድ አምልኮ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም መለኮት መሆኑን (ቊ 3 ዮሐ 1፥1 እና ማብ)፣ ከድንግል መወለዱን (ማቴ 1፥23 እና ማብ)፣ ወይም ድነት ይገኝ ዘንድ የተከናወነውን ቤዛዊ ሞቱንና ትንሣኤውን ሲክዱ፣ የክርስቶስ ተቃዋሚዎች መሆናቸውን ራሳቸውን በራሳቸው ያጋልጣሉ (ቊ 9-10፤ 2፥2፤ በገጽ 1735 ላይ፥ *"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጻፈው ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ መለየት ማለት ለጋኔናዊ የአታላይነት መንፈስ ራስን ማጋለጥ ነው (ቊ 1)፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ሥልጣንና ፍጹም አስተማማኝነት ንቆ ትቶአል (2ጴጥ 1፥3 እና ማብ፤ በገጽ 1941 ላይ፣ *"መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥4 በእናንተ ውስጥ ያለው ... ይበልጣል፤** መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ልብ የሚያድር ስለ መሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ አጽንዖት ያደርጋል (1ቆሮ 6፥19)። በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በዓለም ውስጥ ያለውን ክፋት ማለትም ኀጢአትን፥ ሰይጣንን፥ ፈተናን፥ ውጥረትን፣ ሐዘንን፣ ስደትን፣ የሐሰት ትምህርትን ሳይቀር ማሸነፍ እንችላለን፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን እንዲፈጸም ወዳለው ፈቃድም በድል አድራጊነት እንደርሳለን።

**4፥7 እርስ በርሳችን እንዋደድ፤** ፍቅር የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ (ገላ 5፥22-23)፣ አዲስ ልደት እውን ስለ መሆኑም ማስረጃ ቢሆንም እንኳ (2፥29፤ 3፥9-10፤ 5፥1)፣ እኛ በሕይወታችን እናሳድገው ዘንድ ኀላፊነት አለብን። በዚህም ምክንያት ዮሐንስ ሌሎችን እንድንወድ፥ ስለ እነርሱ ደኅንነት እንድንጨነቅ፣ ደኅንነታቸውንም እንድንሻ ይመክረናል። ዮሐንስ ከዚህ ላይ የሚናገረው እንዲሁ በደፈናው ስለ መልካም ምኞት ሳይሆን፣ ሰዎች ከችግራቸው እንዲወጡ ለመርዳት ስለ መወሰንና ለእነርሱ ቅን ልብ እንዲኖረን ጥረት ስለማድረግም

ያውቃል። 8የማይወድ ግን እግዚአብሔርን
አያውቅም፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።
9እግዚአብሔር ፍቅሩን በመካከላችን የገለጠው
እንዲህ ነው፤ እኛ በእርሱ አማካይነት
በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድያ
ልጁን ወደ ዓለም ላከ። 10ፍቅር ይህ ነው፤
እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው ሳይሆን
እርሱ እንደ ወደደንና ስለ ኀጢአታችን ማስ
ተስረያ[a] ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው።
11ወዳጆች ሆይ እግዚአብሔር እንዲህ ከወደደን፣
እኛም እርስ በእርሳችን መዋደድ ይገባናል።
12እግዚአብሔርን ያየ ከቶ ማንም የለም፤ እርስ
በርሳችን ብንዋደድ ግን እግዚአብሔር በእኛ
ይኖራል፤ ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ይሆናል።
13መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ
እንደምንኖር እርሱም በእኛ እንደሚኖር
እናውቃለን። 14አብ ልጁን የዓለም አዳኝ
ይሆን ዘንድ እንደላከው ዐይተናል፤
እንመሰክራለንም። 15ኢየሱስ የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆነ አምኖ በሚመሰክር ሁሉ፣
እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል፤ እርሱም
በእግዚአብሔር ይኖራል። 16ስለዚህም እግዚአብሔር
ለእኛ ያለውን ፍቅር እናውቃለን፤ በፍቅሩም
እናምናለን።
እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅር የሚኖር
በእግዚአብሔር ይኖራል፤ እግዚአብሔርም
በእርሱ ይኖራል። 17በዚህም ዓለም እርሱን
እንመስላለንና። በፍርድ ቀን ድፍረት
ይኖረን ዘንድ፣ ፍቅር በዚህ ዐይነት
በመካከላችን ፍጹም ሆኖአል፤ 18በፍቅር
ፍርሀት የለም፤ ፍጹም ፍቅር ግን ፍርሀትን
አውጥቶ ይጥላል፤ ፍርሀት ከቅጣት ጋር
የተያያዘ ነውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ
ፍጹም አይደለም።
19እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ
እንወደዋለን። 20ማንም፣ "እግዚአብሔርን
እወደዋለሁ" እያለ ወንድሙን ቢጠላ፣
እርሱ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን
የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ
አይችልምና። 21እርሱም "እግዚአብሔርን
የሚወድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል"
የሚለውን ይህን ትእዛዝ ሰጥቶናል።

## በእግዚአብሔር ልጅ ማመን

5 ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ
ሆነ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር
ተወልዶአል፤ አባትንም የሚወድ ሁሉ
ልጁንም እንደዚሁ ይወዳል። 2እግዚአብሔርን
ስንወድና ትእዛዛቱን ስንፈጽም የእግዚአብሔርን
ልጆች እንደ ምንወድ በዚህ እናውቃለን፤
3እግዚአብሔርን መውደድ ትእዛዛቱን
መፈጸም ነውና። ትእዛዛቱም ከባድ
አይደሉም፤ 4ምክንያቱም ከእግዚአብሔር
የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋል። ዓለምን
የሚያሸን ፈውም እምነታችን ነው። 5ኢየሱስ
የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን ራእ 2፥7
በስተቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማነው?
6በውሃና በደም የመጣው ይህ፣ ኢየሱስ
ክርስቶስ ነው። እርሱ በውሃና በደም እንጂ
በውሃ ብቻ አልመጣም። የሚመሰክረውም

4፥8 ቍ7:16
4፥9 ዮሐ1፥18፤ 3፥16:17፤ 1ዮሐ5፥11
4፥10 ሮሜ3፥25፤ 5፥8:10
4፥11 ዮሐ3፥16፤ 15፥12፤ 1ቆሮ10፥14፤ 1ዮሐ3፥11
4፥12 ቍ17፤ ዮሐ1፥18፤ 1ዮሐ2፥5
4፥13 1ዮሐ2፥3፤ 3፥24
4፥14 ሉቃ2፥11፤ ዮሐ3፥17፤ 15፥27
4፥15 1ዮሐ2፥23፤ 3፥24፤ 5፥5
4፥16 ቍ8:12:13፤ 1ዮሐ3፥24
4፥17 ቍ12፤ ማቴ10፥15፤ ኤፌ3፥12፤ 1ዮሐ2፥5
4፥18 ሮሜ8፥15
4፥19 ቍ10
4፥20 ቍ12፤ ዮሐ1፥18፤ 1ዮሐ1፥6፤ 2፥4:9፤ 3፥17
4፥21 ማቴ5፥43፤ 1ዮሐ2፥7:9
5፥1 ዮሐ1፥13፤ 3፥15፤ 8፥42፤ 1ዮሐ2፥22:23፤ 4፥2:15
5፥2 1ዮሐ2፥3፤ 3፥14
5፥3 ማቴ11፥30፤ ማቴ23፥4፤ ዮሐ14፥15 5፥4 ዮሐ1፥13፤ 16፥33
5፥5 ቍ1፤ 1ዮሐ2፥23 5፥6 ዮሐ14፥17፤ 19፥34

[a]4፥10 ወይም *ኀጢአታችንን አስወግዶ፣ ቍጣውን ያርቅልን ዘንድ*

ነው (3፥16-18 ይመ፤ ከሉቃ 6፥31 ጋር ያነጻጽሩ)። ፍቅርን በተግባር እናሳይ ዘንድ ዮሐንስ የሚያደፋፍረን በሦስት ምክንያት ነው፦ (1) ፍቅር እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ለእኛ በመስጠት የገለጠው ጕዳይ ሲሆን (ቍ 9-10)፣ የራሱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው (ቍ 7-9)። የእርሱን ባሕርይ ባሕርያችን በማድረግ ከእርሱ ጋር የምንጋራውም ከእርሱ በመወለዳችን ነው (ቍ 7)። (2) እግዚአብሔር ስለ ወደደን ፍቅሩን፣ ምሕረቱንና ተረዳኢነቱን ተመክሮአችን ያደረግን ሁሉ፣ በግል ሕይወታችን ዋጋ የሚያስከፍለን ቢሆንም እንኳ፣ ሌሎችን የመርዳት ግዴታ አለብን። (3) እርስ በርሳችን ብንዋደድ፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መኖሩን ይቀጥላል። ፍቅሩም በእኛ ውስጥ ፍጹም ይሆናል (ቍ 12)።

**4፥17 በፍርድ ቀን ድፍረት ይኖረን ዘንድ፤** በክርስቶስ ብንጸና፣ ከአብ ጋር ኅብረት ቢኖረን (1፥3)፣ ትእዛዞቹን ለማክበር ትጋት ብናሳይ (2፥3)፣ ከዓለም እንደ ተለየን ብንጸና (2፥15-17)፣ በእውነት ብንኖር (2፥24)፣ ሌሎችን ብንወድ (ቍ 7-12)፣ በፍርድ ቀን የማይፈረድብን ለመሆናችን መተማመኛ ሊኖረን ይችላል (ቍ 17-18 ይመ፤ በገጽ 2030 ላይ፣ *"የድነት ዋስትና"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥1 የሚያምን ... የሚወድ፤** እውነተኛ የሆነ እምነት ለአብና ለልጁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስጋናንና ፍቅርን ይገልጻል። እምነትና ፍቅር የማይለያዩ ናቸው፤ ከእግዚአብሔር ስንወለድ፣ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፍቅር በልባችን ያፈስልናል (ሮሜ 5፥5)።

**5፥2 በዚህ እናውቃለን፤** ለሌሎች የምናሳየው ፍቅር እውነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር የሚሆነው፣ እግዚአብሔርን የምንወድና ትእዛዞቹን የምናከብር ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው (ከ2፥3፤ 3፥23፤ ከዮሐ 15፥10 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 22፥37 እና ማብ፤ ዮሐ 14፥21 እና ማብ ይመ)።

**5፥4 ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን ነው፤** ዓለምን የሚያሸንፍ እምነት የዘላለም ሕይወትን ነባራዊ እውነታ አሻግሮ የሚያይ፣ የእግዚአብሔርን ኀይል ተመክሮው የሚያደርግና ክርስቶስን የሚወድ እምነት ነው፤ ይኸውም የዓለም ኀጢአተኛ ደስታ፣ ሥጋዊ ፋይዳ፣ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለው መንገድ፣ ራስ ወዳድነት የሚታይበት ቍስአካላዊነት ሁሉ የማያጓጓን እስከሚሆን ድረስ ብቻ ሳይሆን፣ እስከሚያንገሸግሸን፣ እስከሚያስጠላንና እስከሚያሳዝነን ድረስ (ራእ 2፥7 እና ማብ ይመ) በንቀት በማየት፣ የእግዚአብሔርን ኀይል ተመክሮ እስከ ማድረግና ክርስቶስን እስከ መውደድ ድረስ የሚያበቃ እምነት ማለት ነው።

**5፥6 በውሃና በደም፤** ይህ ሐረግ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ ስለ ተጠመቀው ጥምቀትና በመስቀል ላይ ስለ ተፈጸመው ሞቱ ሳያመለክት አይቀርም። አንዳንዶች መለኮታዊ ባሕርይ ያለው ክርስቶስ ሞትን አልቀመሰም የሚል ትምህርት በማስተማራቸው ዮሐንስ ይህን ሳይጽፍ አይቀርም። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ሥግው ሆኖ በመሞቱ ኀጢአታችንን ሁሉ ለማስተሰረይ ብቃት አለው። መንፈስ ቅዱስም ስለዚህ እውነት ይመሰክራል (ቍ 7-8)።

መንፈስ ነው፤ መንፈስ እውነት ነውና።
[7]ስለዚህ ሦስት ምስክሮች አሉት። [8]እነርሱም*
መንፈሱ፣ ውሃውና ደሙ ናቸው፤ ሦስቱም
ይስማማሉ። [9]የሰውን ምስክርነት ከተቀበልን፣
የእግዚአብሔር ምስክርነት ከዚያም ይልቃል፤
ይህ ስለ ልጁ የሰጠው የእግዚአብሔር ምስክርነት
ነውና። [10]በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ
በልቡ ምስክር አለው፤ ማንም እግዚአብሔርን
የማያምን ሁሉ እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን
ምስክርነት ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል።
✝ [11]ምስክርነቱም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር
የዘላለምን ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት
ያለው በልጁ ነው። [12]ልጁ ያለው ሕይወት
ራእ 3፥20 አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት
የለውም።

## ማጠቃለያ ሐሳብ

[13]በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ
እናንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ
ታውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ፤
[14]በእግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ያለን ድፍረት
ይህ ነው፤ ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ
ብንለምን እርሱ ይሰማናል፤ [15]የምንለምነውን
ሁሉ እንደሚሰማን ካወቅን፣ የለመነውንም
ነገር እንደ ተቀበልን እናውቃለን።
[16]ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያበቃ
ኀጢአት ሲያደርግ ቢያየው ይጸልይ፤
እግዚአብሔርም ለሞት የማያበቃ ኀጢአት
ላደረጉት ሕይወትን ይሰጣል። ለሞት
የሚያበቃም ኀጢአት አለ፤ ስለዚህኛው ግን
ይጸልይ አልልም። [17]ዐመፅ ሁሉ ኀጢአት

5፥7 ማቴ18፥16
5፥9 ማቴ3፥16፡17፤ ዮሐ5፥32፡34፡37፤ 8፥17፡18
5፥10 ዮሐ3፥33፤ ሮሜ8፥16፤ ገላ3፥6፤ 1ዮሐ1፥10
5፥11 ማቴ25፥46፤ ዮሐ1፥4
5፥12 ዮሐ3፥15፡16፡36
5፥13 ቍ11፤ ማቴ25፥46፤ 1ዮሐ3፥23
5፥14 ማቴ7፥7፤ ኤፌ3፥12፤ 1ዮሐ3፥21
5፥15 ቍ18፡19፡20፤ 1ነገ3፥12
5፥16 ዘፀ23፥21፤ ኤር7፥16፤ 14፥11፤ ዕብ6፥4-6፤ 10፥26፤ ያዕ5፥15
5፥17 ቍ16፤ ዮሐ2፥1፤ 3፥4

*5፥7፡8 ጥንታዊ ባልሆነ በቡልጌት ቅጅ ላይ በሰማይ የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው፥ እነርሱም አባት፥ ቃልና መንፈስ ቅዱስ ናቸው ይላል:: * በምድር የሚመሰክሩት ሦስቱ ናቸው ሆኖም ይህ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በነበሩት የግሪክ ቅጆች ውስጥ አይገኝም::

**5፥12 ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤** ሰዎች ሁሉ ወንጌልን መስማት አለባቸው፥ ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በእግዚአብሔር ልጅ ነው፥ የዘላለም ሕይወትን በሌላ መንገድ ለመቀበል ወይም ለማግኘት ከቶ አይቻልም:: እርሱ ብቻ፣ *"መንገድና ሕይወት"* ነው (ዮሐ 14፥6):: የዘላለም ሕይወት ማለት በእኛ ውስጥ ያለ የክርስቶስ ሕይወት ማለት ነው:: ከእርሱ ጋር ሕያው የሆነ የእምነት ግንኙነት እስካለን ድረስ ይህ ሕይወት ይኖረናል (ዮሐ 15፥4 ይመ፥ ዮሐ 17፥3 እና ማብ ይመ፥ ቈላ 3፥4 ይመ)::

**5፥13 የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ፤** ዮሐንስ ይህን መልእክት ሲጽፍ፣ ዐላማው ለእግዚአብሔር ሕዝብ የድነትን ዋስትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰፈርት ለመስጠት እንደ ሆነ ገለጸ:: ይህ ሐሳብ በሰፊው እንዴት እንደ ተብራራ ለማየት፣ በገጽ 2030 ላይ፣ "የድነት ዋስትና" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

**5፥14 ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን፤** በጸሎታችን ለእግዚአብሔር ራሳችንን ማስገዛት አለብን፥ የእርሱ ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸምም መለመን ይኖርብናል (ዮሐ 14፥13):: የእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸ በመሆኑ፣ በብዙ ሁኔታዎች እናውቀዋለን፤ በሌላም ጊዜ ከልባችን ፈቃዱን ስንሻ ብቻ ግልጽ ይሆናል:: ስለ አንድ ጕዳይ ፈቃዱን አንድ ጊዜ ካወቅን፣ በልበ ሙሉነትና በእምነት መጠየቅ እንችላለን:: ይህን ስናደርግ እርሱ እንደሚሰማን፣ እርሱ ለእኛ ያለው የእርሱ ዐላማም በእኛ ውስጥ እንዲሚፈጸም እናውቃለን (3፥22 እና ማብ ይመ፥ በገጽ 528 ላይ፣ ***"መልስ የሚያስገኝ ጸሎት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)::

**5፥16 ይጸልይ ... ሕይወትን ይሰጣል፤** እግዚአብሔር ይመልስልናል ብለን ስለምንተማመንበት የጸሎት ዐይነት ማለትም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለሚቀርበው ጸሎት ዮሐንስ ይናገራል (ከቍ 14-15 ጋር ያነጻጽሩ)፥ ይኸውም፣ ሕይወትና ጸጋ ይበዛላቸው ዘንድ ልናገለግላቸው ስለሚገባን የእግዚአብሔር ሰዎች ማለትም ጸሎት ስለሚያስፈልጋቸው በመንፈሳዊ ሕይወት ረገድ ደካማ ስለ ሆኑ አማኞች የምንጸልየው ጸሎት ነው:: እንዲህ ዐይነቱ ጸሎት እንዴት መካሄድ እንዳለበት የሚመሩት ሁኔታዎች የሚከተሉት ናቸው፥

(1) ጸሎት የሚያስፈልጋቸው ወንድም ወይም እኅት መሆን ይገባቸዋል፥ ይህም ኀጢአትን አውጥቶና አውርዶ ያልፈጸመ ወይም ሆን ብሎ ያልሠራ ሲሆን፣ በደሉ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ሆን ተብሎ የሚደረግን ዐመፅ የማይመለከት መሆን አለበት (የሚቀጥለውን ማብራሪያ ይመልከቱ):: ስለዚህ የእነዚህ ወገኖች መተላለፍ መንፈሳዊ ሞትን ከሚያስከትል በደል ደረጃ አልደረሰም ማለት ነው (ከሮሜ 8፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፣ እነዚህ አማኞች አሁንም መንፈሳዊ ሕይወት አላቸው፥ ሆኖም በመንፈሳዊ ሕይወት ረገድ ደካሞች ናቸው:: ንስሓ የሚገባ ልብ አላቸው፥ እግዚአብሔርን ከሚያሳዝነው ነገር ሁሉ ነጻ ለመሆንም ይፈልጋሉ፤ ይሁን እንጂ የሰይጣንና የኀጢአትን ኀይል ይሰብሩ ዘንድ ርዳታ ይፈልጋሉ::

(2) ለእንደዚህ ያሉ ሰዎች፣ "ሕይወትን" እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ቤተ ክርስቲያን መጸለይ አለባት:: ከዚህ ላይ፣ "ሕይወት" ሲባል ኀጢአት የሚፈታተነው ሕይወት ማለት ሲሆን (ከሮሜ 8፥6፥ ከ2ቆሮ 3፥6፥ ከ1ጴጥ 3፥7 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የመንፈሳዊ ኀይልና የእግዚአብሔር ጸጋ ዳግም በሕይወት ውስጥ እውን መሆን ማለት ነው (በገጽ 1746 ላይ፣ ***"እምነትና ጸጋ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: እግዚአብሔር ይህን ዐይነቱን ጸሎት ሰምቶ እንደሚመልስ የተስፋ ቃል ሰጥቶአል::

(3) ለሞት የሚያደርስ ኀጢአት (ይኸውም መንፈሳዊ ሞት) ለሠሩ፣ በክርስትና ሕይወታቸው ረጅም ዕድሜ ላሳለፉ አማኞች፣ እግዚአብሔር ተጨማሪ ጸጋና ሕይወት ይሰጣል ብላ ቤተ ክርስቲያን ርግጠኛ በመሆን ልትጸልይ አትችልም:: ይህ ዐይነቱ ኀጢአት እግዚአብሔርን ሆን ብሎ ካለመታዘዝ የሚመነጨውን በፈቃድ የሚፈጸምን ዐመፅ ያካትታል (በገጽ 1853 ላይ፣ ***"የኀጢአተኛ ተፈጥሮ ሥራዎችና የመንፈስ ፍሬ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በመንፈሳዊ ረገድ ሙታን ስለ ሆኑ፣ ሕይወት የሚሰጣቸው ንስሓ በመግባት ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ ብቻ ነው (ሮሜ 8፥13 እና ማብ ይመ):: በክርስቶስ የእግዚአብሔርን ድነት እንደ ገና የሚቀበሉት ሰዎች በቂ ዕድል ያገኙ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ሕይወታቸውን እንዲቈጣጠርና እንዲመራ መጸለይ አለብን::

**5፥17 ለሞት የማያበቃም ኀጢአት፤** ዮሐንስ

# የድነት ዋስትና

*1ዮሐ 5፥13 "በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ፣ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ"*

አያንዳንዱ ክርስቲያን የድነት ዋስትና እንዲኖረው ይገባል፤ ይኸውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ፣ ወይም ሞት ድንገት ሲደርስ፣ በመንግሥተ ሰማይ ከጌታ ኢየሱስ ጋር የመሆን ርግጠኝነት ነው (ፊል 1፥23)። ዮሐንስ ይህን የመጀመሪያ መልእክቱን ሲጽፍ፣ ዐላማው የእግዚአብሔር ሰዎች ይህ የድነት ዋስትና ይኖራቸው ዘንድ ነው (1ዮሐ 5፥13)። ዮሐንስ በየትኛውም ቦታ አዲስ ሰው ሆኖ የመገኘት ተመክሮ የድነት ማረጋገጫ ወይም ዋስትና ነው አለማለቱን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ያለፈን ተመክሮ ወይም ሕይወት ይታይበት የነበረን እምነት ብቻ መሠረት በማድረግ የዘላለም ሕይወት አለን ማለት ትልቅ ስሕተት ነው። ይህ መልእክት ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሚያድግ የኅብረት ግንኙነት ውስጥ ያለን ስለ መሆናችን የምናውቅባቸው ዘጠኝ መንገዶች ያቀርባል፦

(1) "በእግዚአብሔር ልጅ ስም" ብናምን የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ አለን (1ዮሐ 5፥13 ይመ፤ ከ4፥15፤ 5፥1፡5 ጋር ያነጻጽሩ)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታችንና አዳኛችን እንዲሆን የተላከ፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የማይቀበል እምነት ከሌለ በቀር የዘላለም ሕይወት ወይም የድነት ዋስትና አይኖርም (በገጽ 1746 ላይ፣ "እምነትና ጸጋ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ክርስቶስን የሕይወታችን ጌታ አድርገን ብናከብረው፣ ትእዛዞቹንም ለማክበር ከልብ ጥረት ብናደርግ፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ይኖረናል፤ "ትእዛዛቱን ብንፈጽም እርሱን ማወቃችንን በዚህ ርግጠኞች እንሆናለን። "እርሱን አውቃለሁ" እያለ ትእዛዙን የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ፣ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ፍጹም ሆኖአል። በእርሱ መሆናችንን የምናውቀው በዚህ ነው፤ ማንም በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል።" (1ዮሐ 2፥3-5 ይመ፤ ከ3፥24፤ 5፥2፤ ከዮሐ 8፥31፡51፤ 14፥21-24፤ 15፥9-14፤ ከዕብ 5፥9 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) ዓለምን ከመውደድ ይልቅ አብንና ልጁን ብንወድ፣ የዓለምንም ተጽዕኖ ድል ብናደርግ፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ይኖረናል፤ "ዓለምን ወይም በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ዘንድ የለም፤ ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፦ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም።" (1ዮሐ 2፥15-16 ይመ፤ ከ4፥4-6፤ 5፥4 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 2022 ላይ፣ "ክርስቲያን ከዓለም ጋር ያለው ግንኙነት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) ኀጢአት ከመሥራት ይልቅ ዘወትርና በጽናት የጽድቅ ሥራ ብንሠራ፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ይኖረናል፤ "እርሱ ጻድቅ መሆኑን ካወቃችሁ፣ ጽድቅን የሚያደርግ ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ ታውቃላችሁ።" (1ዮሐ 2፥29)፤ በአንጻሩ ግን፣ "ኀጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው" (3፥7-10 ይመ፤ 3፥9 እና ማብ ይመ)።

(5) ወንድሞቻችንንና እኅቶቻችንን ብንወድ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ አለን፤ "ወንድሞቻችንን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ... እኛ የእውነት ወገን መሆናችንን በዚህ እናውቃለን፤ ልባችንንም በፊቱ እናሳርፋለን፣ (1ዮሐ 3፥14፡19 ይመ፤ ከ2፥9-11፤ ከ3፥23፤ ከ4፥8፡11-12፡16፡20፤ ከ5፥1፤ ከዮሐ 13፥34-35 ጋር ያነጻጽሩ)።

(6) መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን እንደሚኖር የምንገነዘብ ከሆነ፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ አለን፤ "በእኛ መኖሩን (ኢየሱስ ክርስቶስ) በዚህ ይኸውም እርሱ በሰጠን መንፈስ እናውቃለን" (1ዮሐ 3፥24)። እንደ ገናም፣ "መንፈሱን ስለ ሰጠን፣ እኛ በእርሱ እንደምንኖር፣ እርሱም በእኛ እንደሚኖር እናውቃለን" (4፥13)።

(7) የኢየሱስን አርአያነት ለመከተልና እርሱ እንደኖረውም ለመኖር ጥረት ብናደርግ፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ አለን፤ "በእርሱ እኖራለሁ የሚል፣ ኢየሱስ እንደ ተመላለሰ ሊመላለስ ይገባዋል" (1ዮሐ 2፥6 ይመ፤ ከዮሐ 8፥12 ጋር ያነጻጽሩ)።

(8) "በሕይወት ቃል" ብናምን፣ እርሱንም ብንቀበልና በእርሱ ብንጸና ይኸውም ሕያው በሆነው በክርስቶስ (1ዮሐ 1፥1)፣ ማለትም ከመጀመሪያ በሆነው በክርስቶስ መልእክትና በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት መልእክት ብንኖር፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ ይኖረናል፤ "ከመጀመሪያ

የሰማችሁት በእናንተ ውስጥ ይኑር፤ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ውስጥ ቢኖር፣ እናንተም በወልድና በአብ ትኖራላችሁ።" (2፥24 ይመ፤ ከ1፥1-5፤ ከ4፥6 ጋር ያነጻጽሩ)።

(9) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ራሱ ሊወስደን ስለ መመለሱ ማለትም ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ልባዊ የሆነ ናፍቆትና ጽኑ ተስፋ ካለን፣ የዘላለም ሕይወት ማረጋገጫ አለን፤ "ወዳጆች ሆይ፥ እኛ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ወደ ፊት ምን እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ እናየዋለንና፣ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን። በእርሱ ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ፣ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል።" (1ዮሐ 3፥2-3 ይመ፤ ከዮሐ 14፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)።

ነው፤ ለሞት የማያበቃም ኀጢአት አለ።
18ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኀጢአት
እንደማያደርግ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሚጠብቀው፣ ክፉውም እንደማይነካው
እናውቃለን። 19እኛ ከእግዚአብሔር እንደሆንን፣
መላው ዓለምም በክፉው ሥር እንደ ሆነ
እናውቃለን።
20የእግዚአብሔር ልጅ እንደ መጣ፣ እውነተኛ
የሆነውን እርሱን እንድናውቅ ማስተዋልን
እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እኛም እውነተኛ
በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አለን።
እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት
ነው።
21ልጆች ሆይ፤ ራሳችሁን ከጣዖቶች
ጠብቁ።

5፥18 ማቴ5፥37፤ ዮሐ1፥13፤ 14፥30
5፥19 ዮሐ12፥31፤ 14፥30፤ 17፥15፤ 1ዮሐ4፥6
5፥20 ቍ5፥11፤ ማቴ25፥46፤ ሉቃ24፥45፤ ዮሐ17፥3
5፥21 1ቆሮ10፥14፤ 1ተሰ1፥9፤ 1ዮሐ2፥1

ሁለት የተለያየ የኀጢአት ዐይነት እንዳለ ያሳያል፡ ይኸውም (1) *የመጀመሪያው* ቀለል ያለ የኀጢአት ዐይነት ሲሆን፣ ሆን ተብሎ ወይም ሳይታሰብ የተፈጸመና በቅጽበት ወደ መንፈሳዊ ሞት የማያመራ ኀጢአት ነው፤ (2) ይህኛው ደግሞ ዘግናኝ የሆነ የኀጢአት ዐይነት ነው፤ በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ የሚደረግን ዐመፅ የሚያካትት ሲሆን፣ ከመንፈሳዊ ሞት የመነጨ ወይም ወደ መንፈሳዊ ሞት የሚያመራ ነው፤ ወይም ደግሞ ከእግዚአብሔር ሕይወት መለየትን የሚያስከትል ኀጢአት ነው (3፥15 እና ማብ፤ ዘኍ 15፥31 እና ማብ፤ ሮሜ 8፥13 እና ማብ፤ ገላ 5፥4 እና ማብ ይመ)።

**5፥19 በክፉው ሥር እንደ ሆነ፤** ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ መሆኑን የሚያሳውንና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚቀርበውን ትምህርት ካልተረዳን በቀር፣ አዲስ ኪዳንን ከቶ በቅጡ መረዳት አንችልም፤ እርሱ ክፉው ነው፤ ኀይሉም የአሁኑን ክፉ ዘመን ይቈጣጠራል (ከሉቃ 13፥16፤ ከ2ቆሮ 4፥4፤ ከገላ 1፥4፤ ከኤፌ 6፥12፤ ከዕብ 2፥14 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 4፥10 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 1443 ላይ፣ ***"የእግዚአብሔር መንግሥት"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(1) በደለኛ ሰዎችን፣ ክፋትን፣ ጭካኔንና ኢፍትሓዊነትን በውስጡ አካቶ የያዘውን ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለውን ዓለም በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በቀጥታ ይቈጣጠራል ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምርም። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ያለው ሥቃይ ሁሉ እንዲደርስ ከቶ አይፈልግም፤ የሥቃይ ምንጭም አይደለም፤ ወይም በዚህ ዓለም የሚሆነው ሁሉ ፍጹም የሆነው የእርሱ ፈቃድ አይደለም (ማቴ 23፥37፤ ሉቃ 13፥34፤ 19፥41-44 ይመ፤ በገጽ 1075 ላይ፣ ***"የእግዚአብሔር ፈቃድ"*** በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። መጽሐፍ ቅዱስ በአሁኑ ጊዜ ዓለም በእግዚአብሔር ግዛት ውስጥ አለመሆኑን ያሳያል፤ ይልቁንም በእርሱ አገዛዝ ላይ በማመፅ ላይ ይገኛል፤ ለሰይጣንም ባሪያ ሆኖአል፤ ከዚህ ሁኔታ የተነሣ ክርስቶስ ለመሞትና (ዮሐ 3፥16) ዓለምን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስታረቅ መጣ (2ቆሮ 5፥18-19)። ኀጢአትን፣ ክፋትን ወይም መንፈሳዊ ለብታን ከመዋጋት ራሳችንን ነጻ ለማድረግ ስንል፣ "እግዚአብሔር ሁሉን በመቈጣጠር ላይ ነው" የሚለውን ሐሳብ ከቶ ማስተናገድ የለብንም።

(2) ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ይህን ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌለውን ዓለም የሚቈጣጠርበት ሁኔታ አለ፤ እግዚአብሔር ልዑል አምላክ ነው፤ ሁሉም ነገር የሚከናወነው በእርሱ የይሁንታ ፈቃድ ነው፤ ወይም ደግሞ ሁሉም ነገር ሲከናወን እርሱ እንዳላየ አይቶ ያልፈዋል፤ እንዲሁም ዐላማውን ለመፈጸም ሲል እርሱ በቀጥታ ጣልቃ በመግባት ነገሮች ይፈጸማሉ። ያም ሆኖ በዚህ የታሪክ ወቅት እግዚአብሔር በዓለም ላይ ያለውን ሉዐላዊ ኀይሉንና አገዛዙን በበጎ ፈቃዱ ወስኖታል። ነገር ግን ይህ በራሱ ፈቃድ እውን ሆኖ የሚገኘው ውስኑነት ጊዜያዊ ነው፤ በጥበቡ የወሰነው ቀን ሲደርስ ሰይጣንንና ክፋትን ሁሉ ይደመስሳል (ራእ 19—20)። በዚያን ጊዜ ብቻ፣ "የዓለም መንግሥት፣ የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ሆነች፤ እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል" የሚለው እውን ይሆናል (ራእ 11፥15)።

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት - ሁለተኛ

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-3)
   (ሀ) ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ (1፥1)
   (ለ) ስለ እውነት ሲባል (1፥2-3)
I. የይሁንታ ቃልና ትእዛዝ (1፥4-6)
   (ሀ) አሁንም ይገፋበት ዘንድ ሐሳብ የቀረበበት ለእውነት ሲባል አስቀድሞ የተገለጸ ሎሌነት (1፥4)
   (ለ) ፍቅር ማሳየትና መታዘዝ ግዴታ መሆኑ መገለጹ (1፥5-6)
II. ምክርና ማስጠንቀቂያ (1፥7-11)
   (ሀ) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን መለየት (1፥7)
   (ለ) የእነርሱ ተጽዕኖ እንዳያደርባችሁ ተጠንቀቁ (1፥8-9)
   (ሐ) በቤታችሁ እንዳይቀመጡ ወይም እንዳይገለገሉ ከልክሏቸው (1፥10-11)
መደምደሚያ (1፥12-13)

**ጸሓፊ፤** *ዮሐንስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በእውነት መመላለስ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *85—95 ዓ.ም.*

*ታሪካዊ ጳራ*

ጸሓፊው ራሱን፣ "ሽማግሌው" በማለት ይገልጻል (ቍ 1)። ይህ የሆነው ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት መካከል ዮሐንስ ብቻ ዕድሜ ጠግቦ በሕይወት ያለ አገልጋይ በመሆኑ ነው፤ ከዚህም የተነሣ ይህ የተከበረ የሥልጣን ደረጃ በመጀመሪያው ምእት ዓመት መገባደጃ ላይ ማለትም ምእት ዓመቱ ሊያልቅ ሁለት ዐሥርት ዓመታት ሲቀሩ፣ ለሐዋርያው ዮሐንስ ወንጌል በደረሰበት አገር ሁሉ የተሰጠው ማዕረግ ሳይሆን አይቀርም።

ዮሐንስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ "ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ" በማለት ነው (ቍ 1)፤ አንዳንዶች፣ "ለተመረጠችው እመቤትና" የሚለውን ሐረግ በዘይቤያዊ አገላለጽ ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው ሲሉ፣ "ለልጆቿ" ሲባል ደግሞ አባላቱን ያመለክታል ይላሉ፤ "የተመረጠችው የእኅትሽ" (ቍ 13) የሚለው ሐረግ ደግሞ አሁንም በዘይቤያዊ አገላለጽ እኅት ማኅበረ ምእመናንን ያሳያል በማለት ይተረጕሙታል። ሌሎች ደግሞ መልእክቱ የተጻፈላትን ሴት በእማሬያዊ ትርጒም ረገድ በማየት፣ መልእክቱ የተጻፈላት ሴት፣ ዝነኛ የሆነች፣ በታናሽ እስያ የምትኖር፣ በዮሐንስ ዘንድ የምትታወቅና እርሱ መንፈሳዊ አባትና ባለሥልጣን በሆነበት ቅርብ አካባቢ ትኖር የነበረች መበለት ናት በማለት የዚህን ሐረግ ምንነት ይተረጕማሉ። ቤተ ሰቧና (ቍ 1) የእኅቷ ልጆች (ቍ 13) በዚያ ክልል በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዝና ያላቸው ሰዎች ናቸው። እንደ ሌሎቹ የዮሐንስ መልእክቶች ሁሉ ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክት በሰማኒያዎቹ ዓመታት መገባደጃ ላይ ወይም በዘጠናዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ላይ በኤፌሶን ሳይጻፍ አልቀረም።

**ዐላማ**

ዮሐንስ ከሐዋርያዊ እውነት ርቀው የስሕተትን ትምህርት የሚያሠራጩትን ተዘዋዋሪ አገልጋዮች (አስተማሪዎች፣ ወንጌላውያንና ነቢያት)፣ በእንግድነት ስለ መቀበል፣ ሰላምታ ስለ መስጠት፣ ወይም ርዳታ ስለ ማድረግ "የተመረጠችው እመቤት"ን ለማስጠንቀቅ ይህን መልእክት ጻፈ፤ የተመረጠችው እመቤት ጥንቃቄ ካላደረገች በቀር፣ ስሕተታቸውን

በማሠራጨት የበደላቸው ተካፋይ ትሆናለች፡፡ ይህ መልእክት በአንደኛ ዮሐንስ መልእክት ላይ የተወገዘውን ተመሳሳይ የሐሰት ትምህርት ይነቅፋል፡፡

### ቅኝት

ይህ መልእክት ከሐዋርያው ትምህርት (ቊ 7-8) ርቀው የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትሥጉት ከሚክዱት ከሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ጥንቃቄ ይደረግ ዘንድ በማሳሰብ፣ በአንደኛ ዮሐንስ መልእክት ላይ የተመለከተውን ማስጠንቀቂያ በአጽንዖት ያቀርባል፡፡ ዮሐንስ የተመረጠችውን እመቤትና ልጆቿን፣ "በእውነት ጸንተው" እንዲኖሩ (ቊ 4) ያበረታታል፡፡ እውነተኛ ፍቅር የክርስቶስን ትእዛዞች ማክበርንና እርስ በርስ መዋደድን (ቊ 6) ያካትታል፡፡ ክርስቲናዊ ፍቅር በእውነትና በስሕተት መካከል ያለውን ነገር ለይቶ ማየት አለበት እንጂ፣ ለሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በር መክፈት አይገባውም (ቊ 7-9)፡፡ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን በወዳጅነት መንፈስ መቀበል ማለት የስሕተታቸው ተካፋይ መሆን ማለት ነው (ቊ 10-11)፡፡ መልእክቱ ዐጭር መልእክት ነው፤ ምክንያቱም ዮሐንስ ከእመቤቲቱ ጋር ፊት ለፊት በቅርቡ ለመገናኘት ዐቅዶአል (ቊ 12)፡፡

### ልዩ ገጽታ

ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እጅግ ዐጭሩ መጽሐፍ ይህ ነው፡፡ (2) በመልእክት፣ በቃላት አመራረጥና ግልጽነት ባለው የአጻጻፍ ስልት ረገድ ከአንደኛና ከሦስተኛ የዮሐንስ መልእክት ጋር በሚያስደንቅ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው፡፡ (3) የራስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ምእመናን አባል ላልሆኑት ግለሰቦች ያላንዳች ልዩነት ርዳታ በማድረግ ጒዳይ ላይ ጥንቃቄ እንዲደረግ በመምከሩ፣ ለሦስተኛው ዮሐንስ መልእት ዐቢይ ሐሳብ ሚዛናዊ የሆነ መልእክትን ይሰጣል፤ ይኸውም እንግዳን ሲያስተናግዱ ከልክ በላይ እንዳይሆን ወይም ከልክ በታች እንዳይደረግ፣ ለሚዛናዊነት የሚበቃውን ሐሳብ መያዙን ያሳያል፡፡ ይህ መልእክት እንደነዚህ ያሉትን አገልጋዮች ከመርዳት በፊት፣ ሁሉንም ነገር ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋርያት ትምህርት አንጻር ጥንቃቄ ያለበት ምዘና መመዘን እንዲደረግ ያደፋፍራል፡፡

### ሁለተኛ የዮሐንስን መልእክት ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአንድ ቀን መነበብ ይኖርበታል፤
ሁለተኛ የዮሐንስ ❑ መልእክት

*ማስታወሻ*

ሽማግሌው፤

በእውነት ለምወዳት እኔ ብቻ ሳልሆን
እውነትን የሚያውቁ ሁሉ ለሚወዱት
ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ፤
2በውስጣችን ከሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም
ከሚሆን እውነት የተነሣ፣ 3ከእግዚአብሔር
አብና የአብ ልጅ ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ
ጸጋ፣ ምሕረትና ሰላም በእውነትና በፍቅር
ከእኛ ጋር ይሆናል።
4ከልጆችሽ አንዳንዶቹ ከአብ በተሰጠን
ትእዛዝ መሠረት በእውነት ጸንተው እየሄዱ
በማግኘቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። 5አሁንም
እመቤት ሆይ፤ ከመጀመሪያ የነበረችውን
እንጂ አዲስ ትእዛዝ አልጽፍልሽም፤ ይኸውም
እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ ነው። 6ይህም
ፍቅር፤ በትእዛዙ መሠረት እንመላለስ
ዘንድ ነው። ትእዛዙም ከመጀመሪያ እንደ
ሰማችሁት በፍቅር እንድትኖሩ ነው።
7ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደመጣ
የማያምኑ ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ወጥተዋል።
እንዲህ ያለ ማንኛውም ሰው አታላይና
የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። 8እናንተም
የደከማችሁበትን ዋጋ እንዳታጡ፣ ነገር
ግን ሙሉ ሽልማት እንድትቀበሉ ለራሳችሁ
ተጠንቀቁ። 9በክርስቶስ ትምህርት
የማይኖርና ከትምህርቱ የሚወጣ ሁሉ
አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት
የሚኖር ግን አብም ወልድም አለው።
10ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ፣ ይህንንም
ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት፤

1፥1 ቆላ3፡13፥ ዮሐ8፥32፥ ሐሥ11፥30፥ ሮሜ16፥13፥ 1ጢሞ2፥4፥ 1ጴጥ5፥13፥ 3ዮሐ1፥1
1፥2 ዮሐ14፥17፥ 2ጴጥ1፥12፥ 1ዮሐ1፥8
1፥3 ሮሜ1፥7
1፥4 ዮሐ3፥4
1፥5 1ዮሐ2፥7
1፥6 ዮሐ14፥15፥ 1ዮሐ2፥5፡7
1፥7 ዮሐ1፥14፥ 1ዮሐ2፥18፡22፥ 4፥1፡2፡3
1፥8 ማቴ10፥42፥ ማር10፥29፡30፥ 1ቆሮ3፥8፥ ዕብ10፥35፡36፥ 11፥26
1፥9 ዮሐ8፥31፥ 1ዮሐ2፥23 1፥10 ሮሜ16፥17

**1፥1 ለተመረጠችው እመቤትና፤** አንዳንዶች ይህን አባባል መሠረት በማድረግ የዮሐንስ መልእክት የተጻፈው ፈሪሀ እግዚአብሔር ላላት፣ "ኪያሪያ" (በግሪክ ቋንቋ ትርጕሙ፣ "እመቤት" ማለት ነው) ለተባለችው እመቤትና ለቤተ ሰቧ ነው ይላሉ:: ይሁን እንጂ፣ "ለተመረጠችው እመቤትና ለልጆቿ" ሲባል በዘይቤያዊ አገላለጽ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለአባላቷ" ማለት ሳይሆን አይቀርም (ከ1ጴጥ 5፥13 ጋር ያነጻጽሩ)::

**1፥1 በእውነት ለምወዳት፤** በአዲስ ኪዳን ላይ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለጠውን በጥንቃቄ በመከተል ዮሐንስ ሌሎችን ይወዳል፣ ስለ እነርሱም ይጨነቃል:: ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ራሱን አሳልፎ ሳይሰጡ፣ ለሌሎች ፍቅር ሊገለጥ ይችላል:: በዚህ መልኩ ለሌሎች መጨነቅን የሚያሳዩ ሰዎች ፍቅርን፣ ተቀባይነትን፣ ባልንጀራነትንና አንድነትን ከእግዚአብሔር እውነትና ትእዛዞች በላይ በማላቅ ከፍተኛ ስፍራ ይሰጣሉ (ቊ 5-6):: በሌላ በኩል ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግል አንድ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ሊያራምድ ለቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮም ጥብቅና ሊቆም ይችላል፣ ይህን ሁሉ ያድርግ እንጂ ለሌሎች ፍቅርን ሊገልጽና እንክብካቤን ላያደርግ ይችላል:: እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ለእርሱ እውነትና ለሌሎች ማለትም ለክርስቲያን ወገኖች ፍቅራችንን እንድንገልጥ ነው:: እውነትን በፍቅር መንገር አለብን (ኤፌ 4፥15 ይመ፤ ከ1ቆሮ 13፥6 ጋር ያነጻጽሩ)::

**1፥3 ጸጋ፣ ምሕረትና ሰላም፤** የእግዚአብሔርን ጸጋ፣ ምሕረትና ሰላም ለመቀበል፣ ማድረግ ያለብን፣ ለእውነት መቆምና (ቊ 7-11) ሌሎችን መውደድ ነው (ቊ 5-6):: ከሁለቱ አንዱን ሳይፈጽሙ መቅረት፣ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን በረከቶች እንዳታገኝ ያደርጋታል::

**1፥5 እርስ በርሳችን እንዋደድ፤** ዮሐ 13፥34-35 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**1፥6 ትእዛዙም፤** ዮሐ 14፥21 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**1፥7 ብዙ አሳቾች፤** ብዙ አሳቾችና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያጣምሙ፣ አመለካከታቸውንም እንዲቀበሏቸው ክርስቲያኖችን ለማግባባት የሚሞክሩ ስለ መሆናቸው ዮሐንስ አስጠነቀቀ:: የሐሰት ትምህርታቸውም ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ጋር የተያያዘ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ፣ ከድንግል የተወለደ (ማቴ 1፥18፤ ሉቃ 1፥27)፣ ደሙ ለሚያምኑት ሁሉ ለበደላቸው በሙሉ ይቅርታን የሚያስገኝ (1ዮሐ 2፥2፤ 4፥9-10)፣ "እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት" (ዮሐ 5፥20) መሆኑን ይክዳሉ::

**1፥9 በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና፤** ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የክርስቶስንና የሐዋርያትን መገለጥ የሚክዱ ሁሉ እግዚአብሔር የላቸውም፤ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን ቢሉም እንኳ (1ዮሐ 2፥4)፣ በክርስቶስ ትምህርት እስካልጸኑ ድረስ ተታለዋል፤ የክርስቶስን አስተምህሮ የሚክዱ ሁሉ ክርስቶስን ይክዳሉ:: በአዲስ ኪዳን ላይ የተገለጠውን እውነትና ጽድቅ የማይቀበልና የማያከብር ሥነ መለኮት ሁሉ ክርስቲያናዊ ሥነ መለኮት አይደለም፤ ተንቆ ሊተው ይገባል (ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)::

**1፥10 በቤታችሁ አትቀበሉት፤** አንድ አማኝ ለክርስቶስና ለእግዚአብሔር ቃል ያለው ፍቅርና ታማኝነት፣ ለክርስቶስና ለሐዋርያት ትምህርት ራሱን አሳልፎ ያልሰጠውን ክርስቲያን ነኝ የሚልን አማኝ (ቊ 9) (አገልጋይን ወይም ተራ ምእመንን)፣ የክርስቶስ ወንጌል ጠላት ነው ብሎ በመቊጠር ቊርጥ አድርጎ እንዲተወው ያደርጉታል:: የአዲስ ኪዳንን እምነት የሚያጣምሙ ወይም የሚቃወሙ ሰዎች፣ በአማኞች ኅብረት ውስጥ ተቀባይነት ማግኘት የለባቸውም:-

(1) እግዚአብሔር የሐሰት ትምህርትን እንዳይቀበሉ ጥንቃቄ ያደርጉ ዘንድ እውነተኛ አማኞችን ያስጠነቅቃል (ቊ 8):: "ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም" መግባታቸውን እውነተኛ አማኞች ልብ ማለት አለባቸው (ቊ 7)::

(2) በመምህርነት ሙያቸው በክርስቶስ ትምህርት የማይቀጥሉትንና አምላክ የሌላቸውን (ቊ 9) እና በእግዚአብሔር የተወገዙትን (ገላ 1፥9 እና ማብ ይመ) አስተማሪ ተብየዎችን ሁሉ አማኞች መመዘን አለባቸው::

(3) ለእንደነዚህ ዐይነቶቹ መምህራን የማበረታቻ ቃል እንዳይሰጥ፣ የገንዘብ ልግስና እንዳይደረግ ወይም ማንም በነላፊነታቸው ሥር እንዳይገኝ እግዚአብሔር ያዛል:: ከእነርሱ ጋር መተባበር ማለት በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ በሚያደርጉት ተቃውሞ መተባበር ነው፤ ከዚያም በቃሉ እውነት ላይ የተለሳለሰ አቋም ካላቸው መምህራን ጋር አብሮ መወገዝ ነው (ቊ 11)::

(4) በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ዮሐንስ የጻፈው ይህ ሥልጣን ያለው ቃል፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙት ብዙዎችን የሚያስቈጣ ነው:: እነዚህ ሰዎች

ሰላምም አትበሉት፤ 11የሚቀበለው ሰው፣
የክፉ ሥራው ተባባሪ ይሆናልና።
12የምጽፍላችሁ ብዙ ነገር ነበረኝ፤
ይሁን እንጂ በወረቀትና በቀለም እንዲሆን
አልፈልግም፤ ዳሩ ግን ደስታችን ፍጹም
ይሆን ዘንድ ወደ እናንተ መጥቼ ፊት ለፊት
ላነጋግራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።
13የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላ
ምታ ያቀርቡልሻል።

1፥11 1ጢሞ5፥22
1፥12 ዮሐ3፥29፤ 3ዮሐ1፥13፡14
1፥13 ቁ1

ይህ የዮሐንስ ምክር የፍቅር ለዛ ወይም የአንድነት መንፈስ የሌለው ይመስላቸዋል። ይሁን እንጂ የዮሐንስ ትምህርት ስሕተት መስሎ የሚታየው፣ ለክርስቶስ ክብርና ለቃሉ ባለሥልጣንነት ለማይጨነቁትና የእግዚአብሔርን እውነት ወደ ጐን በመተዋቸው ዘላለማዊት ነፍሳቸው ለጠፋባቸው ሰዎች ነው።

# የሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት - ሦስተኛ

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1)

I. ስለ ጋይዮስ መልካም ተግባርና ክርስቲያናዊ ሕይወት የተገለጸ አድናቆት (1፥2-8)
   (ሀ) ስለ መንፈሳዊ ጤንነቱ (1፥2)
   (ለ) በእውነት ስለ መመላለሱ (1፥3-4)
   (ሐ) ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ለሚያገለግሉ ወንድሞች ስለ አደገረው መስተንግዶ (1፥5-8)

II. ለጋይዮስ የተሰጠ ምክር (1፥9-12)
   (ሀ) ስለ ዲዮጥራጢስ መጥፎ ምሳሌነት (1፥9-11)
   (ለ) ስለ ድሜጥሮስ መልካም አርአያነት (1፥12)

*መደምደሚያ* (1፥13-14)

**ጸሐፊ፤** *ዮሐንስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በታማኝነት መሥራት*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *85—95 ዓ.ም.*

**ታሪካዊ ዳራ**

የተወደደው ሐዋርያ ዮሐንስ፣ "ሽማግሌ" በማለት በድጋሚ ራሱን ያስተዋውቃል (ቁ 1)፤ የሁለተኛ ዮሐንስን መልእክት መግቢያ ይመ):: ይህ ግላዊ መልእክት የተጻፈው ጋይዮስ ለተባለ ታማኝ ክርስቲያን ነው (ቁ 1)፤ ጋይዮስ በታናሹ እስያ በሚገኙት ክርስቲናያዊ ማኅበረ ሰቦች ውስጥ አባል ሳይሆን አይቀርም:: እንደ ሌሎቹ የዮሐንስ መልእክቶች ሁሉ፣ ሦስተኛው መልእክትም በሰማኒያዎቹ ዓመታት ማክተሚያ ወይም በዘጠናዎቹ ዓመታት መግቢያ ላይ በኤፌሶን ከተማ ሳይጻፍ አልቀረም::

በመጀመሪያው ምእት ዓመት መጨረሻ አካባቢ ከከተማ ወደ ከተማ እየተዘዋወሩ የሚያገለግሉ ወንጌላውያን፣ በቤታቸው ተቀብለው በሚያስተናግዷቸውና በጕዟቸው በሚረዷቸው አማኞች ብዙ ጊዜ ድጋፍ ይደረግላቸው ነበር (ቁ 5-8 ይመ፤ ከ2ዮሐ 1፥10 ጋር ያነጻጽሩ):: ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያከናውኑትን ተጓዥ አገልጋዮችን ከሚረዱ አያሌ ታማኝ ክርስቲያኖች መካከል ጋይዮስ አንዱ ነበር (ቁ 1-8):: ይሁን እንጂ ዲዮጥራጢስ የተባለው መሪ በትዕቢት መንፈስ ተነሣሥቶ የዮሐንስን ሥልጣን በመቃወም፣ ዮሐንስ የላካቸውን ተዘዋዋሪ ወንድሞች ለመርዳት ፈቃደኛ አልሆነም::

**ዐላማ**

ዮሐንስ ይህን መልእክት የጻፈው፣ ታማኝ የሆኑትን ተዘዋዋሪ አገልጋዮች ጋይዮስ በታማኝነት በመቀበሉና በመርዳቱ፣ እርሱን ለማመስገን፣ ዐመፀኛ የሆነውን ዲዮጥራጢስን ግን ኢርቱዕ በሆነ መልክ ለማስጠንቀቅና ለራሱ የወደፊት ጕብኝት መንገድ ለመጥረግ ነው::

**ቅኝት**

በሦስተኛው የዮሐንስ መልእክት ላይ ሦስት ሰዎች በስም ተጠቅሰዋል፤ (1) ጋይዮስ በእግዚአብሔር ፍርሀቱ በእውነት በመመላለሱ (ቁ 3-4)፣ ተዘዋዋሪ አገልጋይ ወንድሞችን አርአያነት ባለው መልኩ በእንግድነት በመቀበሉ (ቁ 5-8)፣ በእጅጉ ተመስግኖአል፤ (2) ፈላጭ ቈራጭ የሆነው መሪ ዲዮጥራጢስ ስለ ትዕቢቱና ("መሪ መሆን የሚወደው" ተብሎአል) ትዕቢቱም በገሃድ በመታየቱ፣ ይኸውም ከዚህ ቀደም ዮሐንስ የጻፈውን

መልእክት ንቆ ባለመቀበሉ (ቁ. 9)፣ ዮሐንስን በመሳደቡ፣ የዮሐንስን መልእክተኞች አልቀበልም በማለቱና የሚቀበሏቸውንም ከቤተ ክርስቲያን ለማባረር በመዛቱ (ቁ. 10) ተወግዞአል። (3) ድሜጥሮስ ምናልባትም ይህን መልእክት ያደርስ ዘንድ የተላከ አገልጋይ ወይም የአቅራቢ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኖ መልካም ዝና ያለውና ለእውነትም ታማኝ የሆነ ሰው በመሆኑ ተመስግኖአል (ቁ. 12)።

## ልዩ ገጽታ

ሦስተኛ የዮሐንስ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት ሁለት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ዐጭር ቢሆንም እንኳ፣ በመጀመሪያው ምእት ዓመት መጨረሻ ላይ ስለ መጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዋና ዋና ገጽታዎች ልዩ ግንዛቤን ይሰጣል። (2) በሦስተኛ ዮሐንስ መልእክትና በሁለተኛ ዮሐንስ መልእክት መካከል አስደናቂ የሆኑ ተመሳሳይነቶች አሉ፤ ይሁን እንጂ ሁለቱ መልእክቶች በአንድ ዐቢይ ገጽታ ላይ ይለያያሉ፤ ይኸውም ሦስተኛ ዮሐንስ መልእክት ታማኝ የሆኑትን ተዘዋዋሪ አገልጋዮች በእንግድነት መቀበል ተገቢ መሆኑን ሲያሳስብና ሲደግፍ፣ ሁለተኛ የዮሐንስ መልእክት ደግሞ እምነት የማይጣልባቸውን ሰዎች በእንግድነት መቀበልና መደገፍ ተገቢ አለመሆኑን ያስረዳል፤ ይኸውም አማኞች ስሕተትን ወይም ክፉን ሥራ ሲያራምዱ እንዳይገኙ ነው።

## ሦስተኛ የዮሐንስን መልእክት ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሦስተኛ የዮሐንስ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በአንድ ቀን መነበብ ይኖርበታል፤
❑ ሦስተኛ የዮሐንስ መልእክት

*ማስታወሻ*

ሽማግሌው፤
በእውነት ለምወደው ለውድ ወዳጄ፣ ለጋ
ይዮስ፤
2 ወዳጅ ሆይ፤ ነፍስህ በመልካም ሁኔታ
ላይ እንዳለች ሁሉ መልካም ጤንነት
እንዲኖርህና በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ
እጸልያለሁ። 3 ለእውነት ታማኝ እንደሆንህና
የምትመላለሰውም በእውነት እንደ ሆነ
አንዳንድ ወንድሞች መጥተው ስለ አንተ
ሲመሰክሩልኝ እጅግ ደስ አለኝ። 4 ልጆቼ
በእውነት የሚመላለሱ መሆናቸውን
ከመስማት የሚበልጥ ደስታ የለኝም።
5 ወዳጅ ሆይ፤ ለአንተ እንግዶች
ቢሆኑም እንኳ ለወንድሞች በምታደርገው
ነገር ሁሉ ታማኝ ነህ። 6 እነርሱ አንተ
ስላለህ ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ፊት
መስክረዋል፤ በመንገዳቸውም እግዚአብሔርን
ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ ብትረዳቸው መልካም
ታደርጋለህ፤ 7 ስለ ስሙ የወጡት ከአሕዛብ

1፥1 ሐሥ11፥30፤ 2ዮሐ1፥1
1፥3 ቊ5፡10፤ ሐሥ1፥16፤ 2ዮሐ1፥4
1፥4 ቊ3፤ 1ዮሐ2፥1
1፥5 ቊ3፤ ሮሜ12፥13፤ ዕብ13፥2
1፥6 1ቆሮ16፥11፤ 2ቆሮ1፥16፤ ኤፌ4፥1
1፥7 ዮሐ15፥21፤ ሐሥ20፥33፡35

**1፥2 በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ፤** አማኞች መልካም ጤንነት እንዲኖራቸውና ሕይወታችን በበረከቱ የተሞላ እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: ሁሉም ነገር ደኅና እንዲሆንልን ይኸውም ሥራችን፣ ዕቅዳችን፣ ዐላማችን፣ አገልግሎታችን፣ ቤተ ሰባችን፣ ወዘተ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት እንዲሳካልን ጌታ ይፈልጋል:: ስለዚህ በክርስቶስ ቤዛነት እውን የሚሆንልን የእግዚአብሔር በረከት የታቀደው፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ መሻታችንን እንዲያሟላ ነው::

ስለ ተሳካ ኑሮና ስለ መንፈሳዊ ብልጽግና መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ያስተምራል፦ (1) "በነገር ሁሉ እንዲሳካልህ" የሚለውን ሐረግ የሚተካው ቃል፣ የግሪክ ቃል፣ "ኤዩዱ" የሚል ሲሆን፣ ትርጕሙም፣ "መልካም ጕዞ ይሁንልህ፤ መንገድህ ቀና ይሁንልህ" ማለት ነው:: በዚህ ትርጕም መሠረት የዮሐንስ ቀዳሚ ጸሎት፣ አማኞች በድነት መንገድ ሲጓዙ፣ በእግዚአብሔር ፈቃድና በእርሱ እውነት ምንጊዜም ጸንተው በመገኘት የጌታን በረከት እንዲያገኙ ነው (ከቊ 3-4 ጋር ያነጻጽሩ)::

(2) ለራሳችንና ለቤተ ሰባችን መጠለያ፣ ምግብና ልብስ ለማሟላት፣ ሌሎችንም ለመርዳትና የክርስቶስን ዐላማ ለማስፈጸም ሲባል (ፊል 4፥15-19) በቂ ገንዘብ እንድናገኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ለመስጠት እንደሚችል (2ቆሮ 9፥8-12)፣ "እንደ ታላቅ ባለጠግነቱ መጠን … በክርስቶስ" ሊሰጠን ቃል እንደ ገባ እናውቃለን (ፊል 4፥19 ይመ፤ በገጽ 100 ላይ፣ "*መግቦተ እግዚአብሔር*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(3) እግዚአብሔር ለኑሯችን የሚያስፈልገንን ሁሉ እንዲሰጠን ልንጸልይ ብንችልም፣ እርሱ ልጆቹ በችግር ሕይወት ውስጥ ያልፉ ዘንድ የሚፈቅደውን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ማስተዋል አለብን። (ሀ) በእርሱ እንድንተማመን ለማበረታታትና እምነታችንን፣ መንፈሳዊ ጽናታችንንና አገልግሎታችንን ለማሳደግ ሲባል ዕጦት ሊያጋጥመን ወይም በችግር ውስጥ ልናልፍ እንችላለን (ሮሜ 8፥35-39፤ 2ቆሮ 4፥7-12፤ 6፥4-10፤ 12፥7-10፤ 1ጴጥ 1፥6-7):: (ለ) ስለ ጌታ ኢየሱስ ስንል በምንመሰክረውና እርሱን በማገልገላችን ከዓለም ከሚመጣው ስደትና እንግልት የተነሣ ከባድ መከራ ውስጥ ልናልፍ እንችላለን (ሉቃ 6፥20-23፤ ዕብ 10፥32-34፤ 1ጴጥ 2፥19-21፤ ራእ 2፥9-10 ይመ፤ በገጽ 744 ላይ፣ "*የጻድቃን መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: (ሐ) ከብሔራዊ ወይም ከተፈጥሮ ክሥተት ማለትም ከጦርነቱ፣ ከራብ፣ ከድርቅ ወይም ከዝቅተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ወይም ከማኅበራዊ ሁኔታዎች የተነሣ ችግር ሊደርስብን ይችላል (ሐሥ 11፥28-30፤ 2ቆሮ 8፥2፡12-14)::

(4) ለሥጋዊ ሕይወታችን የእግዚአብሔር ሀልዎት፣ ርዳታና በረከት መኖር ከመንፈሳዊ ሕይወታችን ጋር የተያያዘ ነው፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሻት አለብን (ማቴ 6፥10፤ 26፥39፤ ዕብ 10፥7-9)፤ መንፈስ ቅዱስን መታዘዝ አለብን (ሮሜ 8፥14)፤ ከዓለም አካሄድ እንደ ተለየን መቅረት አለብን (ሮሜ 12፥1-2፤ 2ቆሮ 6፥16-18)፤ የእግዚአብሔርን ቃል መውደድ አለብን (ያዕ 1፥21፤ 1ጴጥ 2፥2)፤ በጸሎት ሆነን የእግዚአብሔርን ርዳታ መፈለግ አለብን (ማቴ 6፥9-13፤ ዕብ 4፥16)፤ ጠንክረን መሥራት (2ተሰ 3፥6-12)፤ የሚያስፈልገንን እንደሚሰጠን በእርሱ ላይ መታመን (ማቴ 6፥25-34፤ 1ጴጥ 5፥7) እንዲሁም አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን መፈለግ በሚለው መርሕ መሠረት መኖር አለብን (ማቴ 6፥33 ይመ፤ ማቴ 6፥11 እና ማብ፤ ሉቃ 11፥3 እና ማብ፤ ቈላ 4፥12 እና ማብ ይመ፤ እ 1430 ላይ፣ "*መለኮታዊ ፈውስ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)::

(5) የእያንዳንዳችን ነፍስ በመልካም ሁኔታ ያለች ብትሆንም እንኳ፣ በሌላው የሕይወታችን ፈርጅ ከመቅጽበት ከችግር አንላቀቅም:: የሚያጋጥመንን መከራ፣ ችግርና ዕጦት በጸሎትና በእግዚአብሔር ላይ እምነትን በመጣል ልንጋፈጠው ያስፈልጋል::

**1፥5 *ታማኝ ነህ፤*** ጋይዮስ በአንድ በተወሰነ አቅጣጫ በእውነት በመመላለሱ ዮሐንስ ያመሰግነዋል (ቊ 3-4)፤ ይኸውም ተዘዋዋሪ ሚስዮናውያንን በታማኝነት በመርዳቱ ነው (ቊ 5-8)፤ ማረፊያ ቤት፣ ምግብ፣ ገንዘብና ለጕዟቸው ሊያስፈልጋቸው የሚችለውን ነገር ሁሉ ሰጥቶአቸው (ከቲቶ 3፥13 ጋር ያነጻጽሩ):: ጋይዮስ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሚስዮናዊ ዐላማ የነበረው መሰጠት አስደናቂ ስለ ነበር፣ ሚስዮናውያኑ ራሳቸው ይህንኑ ለዮሐንስ ገለጹለት (ቊ 6):: ጋይዮስ ለእነዚህ ሰባኪዎች ይህን በጎ ነገር ያደረገላቸው ለእነርሱ፣ ለወንጌልና ጌታ ክርስቶስን አዳኝ አድርገው ላልተቀበሉት ሰዎችም ካለው ፍቅር የተነሣ ነው::

**1፥7 ስለ ስሙ፤** ከቊ 5-8 ያለው ክፍል ለክርስቶስ ወንጌል ሲሉ ተዘዋዋሪ የወንጌል መልእክተኞች ስለ ሆኑት ያመለክታል:: ለሚስዮናዊ ተግባር አስፈላጊ ለሆነውና ለሥራው ሁሉ ይሆን ዘንድ አስተዋፅኦ ማድረግ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተግባርና መብት ነው:: (1) ሚስዮናውያንን የመቀበል፣ የመላክና የመርዳት ተግባር መከናወን የሚገባው እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ መሆን አለበት (ቊ 6፤ 1ቆሮ 9፥14፤ ፊል 4፥10-18):: እንደ ለማኝ መቈጠር የለባቸውም፤ ነገር ግን ጌታን በምንቀበልበት መልክ ልንቀበላቸው ይገባል (ማቴ 10፥40)፤ ለዓለም ሁሉ ወንጌልን የሚያደርሱ የእርሱ አገልጋዮች ተደርገው መታየትም አለባቸው (ማቴ 28፥19 እና ማብ ይመ)::

(2) በቀዳሚዋ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ሚስዮናውያንን መላክ፣ ለጕዟቸው የሚያስፈልገውን መስጠትን፣ ለምግብም የሚሆነውን አሟልቶ ማቅረብን፣ ለማንኛውም

ምንም ሳይቀበሉ ነውና። 8እንግዲህ አብረን
ለእውነት እንድንሠራ እንዲህ ያሉትን
ሰዎች ልናስተናግድ ይገባናል።
9ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጽፌ ነበር፤ ነገር
ግን መሪ መሆን የሚወደው ዲዮጥራጢስ
አይቀበለንም። 10ስለዚህ እኔ ከመጣሁ
እርሱ በክፉ ቃላት ስማችንን ለማጥፋት
የሚያደርገውን ሁሉ ይፋ አወጣለሁ፤ ይህም
አልበቃ ብሎት ወንድሞችን አይቀበልም፤
ሊቀበሏቸው የሚፈልጉትን ይከለክላቸዋል፤
ከቤተ ክርስቲያንም ያስወጣቸዋል።
11ወዳጅ ሆይ፤ መልካም የሆነውን እንጂ
ክፉውን አትምሰል። መልካም የሆነውን

1፥10 ቆላ5፡14፤
ዮሐ9፥22፡34፤
2ዮሐ1፥12
1፥11
መዝ34፥14፤
37፥27፤
1ዮሐ2፥29፤
3፥6፡9፡10
1፥12 ዮሐ19፥35፤
21፥24፤
1ጢሞ3፥7
1፥14 ዮሐ10፥3፤
ሮሜ1፥7፤
ኤፌ6፥23፤
2ዮሐ1፥12

የሚያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ክፉ
የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም።
12ለድሜጥሮስ፣ ሰው ሁሉ ይመሰክርለታል፤
እውነት ራሷም ትመሰክርለታለች፤ እኛ
ደግሞ እንመሰክርለታለን፤ እናንተም
ምስክርነታችን እውነት እንደሆነ
ታውቃላችሁ። 13የምጽፍልህ ብዙ ነገር
ነበረኝ፤ ይሁን እንጂ በቀለምና በብርዕ
እንዲሆን አልፈልግም፤ 14በቅርቡ
ላይህ ተስፋ አደርጋለሁ፤ ፊት ለፊትም
እንነጋገራለን። 15ሰላም ለአንተ ይሁን፤
ወዳጆች ሰላምታ ያቀርቡልሃል። ለወዳጆች
በየስማቸው ሰላምታ አቅርብልኝ።

ጉዳይ ወጭ የሚሆነውንና ያለጭንቀት የሚኖሩበትን ገንዘብ መክፈልንም ያካትታል (ገላ 6፥6-10 እና ማብ፤ ፊል 4፥16 እና ማብ ይመ፤ ቲቶ 3፥13 ይመ)። ሚስዮናውያንን በመርዳት የእግዚአብሔር ሰዎች እውነትን በማሠራጨት ተግባር አንድ አካል ሆነው ሠርተዋል (ቁ 8)።

**1፥7 ከአሕዛብ ምንም ሳይቀበሉ፤** የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ለማወጅ ቤት ንብረታቸውን ትተው ወደ ሌሎች ቦታዎች የሚሄዱ ሚስዮናውያን፣ ገና ወደ ክርስቶስ ከሚያመጧቸውና ካላመኑት ሰዎች ምንም ዐይነት ርዳታ ላለመቀበል ቊርጠኞች መሆን አለባቸው። ከማያምኑ ሰዎች ርዳታን መቀበል፣ ሚስዮናዊው ገንዘብ ለማግኘት ሲል ወንጌልን የሰበከ ስለሚያስመስልና አሉባልታን ስለሚያስነሣ፣ የወንጌል ሥርጭትን ሊያደናቅፍ ይችላል (ከ1ቆሮ 9፥12 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ሚስዮናውያን ርዳታን መቀበልና ማግኘት ያለባቸው ከግለሰብ አማኞችና ከቤተ ክርስቲያን ነው (ሉቃ 10፥7፤ 1ቆሮ 9፥14፤ 1ጢሞ 5፥18)። ለቤተ ክርስቲያናችን በሚስዮናዊ ተግባር ረገድ አስተዋፅኦ ስናደርግ፣ "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ያገኛል፤ ጻድቅን በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቅን ዋጋ ያገኛል" (ማቴ 10፥41 እና ማብ ይመ) የሚለውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ማስታወስ ይኖርብናል።

# የያዕቆብ ወንድም የይሁዳ መልእክት

*አስተዋፅኦ*

ለክርስቲያኖች የቀረበ ሰላምታ (1፥1-2)

I. መልእክቱ ለምን እንደተጻፈ የተሰጠ መግለጫ (1፥3-4)

II. የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ማጋለጥ (1፥5-16)

(ሀ) እንደሚጠፉ አስቀድሞ መገለጹ (1፥5-7)

1. በእስራኤልም ላይ ጥፋት መድረሱ (1፥5)
2. በማያምኑና ዐመፃ ባካሄዱ መላእክት ላይ የደረሰው ጥፋት (1፥6)
3. የሰዶምና የገሞራ መጥፋት (1፥7)

(ለ) በአሁኑ ጊዜ ምን እንደሚመስሉ (1፥8-16)

1. የሚሳደቡ (1፥8-10)
2. ቅድስና የሌላቸው (1፥11)
3. ጥፋተኞች (1፥12-16)

III. ለእውነተኛ አማኞች የተሰጠ ምክር (1፥17-23)

(ሀ) በሐዋርያት አስቀድሞ የተነገረውን ትንቢት እንዲያስቡ (1፥17-19)

(ለ) በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳቸውን እንዲጠብቁ (1፥20-21)

(ሐ) እግዚአብሔርን እየፈሩ ምሕረት በማድረግ ሌሎችን እንዲረዱ (1፥22-23)

ቃለ ውዳሴ (1፥24-25)

**ጸሐፊው፤** *ይሁዳ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ለእምነት ተጋድሎ ማድረግ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *70—80 ዓ.ም.*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይሁዳ፣ "የያዕቆብ ወንድም" (ቍ 1) እንደሆነ በመግለጽ ራሱን ያስተዋውቃል:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ "የኢየሱስ ወንድሞች" ተብለው የተጠሩት ይሁዳና ያዕቆብ ብቻ ናቸው (ማቴ 13፥55፣ ማር 6፥3):: ያዕቆብ በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን በመሪዎቹ ታዋቂ ስለነበር፣ ይሁዳ የእርሱ ወንድም መሆኑን መጠቆም የፈለገው የራሱን ማንነትና ሥልጣን ለመግለጽ በማሰብ ይሆናል::

ይህ አጭር ነገር ግን ጠንካራ መልእክት የተጻፈው፣ በጸጋ ድነናልና ኀጢአት ብንሠራም አይፈረድብንም ብለው በድፍረት የሚያስተምሩትን እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይና ሰው መሆን አስቀድሞ በሐዋርያት የተነገረውን መገለጥ አጥብቀው የሚክዱትን (ቍ 4) የሐሰት አስተማሪዎች በመቃወም ነው:: ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በተሳሳተ እምነታቸው (ቍ 19:22) እና በክፉ ድርጊታቸው (ቍ 4:8:16) አብያተ ክርስቲያናትን ይከፋፍላሉ:: ይሁዳ እነዚህን ሥርዓት የሌላቸው ሰዎች፣ "ዐመፀኞች" (ቍ 15)፣ "መንፈስም የሌላቸው" (ቍ 19) በማለት ይገልጻቸዋል::

በይሁዳ መልእክትና በ2ጴጥ 2፥1—3፥4 መካከል ሊኖር ይችላል የሚባለው ግንኙነት፣ የይሁዳ መልእክት መቼ እንደተጻፈ ማስረጃ ሊሆን ይችላል:: ይሁዳ ከሁለተኛ ጴጥሮስ ጋር (ቍ 17-18) ይበልጥ የተቀራረበ በመሆኑ፣ የተጻፈው ከጴጥሮስ በኋላ ምናልባት ከ70—80 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ይሆናል:: የመልእክቱ ተደራሲያን በግልጽ አልተጠቀሱም፤ ምናልባት በሁለተኛ ጴጥሮስ የተጠቀሱት ተደራሲያን ራሳቸው ሊሆኑ ይችላሉ (የሁለተኛ ጴጥሮስን መግቢያ ይመልከቱ)

### ዐላማ

ይሁዳ ይህን መልእክት የጻፈው፣ (1) ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎች አደገኛ አካሄድና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚያደርጉት አፍራሽ እንቅስቃሴ አማኞች ፈጥነው እንዲያውቁት ለማድረግ እንዲሁም (2) እውነተኛ አማኞች እንዲነሡና "ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት" እንዲጋደሉ (ቍ 3) ግፊት ለመስጠት ነው።

### ቅኝት

ይሁዳ ሰላምታ ካቀረበ በኋላ (ቍ 1-2) በመጀመሪያ ድነትን በሚመለከት ሊጽፍላቸው አስቦ ነበር (ቍ 3)፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ አጣምመው በመተርጐም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እውነትንና ጽድቅን መፈለግ እንዳይኖር (ቍ 4) የሚያደርጉትን የሐሰት አስተማሪዎች ሁኔታ ስላሠጋው፤ ይህን መልእክት ለመጻፍ እንደተገደደ ይገልጻል። ይሁዳ ሴሰኝነታቸውን (ቍ 4:8:16:18) በቃየል መንገድ መሄዳቸውን (ቍ 11) እንደ በለዓም ስግብግብ (ቍ 11) እንደ ቆሬ ዐመፀኞች (ቍ 11) መሆናቸውን ከመግለጹም በላይ ግትርነታቸውን (ቍ 8:16)፣ አታላይነታቸውን (ቍ 4:12)፣ ሥጋዊነታቸውንና (ቍ 19) የሚለያዩ መሆናቸውንም (ቍ 19) አመልክቶአል። ይህን የመሰለውን ኀጢአት በሚያደርጉ ሁሉ ላይ የእግዚብሔር ፍርድ የማይቀር መሆኑን ይናገራል፤ ይህንም በይበልጥ ለመግለፅ ስድስት የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎችን በማስረጃነት ያቀርባል (ቍ 5-11)፤ ሕይወታቸው ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተጠቀሱት ዐሥራ ሁለት ገለጻዎች የእግዚአብሔር ቍጣ በእነርሱ ላይ መምጣት የሚያስፈልግበት ደረጃ ላይ የደረሱ መሆናቸውን ያመለክታሉ (ቍ 12-16)። አማኞች ራሳቸውን እንዲጠብቁና በሕይወታቸው እየዋገቁ ላሉትም (ቍ 20-23) እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲራሩላቸው አጥብቆ ይመክራል። ይሁዳ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በመመልከት አስደናቂነቱ እየጨመረ የሚሄድ ምስጢራዊ ቃል ገልጾ በመናገር መልእክቱን ይደመድማል (ቍ 24-25)።

### ልዩ ገጽታ

የይሁዳ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከተጠቀሱት ሁሉ ይልቅ የይሁዳ መልእክት በግልጽና ጠንከር ባለ ሁኔታ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ያወግዛል፤ የሐሰት ትምህርት በዘመናት ሁሉ ለእውነተኛ እምነትና ለቅዱስ ኑሮ ዕንቅፋት በመሆኑ አጥብቆ ያስጠነቅቃል፤ (2) ገላጻው በተለያዩ ሦስትዮሽ ምሳሌዎች የተደገፈ ነው፣ ለምሳሌ ሦስት የብሉይ ኪዳን የፍርድ ምሳሌዎች (ቍ 5-7)፣ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ማንነት የሚያመለክቱ ሦስት ገለጻዎች (ቍ 8)፣ በርኩሰት ሕይወት የተመላለሱ ሰዎችን የሚያሳይ ሦስት የብሉይ ኪዳን ምሳሌዎች (ቍ 11) ናቸው (3) ይሁዳ ሙሉ በሙሉ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት መሠረታዊ የሆኑ ዋቢ ጽሑፎችን በግልጽ ያመለክታል፤ (ሀ) የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት (ቍ 5-7:11)፣ (ለ) የአይሁድ የሕግ መጻሕፍት (ቍ 9:14-15) (ሐ) ሁለተኛ ጴጥሮስ በተለይም 3፥3፤ ይህም በሐዋርያት አፍ የተነገረ መሆኑን ይገልጻል (ቍ 17-18)፣ (4) በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከማንኛውም መልእክት ይልቅ የእግዚአብሔርን ክብርና ግርማ የሚገልጽ ማጠቃለያ ቡራኬ ይዞአል።

### የይሁዳ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ የይሁዳ መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በ1 ቀን መነበብ ይኖርበታል። 1ቀን ❑ ይሁዳ

*ማስታወሻ*

የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆብ
ወንድም ይሁዳ፤
ለተጠሩት፣በእግዚአብሔርአብለተወደዱትና
በኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠበቁት[ሀ]፤
2ምሕረት፣ ሰላምና ፍቅር ይብዛላችሁ።

## የዐመፀኞች ኀጢአትና የሚጠብቃቸው ፍርድ

3ወዳጆች ሆይ፤ አብረን ስለምንካፈለው
ድነት ልጽፍላችሁ እጅግ ጓጕቼ ነበር፤
ነገር ግን ለቅዱሳን አንዴና ለመጨረሻ ስለ
ተሰጠው እምነት እንድትጋደሉ ለመምከር
እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ። 4ከረጅም
ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ[ለ] የተጻፉ አንዳንድ
ሰዎች ሾልከው ወደ እናንተ ገብተዋልና፤
እነርሱ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው፣
የአምላካችንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡና
እርሱ ብቻ ልዑል ገዥችንንና ጌታችንን የሆነውን
ኢየሱስ ክርስቶስን የሚክዱ ናቸው።
5ምንም እንኳ አስቀድማችሁ ይህን
ሁሉ የምታውቁ ቢሆንም፣ ጌታ[ሐ] ሕዝቡን
ከግብፅ ምድር እንዴት እንዳወጣ፣ በኋላ
ግን ያላመኑትን እንዳጠፋ ላስታውሳችሁ
እወዳለሁ። 6የሥልጣን ስፍራቸውን
ያልጠበቁትን ነገር ግን መኖሪያቸውን
የተዉትን መላእክት በዘላለም እስራት
እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ በጨለማ
ጠብቆአቸዋል። 7እንዲሁም ሰዶምና ገሞራ፣
በዙሪያቸውም ያሉ ከተሞች ለሴሰኝነትና
ከተፈጥሮ ሥርዐት ውጭ ለሆነ ሩካቤ ሥጋ
ራሳቸውን አሳልፈው ሰጡ፤ እነርሱም
በዘላለም እሳት በመቀጣት ለሚሠቃዩት
ምሳሌ ሆነዋል።
8በዚህ ሁኔታ እነዚህ ሕልም አላሚዎች
የገዛ ሥጋቸውን ያረክሳሉ፤ ሥልጣንን
ይቃወማሉ፤ በሰማይ ክብር ያላቸውንም

1፥1 ማቴ13፥55፤ ዮሐ14፥22፤ 17፥12፤ ሐሥ1፥13፤ ሮሜ1፥1፡6፥7
1፥2 ሮሜ1፥7፤ ገላ6፥16፤ 1ጢሞ1፥2
1፥3 ቍ20፤ ሐሥ6፥7፤ 9፥13፤ 1ቆሮ10፥14፤ 1ጢሞ6፥12፤ ቲቶ1፥4
1፥4 ገላ2፥4፤ ቲቶ1፥16፤ 2ጴጥ2፥1፤ 1ዮሐ2፥22
1፥5 ዘኍ14፥29፤ ዘዳ1፥32፤ 2፥15፤ መዝ106፥26፤ 1ቆሮ10፥1-5፤ ዕብ3፥16፡17፤ 2ጴጥ1፥12፡13፤ 3፥1፡2፤ 1ዮሐ2፥20
1፥6 2ጴጥ2፥4፡9 1፥7 ዘዳ29፥23፤ ማቴ10፥15፤ 25፥41፤ 2ጴጥ3፥7 1፥8 2ጴጥ2፥10

*[ሀ]1፥1 ወይም የተጠበቁት ሊሆን ይችላል*
*[ለ]1፥4 ወይም ፍርድ የተወሰነባቸውን ሰዎች*
*[ሐ]1፥5 አንዳንድ የጥንት ቅጆች ኢየሱስ ይላሉ*

**1፥2 ምሕረት ... ይብዛላችሁ፤** “ይብዛላችሁ” (በግሪክ ቋንቋ፣ “ፕሌቱኖ”) የሚለው ቃል በቃል ሲተረጎም “ይጨመርላችሁ” ማለት ነው። ወደ እግዚአብሔር በቀረብን ቍጥር ምሕረቱ፣ ሰላሙና ፍቅሩ እየበዛልን ይሄዳል።

**1፥3 ለቅዱሳን ... ስለተሰጠው እምነት፤** ለክርስቶስ ታማኝ የሆኑት እግዚአብሔር ለሐዋርያትና ለቅዱሳን ስለ ሰጠው እምነት እንዲጋደሉ ከባድ ግዴታ ውስጥ ገብተዋል (ፊል 1፥27 ይመ፤ ከ1ጢሞ 1፥18-19፤ 6፥12 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (1) ይህ እምነት በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰበከውን ወንጌል ይዞአል፤ በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠና በአዲስ ኪዳን የተገለጸ ሲሆን፣ የተወሰነና የማይለወጥ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ይህ “እምነት” ተጨባጭ እውነት ከመሆኑም ባሻገር፣ በፍቅርና በንጽሕና ሊኖሩት የሚገባ የሕይወት መንገድ ነው (ቈላ 1፥9-11፤ 1ጢሞ 1፥5)፤ ድንቅንና ታምራትን በማድረግ እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በመቀበል (ሐሥ 2፥22፤ 14፥3፤ ሮሜ 15፥19፤ ዕብ 2፥4 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1527 ላይ፣ “*አማኞች የሚከተሉአቸው መንፈሳዊ ምልክቶች*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ያውጅ ዘንድ (ማር 16፥15-17፤ 1ተሰ 1፥5 እና ማብ) አማኞችን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ለማጥመቅ በሥልጣን ወደሚመጣው መንግሥት የሚያስገባ ነው (በገጽ 1664 ላይ፣ “*በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ*” በሚል እና በገጽ 1443 ላይ፣ “*የእግዚአብሔር መንግሥት*” በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኵረት ጽሑፎች ይመ)።

(2) “*መጋደል*” (በግሪክ ቋንቋ፣ “ኤፓጎኒዞማይ”) የሚለው ቃል ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለመጠበቅ ሊያደርጉት የሚገባቸውን ውጊያ ያመለክታል። ቃል በቃል ሲተረጎም “*መታገል*”፣ “*መከራ መቀበል*”፣ “ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ *መግባት*” ወይም “*ውጊያ መዋጋት*” ማለት ነው። ከፍተኛ መሥዋዕትነት የሚጠይቅና መከራ ያለበት ቢሆንም፣ የእግዚአብሔርን ቃልና የአዲስ ኪዳንን እምነት ለመጠበቅ የተቻለንን ጥረት ሁሉ ማድረግ ይገባናል። ራሳችንን መካድ ብቻ ሳይሆን ሁኔታው ገፍቶ ሲመጣ ስለ ወንጌል ሰማዕትነት ለመቀበልም የተዘጋጀን መሆን ይገባናል (ከ2ጢሞ 4፥7 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) ስለ እምነት መጋደል ሲባል፣ (ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን የማይቀበሉትን እንዲሁም በክርስቶስና በሐዋርያት የተገለጸውን የመጀመሪያውን እምነት የሚያጣምሙትን አጥብቆ በመቃወም ግልጽ የሆነ ዐቋም መያዝ እና (ለ) ቤዛነትን የሚያስገኝ እውነት መሆኑን ለሰዎች ሁሉ መናገር ማለት ነው (ዮሐ 5፥47 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1941 ላይ፣ “*መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ለክርስቶስና ለአዲስ ኪዳን እምነት ለመቆም ኀላፊነት ያለባቸው ሰዎች የወንጌልን ሥልጣን ለድርድር በማቅረብ፣ እውነቱን በማጣመም፣ ምክንያትን እየደረደሩ ኀይሉንና ተስፋውን በማሳነስ መልእክቱን የሚያዳክሙትን ችላ ማለት የለባቸውም።

**1፥4 የአምላካችንን ጸጋ በርኵሰት የሚለውጡ፤** በጸጋ የዳኑ ክርስቲያኖች አብዝተው ኀጢአት ቢሠሩም እንኳ እግዚአብሔር አይፈርድባቸውም ብለው የሚያስተምሩትን ሰዎች ይሁዳ አጥብቆ ያወግዛል። በዝሙት ኀጢአት የተጠመዱትን ሰዎች እግዚአብሔር በቀላሉ ይቅር እንደሚላቸው ወይም ዛሬ በስነ ምግባር ብልሹነት የሚኖሩ ሰዎች ቀደም ሲል በክርስቶስ ያምኑ የነበረ ከሆነ የዘላለም ሕይወት የማግኘታቸው ጉዳይ የተጠበቀ ነው ብለው ሳያስተምሩ አይቀርም (ከሮሜ 5፥20፤ 6፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)። የኀጢአት ይቅርታ ማግኘት እንደሚቻል ሲሰብኩ ነገር ግን በቅድስና መኖር እንደሚያስፈልግ የተሰጠውን ትእዛዝ ችላ ብለውታል።

**1፥6 መላእክት፤** የይሁዳ መልእክት መጀመሪያ የነበራቸውን የሥልጣን ስፍራ ባለመጠበቅ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁትን፣ ሕጉን የጣሱትን፣ አሁን በእስር ሆነው ፍርድ የሚጠብቁትን መላእክት ይጠቅሳል። ይሁን እንጂ ሰይጣንና ብዙ አጋንንት አሁን በምድር ላይ እየሠሩ ስላሉ፤ ታስረው ያሉት የወደቁት መላእክት ሁሉ አይደሉም (2ጴጥ 2፥4 እና ማብ እንዲሁም 1ዮሐ 5፥19 እና ማብ ይመ)።

**1፥8 ሥልጣንን ይቃወማሉ፤** 2ጴጥ 2፥10 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

ፍጥረታት ይሳደባሉ። 9የመላእክት አለቃ
የሆነው ሚካኤል እንኳ ስለ ሙሴ ሥጋ
ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ፣ "ጌታ
ራእ ይገሥጽህ" አለው እንጂ የስድብ ቃል
12፥7-11 በመናገር ሊከሰው አልደፈረም። 10እነዚህ
ሰዎች ግን የማያውቁትን ነገር ሁሉ
ይሳደባሉ፤ አእምሮ እንደሌላቸው እንስሳት
በደመ ነፍስ በሚያወቁት ነገር ይጠፋሉ።
11ወዮላቸ! በቃየን መንገድ ሄደዋል፤
ለገንዘብ ሲስገበገቡ በበለዓም ስሕተት ውስጥ
ወድቀዋል፤ በቆሬም ዐመፅ ጠፍተዋል።
12እነዚህ ሰዎች በፍቅር ግብዣችሁ ላይ
ያለ አንዳች ኀፍረት ከእናንተ ጋር ቀርበው
የሚበሉ ነውረኞች ናቸው፤ ደግሞም
ራሳቸውን ብቻ የሚመግቡ እረኞች ናቸው፤
እነርሱም በነፋስ የሚነዱ ዝናብ የሌላቸው
ደመናዎች ናቸው፤ በመከር ወራት ፍሬ
የማይገኝባቸው ከሥራቸው ተነቅለው ሁለት
ጊዜ የሞቱ ዛፎች ናቸው። 13የነውራቸውን
አረፋ የሚደፍቁ የተቈጡ የባሕር ማዕበል፣
ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የሚጠብቃቸው
ተንከራታች ከዋክብት ናቸው።
14ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ
ስለ እነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ተንብዮአል፤
"እነሆ፤ ጌታ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳኑ
ጋር ይመጣል፤ 15ይህም፣ በሰው ሁሉ ላይ
ለመፍረድ እንዲሁም ዐመፀኞችን ሁሉ
በክፋት መንገድ በሠሩት የዐመፅ ሥራና
ራእ በክፋት በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩት የስድብ ቃል
1፥7 ሁሉ አጥፊነታቸውን ይፋ ለማድረግ ነው"።
16እነዚህ ሰዎች የሚያጕረመርሙና ሌሎችን
ሰዎች የሚከሱ ናቸው፤ ርኩስ ምኞታቸውን
ይከተላሉ፤ በራሳቸው ይታበያሉ፤
ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ሌሎችን ይክባሉ።

1፥9 ዘዳ34፥6፤ ዳን10፥13፡21፤ 12፥1፤ ዘካ3፥2፤ 1ተሰ4፥16፤ ራእ12፥7
1፥10 2ጴጥ2፥12
1፥11 ዘፍ4፥3-8፤ ዘኍ16፥1-3፡31-35፤ ዕብ11፥4፤ 2ጴጥ2፥15፤ 1ዮሐ3፥12
1፥12 ምሳ25፥14፤ ሕዝ34፥2፡8፡10፤ ማቴ15፥13፤ 1ቆሮ11፥20-22፤ ኤፌ4፥14፤ 2ጴጥ2፥13፡17
1፥13 ኢሳ57፥20፤ ፊል3፥19፤ 2ጴጥ2፥17
1፥14 ዘፍ5፥18፡21-24፤ ዘዳ33፥2፤ ዳን7፥10፤ ዘካ14፥5፤ ማቴ16፥27፤ ዕብ12፥22
1፥15 1ጢሞ1፥9፤ 2ጴጥ2፥6-9
1፥16 ቍ18፤ 1ቆሮ10፥10፤ 2ጴጥ2፥10፡18
1፥17 ኤፌ4፥11፤ ዕብ2፥3፤ 2ጴጥ3፥2
1፥18 ቍ16፤ 1ጢሞ4፥1፤ 2ጢሞ3፥1፤ 2ጴጥ2፥1፤ 3፥3
1፥19 1ቆሮ2፥14፡15
1፥20 ቍ3፤ ኤፌ6፥18፤

## ጸንቶ ስለ መቆም የቀረበ ጥሪ

17ነገር ግን ወዳጆች ሆይ፤ የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው
የተናገሩትን አስታውሱ። 18እነርሱም፣
"በመጨረሻው ዘመን ርኩስ ምኞታቸውን
የሚከተሉ ዘባቾች ይመጣሉ" ብለዋችኋል።
19እነዚህ ሰዎች በመካከላችሁ መለያየትን
የሚፈጥሩ፣ በደመ ነፍስ የሚነዱ መንፈስ
የሌላቸው ናቸው።
20እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፤ እጅግ
ቅዱስ በሆነው እምነታችሁ ራሳችሁን
ለማነጽ ትጉ፤ በመንፈስ ቅዱስም ጸልዩ።
21ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት
ስትጠባበቁ ሳለ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር
ራሳችሁን ጠብቁ።
22ተጠራጣሪ ለሆኑት ራሩላቸው፤
23አንዳንዶችን ከእሳት ነጥቃችሁ
አድኗቸው፤ ለሌሎች ደግሞ በርኩስ ሥጋ
የተበከለውን ልብሳቸውን እንኳ እየጠላችሁ
በፍርሀት ምሕረት አሳዩአቸው።

## ቃለ ውዳሴ

24እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ
ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ
ለሚችለው፣ 25እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው
አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል
ከዘመናት ሁሉ በፊት፣ አሁንና እስከ
ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና
ሥልጣን ይሁን፤ አሜን።

1፥20 ቈላ2፥7፤ 1ተሰ5፥11 1፥21 ማቴ25፥46፤ ቲቶ2፥13፤ ዕብ9፥28፤ 2ጴጥ3፥12 1፥23 አሞ4፥11፤ ዘካ3፥2-5፤ 1ቆሮ3፥15፤ ራእ3፥4 1፥24 ሮሜ16፥25፤ 2ቆሮ4፥14፤ ቈላ1፥22 1፥25 ዮሐ5፥44፤ ሮሜ11፥36፤ 1ጢሞ1፥17፤ ዕብ13፥8

**1፥9 ሚካኤል ... ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ፤** ዋነኛ የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ እግዚአብሔር በሰይጣን ላይ እርምጃ እንዲወስድ ለእርሱ አሳልፎ ከመስጠት በቀር በሰይጣን ላይ የስድብ ቃል አልተናገረም፤ እኛስ ሰዎች በማንኛውም ነገር ላይ በርኩሳን መናፍስት ላይ እንኳ ሳይቀር የስድብ ቃል ከመናገር ምን ያህል አብልጠን ልንጠነቀቅ ይገባናል (2ጴጥ 2፥11)?

**1፥12 ሁለት ጊዜ የሞቱ፤** በይሁዳ መልእክት ተደራሲያን መካከል የሚገኙ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች "ሁለት ጊዜ የሞቱ" ናቸው:: እነዚህ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በአንድ ወቅት "ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገሩ" (ዮሐ 5፥24) በክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ነበሩ፤ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ከክርስቶስ ጋር የነበራቸውን ኅብረት አበላሽተው እንደገና ከሕይወት ወደ ሞት የሄዱ ናቸው (ከኤፌ 2፥1 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሮሜ 8፥13 እና ማብ ይመ):: ከዚህ በፊት ያለው ጥቅስ መንፈሳዊ ሞት ይሞቱ ዘንድ ምክንያት የሆነውን ነገር ይገልጻል::

**1፥14 ሄኖክ ... ተንብዮአል፤** ይሁዳ ይህን የጠቀሰው ምናልባት ከ110 ዓ.ቅ.ክ በፊት ከተጻፈው ከሄኖክ መጽሐፍ ወይም ከአይሁድ ትውፊት ሊሆን ይችላል፡ ይህም የተጠቀሰው ሄኖክ የተናገረው ትንቢት እውነት መሆኑን ለማስገንዘብ እንጂ ጠቅላላ የሄኖክ መጽሐፍ ትክክል ነው ብሎ መቀበሉ አይደለም::

**1፥18 በመጨረሻው ዘመን፤** 1ጢሞ 4፥1 እና ማብራሪያውን እንዲሁም 2ጢሞ 3፥1 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::

**1፥20 ራሳችሁን ለማነጽ ትጉ፤** አማኞች የሐሰት ትምህርትን እየተቃወምን በአራት መንገድ እምነታችንን መጠበቅና ማስፋፋት አለብን፡ (1) በተቀደሰ እምነታችን ራሳችንን በማነጽ፡ ይህ ቅዱስ እምነት በክርስቶስና በሐዋርያት የተሰጠ (ቍ 3) የአዲስ ኪዳን መገለጥ ነው:: ይህም የእግዚአብሔር ቃል ማጥናትን፣ እውነቱንና የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሚገባ ለመረዳት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል (ከሐሥ 2፥42፤ 20፥27፤ ከ2ጢሞ 2፥15፤ ከዕብ 5፥12 ጋር ያነጻጽሩ)::

(2) በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ፡ በሚያበረታው በመንፈስ ቅዱስ ኀይል በመታገዝ እንዲሁም በጸሎት ተግቶ ለመዋጋት በመንፈስ ቅዱስ መደገፍ ያስፈልጋል (ሮሜ 8፥26 እና ማብ ይመ፤ ከገላ 4፥6፤ ከኤፌ 6፥18 ጋር ያነጻጽሩ):: በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ አንድ ሰው በአእምሮና በመንፈስ የሚጸልየውን ጸሎት ያከተተ ነው (1ቆሮ 14፥15 እና ማብ ይመ)::

(3) እግዚአብሔር ለእኛ ባለው ፍቅር ጸንቶ በመኖር፡ ይህም እግዚአብሔርንና ቃሉን በታማኝነት መታዘዝን ይጠይቃል (ዮሐ 15፥9-10)::

(4) የክርስቶስን ዳግም ምጽአትና ከእርሱም ጋር የሚገለጠውን የዘላለም ክብር በመናፈቅና በመጠበቅ ነው (ዮሐ 14፥2 እና ማብ ይመ)::